**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን**
**The Federal Democratic Republic of Ethiopia**
**Federal Housing Corporation**

# የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር
# 451/2013

አዲስ አበባ
2011 ዓ.ም

መግቢያ ...... 1
ክፍል አንድ ...... 2
ጠቅላላ ...... 2
1. አጭር ርዕስ ...... 2
2. ትርጓሜ ...... 2
3. የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን ...... 5
4. የመመሪያው ዓላማ ...... 6
ክፍል ሁለት ...... 7
የግዥ ዕቅድ ...... 7
5. የግዥ ዕቅድ ስለማዘጋጀት ...... 7
6. የግዥ ፍላጎትን መለየት፣ ማሰባሰብ እና ማደራጀት ...... 7
7. የግዥ ዘዴ መምረጥ ...... 9
8. የግዥ መፈፀሚያ ጊዜን መወሰን ...... 9
9. የግዥ ዕቅድ ይዘት ...... 10
10. የግዥ ዕቅድ የሚፀድቅበትና የሚሻሻልበት ሁኔታ ...... 10
11. የገበያ ጥናት ...... 11
ክፍል ሶስት ...... 13
የብሔራዊ እና የዓለም አቀፍ ግዥ ዘዴዎችና አፈፃፀማቸው ...... 13
12. የተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች ...... 13
13 .ብሔራዊ ግልጽ ጨረታ ...... 14
14. ዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ ...... 50
15. የዓለም አቀፍ ጨረታ ግዥ የመወሰን ሥልጣን ...... 52
16 .የብሔራዊ ግልፅ ጨረታ ግዥ የመወሰን ሥልጣን ...... 53
17. የውስን ጨረታ ግዥ አፈፃፀም ...... 54
18. በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀም ግዥ ...... 56
19. ከአንድ አቅራቢ የሚፈጸም ግዥ ...... 61
20. በለቀማ የሚፈጸም ግዥ ...... 64
21. በመወዳደሪያ ሐሳብ መጠየቂያ የሚፈፀም ግዥ ...... 65
23. የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ የሚፈጸም ግዢ ...... 74

24. በቁርጥ ዋጋ ላይ ተመስርቶ የሚከናወን ግዥ ....................76
25. በማዕቀፍ ውል የሚፈፀም ግዥ ....................77
26. የፕሮጀክት ማኔጅመንት አገልግሎት ....................80
ክፍል አራት ....................81
የውል አስተዳደር ....................81
27. የውል ሁኔታዎች ....................81
28. የውል ማስከበሪያ ....................83
29. የቅድሚያ ክፍያ ....................85
30. ውል መፈረም ....................86
31. ውልን ተፈፃሚ ማድረግ ....................88
32. የውል አፈፃፀምን መከታተል ....................89
33. ውል ስለማሻሻል ....................91
34. ውል ስለማቋረጥ ....................91
35. ውል ማጠናቀቅ ....................93
36. ርክክብ እና ክፍያ አፈፃፀም ....................94
ክፍል አምስት ....................97
ሥልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነት ....................97
38. ዋና ሥራ አስፈፃሚ ....................97
39. ኮርፖሬት ሠርቪስ ዘርፍ ም/ዋና ሥራ አስፈፃሚ ....................99
40 የቤት ልማት ዘርፍ እና የቤት አስተዳደር ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚዎች፤ ....................100
41 የፕሮጀክት ክትትልና ኮንትራት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ....................100
42. የቤቶች ጥገናና እድሳት ዳይሬክቶሬት ....................101
43. የካርፖሬሽን ግዥና ንብረት አሰተዳደር ዳይሬክቶሬት ....................102
44. የቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጆች ....................104
45. የግዥ አፈፃፀም /የሌሎች እና የምህንድስና ግዥ/ ቡድን መሪዎች ....................105
46. የግዥ ቡድን ....................105
47. የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት ....................106
48. የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ አወቃቀር ....................107
49. የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ሰብሳቢ ኃላፊነትና ተግባር ....................107
50. የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ፀሐፊ ኃላፊነትና ተግባር ....................107
ክፍል ስድስት ....................109

51. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ........ 109

52. ተቀባይነት ያገኘ የአቅራቢዎች ዝርዝር ስለመጠቀም ........ 109
53. ብቁ ተጫራቾች ........ 111
54. የዕጩ ተወዳዳሪዎች ወይም ተጫራቾች አቤቱታ የማቅረብ መብት ........ 112
55. አቤቱታ ማቅረብ የማይቻልባቸው ሁኔታዎች ፤ ........ 112
56. ለኮርፖሬሽኑ የሚቀርብ አቤቱታ የሚጣራበት ስርዓት ........ 112
57. ኮርፖሬሽኑ የግዥ አፈፃፀም ሂደትን ማገድ ስለመቻሉ ........ 114
58. ልዩነቶች ........ 115
59. የግዥ ሠነዶች ........ 115
ክፍል ሰባት ........ 117
የኮርፖሬሽኑ የግዥ ሥነ-ምግባር ደንብ ........ 117
60. የግዥ የሥነ-ምግባር ደንብ ........ 117
61. የጥቅም ግጭትን ስለማሳወቅ ........ 118
62. ስጦታና መስተንግዶ ........ 119
63. የመረጃዎች ምሥጢርነት ........ 120
64. ተገቢ ግንኙነቶች ........ 121
65. የኃላፊነት መነጣጠል እና የሥራ ዝውውር ........ 121
66. መደበኛ እና ልዩ ኦዲት ........ 122
67. ከዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚጠበቅ ሥነ-ምግባር ........ 122
68. የግዥ መመሪያውን ስለማስተዋወቅ ........ 123
69. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች ........ 123

70. የግዥ መመሪያውን ስለማሻሻል ........ 123
71. የተሻሩ መመሪያዎች ........ 123
72. የግዥ መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ ........ 123

# የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን የግዥ አፈፃፀም መመሪያ

## መግቢያ

ፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 398/2009 መቋቋሙን ተከትሎ ግዥ ለመፈፀም የሚያስችል መመሪያ ያልነበረው በመሆኑ በኮርፖሬሽኑ የግዥ አፈፃፀም ላይ አሉታዊ ተፅእኖ በማሳደሩ፤ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት እንዲያስችል በየጊዜው የተለያዩ የዕቃ፣ የግንባታ ሥራ፣ የምክርና ሌሎች የአገልግሎት ግዥዎችን ለመፈፀም የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ፤

የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን የሚያከናውነውን ማንኛውንም ግዥ ወጥ በሆነ መንገድ በመፈፀም የዕቃ፣ የግንባታ ሥራ፣ የምክርና ሌሎች የአገልግሎት ግዥዎችን አስተማማኝ በሆነ መልኩ የግዥ ቁጥቁጥ በማስቀረት፣ ብክነትን በመቆጣጠር፤ በአነስተኛ ወጪ፣ ፍትሃዊ፣ ተመጣጣኝ እና አስተማማኝ የግብዓት አቅርቦት እንዲኖረው በማድረግ ወቅቱን የጠበቀ ግዥ በመፈፀም፣ ብልሹ አሰራርን በመቅረፍ፣ ተጠያቂነት ያለው አሰራር በመፍጠር፣ በብቃት እና በጥራት ቀጣይነት ያለው የኮርፖሬሽኑን ዕድገትና ልማት ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የፌዴራል የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001ን ለማስፈፀም ከወጣው መመሪያና ከሌሎች የልማት ድርጅቶች ጋር ተጣጥሞ የተዘጋጀ በመሆኑ፤

በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/84 አንቀጽ 14(4) ለኮርፖሬሽኑ የስራ አመራር ቦርድ በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሰረት ይህ የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

# ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ “ የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 451/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ የሚከተለው ትርጉም ይኖራቸዋል ፡

1. **አዋጅ”** ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስት የግዥ ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ነው፤
2. **“ኮርፖሬሽን”** ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 398/2009 የተቋቋመ የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ነው፤
3. **‘’ቅርንጫፍ ጽ/ቤት”** ማለት በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተሞች የሚገኙ የኮርፖሬሽኑ የቤቶች አስተዳደር ተግባራትን የሚከናውኑ ጽ/ቤቶች ናቸው፡፡
4. **’ኤጀንሲ”** ማለት የፌዴራል መንግስት ግዥ እና ንበረት አስተዳደር ኤጀንሲ ነው፤
5. **“ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን”** ማለት በአዋጅ ቁጥር 398/2009 አንቀጽ 3 መሠረት በመንግስት የተሰየመ ኮርፖሬሽኑን በበላይነት የሚቆጣጠር አካል ነው፤
6. **"ቦርድ"** ማለት የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽንን በበላይነት የሚመራ የሥራ አመራር ቦርድ ነው፤
7. **“ዋና ሥራ አስፈፃሚ”** ማለት የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽንን በበላይነት የሚመራ ነው፤
8. **“የማኔጅመንት ካውንስል”** ማለት የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ የኮርፖሬሽኑ ምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚዎች፣ የዳይሬክቶሬቶች ዳይሬክተሮች፣ የቅርንጫፍ ጽ/ቤትና የጽ/ቤት ኃላፊዎችን ያካተተ የአመራር ስብስብ ነው፤
9. **“የግዥ ሥራ ክፍል”** ማለት በኮርፖሬሽኑ ዋና መ/ቤት ስር የሚገኘው የኮርፖሬት ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት፤ እና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ስር የሚገኙ የግዥና ንብረት አስተዳደር ቡድኖች ናቸው፤
10. **"የግዥ ሠራተኞች"** ማለት በግዥ ሥራ ክፍል ግዥ እንዲፈፅሙ ኃላፊነት የተሰጣቸው ሰራተኞች ነው፤

11. **"የቴክኒክ ኮሚቴ"** ማለት በዋና መስሪያ ቤት እና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም እርሱ በሚወክለው የሚሰየም ኮሚቴ ሆኖ የግንባታ ዘርፍ ስራውን፣ የዕቃውን፣ የምክር እና ሌሎች አገልግሎቶችን ደረጃና ጥራት በተጠየቀው መስፈርት መሠረት መሆኑን ገምግሞ የውሳኔ ሀሣብ የሚያቀርብ ለግዛዊ የሚቋቋም ኮሚቴ ነው፤

12. **"የዕቃ እና ሌሎች አገልግሎት የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ"** ማለት በዋና መስሪያ ቤት እና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም እርሱ በሚወክለው የሚሰየም ኮሚቴ ሆኖ በዕቃ እና በሌሎች አገልግሎቶች የሚወጡ ጨረታዎችን ወይም በሌሎች የግዥ ዘዴዎች የተሰበሰቡ ሠነዶችን እንዲሁም የግዥ ፍሰቶችን መርምሮና ገምግሞ የሚያፀድቅ አካል ነው፤

13. **"የምህንድስና እና ዓለም ዓቀፍ የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ "** ማለት በዋናው መ/ቤት ስራን ለማቀላጠፍ ሲባል በዋና ስራ አስፈፃሚ በሚሰየሙ አባላት የሚዋቀር የአለም አቀፍ እና የብሔራዊ የግንባታ፣ የምክር አገልግሎት እና የዓለም አቀፍ ዕቃ ግዥ ጨረታዎችን መርምሮና ገምግሞ የሚያፀድቅ አካል ነው፡፡

14. **"ግዥ"** ማለት የግንባታ ስራውን፣ የዕቃውን፣ የምክር እና ሌሎች አገልግሎቶችን በግዥ፣ በኪራይ ወይም በማናቸውም ሌላ ተመሳሳይ ውል ማግኘት ነው፤

15. **"ዕቃ"** ማለት በጠጣር፣ በፈሳሽ ወይም በጋዝ መልክ የሚገኝ ጥሬ ዕቃ፣ ምርት፣ መሣሪያ፣ ሸቀጥ እና ለገበያ የተዘጋጀ ሶፍትዌር እንዲሁም ከሚገዛው ዕቃ ጋር ግንኙነት ያለው እና ከዕቃዎቹ ጋር ያልበለጠ ዋጋ ያለው የተከላ፣ የትራንስፖርት፣ የጥገናና ሌላ ተመሳሳይ አቅርቦትን ይጨምራል፤

16. **"የግንባታ ሥራ"** ማለት ከሕንፃ፣ ከመንገድ ወይም ከመሠረተ ልማት ሥራ ጋር በተያያዘ የሚከናወን የአዲስ ግንባታ፣ የመልሶ ግንባታ፣ ደረጃ የማሳደግ፣ የማፍረስ፣ የጥገና፣ የማደስ ሥራ እንዲሁም ተጓዳኝ የሆነና ከዋናው ሥራ ያልበለጠ ዋጋ ያለው አገልግሎት ሲሆን፣ እንደ አስፈላጊነቱ የመገንባት፣ በባለቤትነት የመያዝ፣ ሥራውን የማንቀሳቀስ እና የማስተላለፍ ውሎችን ይጨምራል፤

17. **"ሌሎች አገልግሎቶች"** ማለት ከዕቃ፣ ከግንባታ ስራና ከምክር አገልግሎት ውጪ ያለ ሲሆን፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ተከላ አገልግሎት፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ጥገና አገልግሎት፣ ሶፍትዌር አፕግሬዲንግ፤ ሶፍትዌር ከስተማይዜሽን፣ የተሽከርካሪ ጥገና፣ የጥበቃ፣ የፅዳት አገልግሎት፣ የማስታወቂያ፣ የሜዲያ አገልግሎት፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የቴሌኮሙኒኬሽን እና የውሃ አቅርቦት እና የመሳሰሉትን ይጨምራል፤

18. **"የምክር አገልግሎት"** ማለት አማካሪዎች ያላቸውን ሙያዊ ክህሎት በመጠቀም የሚሰጡት የጥናት፣ የዲዛይን እና ቁጥጥር፣ የተለያዩ ኘሮጀክቶችን የማደራጀት፣ ሥልጠና የመስጠት እና እውቀትን የማስተላለፍ የአማካሪነት ባህሪ ያለው የአዕምሮ ሥራ አገልግሎት ወይም ከግዥ ውሉ ጠቅላላ ዋጋ ውስጥ የምክር አገልግሎቱ ዋጋ ከ50% (ሀምሳ በመቶ) በላይ ለሚሆን ማንኛውም ግዥ ነው፤
19. **"በለቀማ የሚፈፀም ግዥ"** ማለት ከመደበኛ አቅራቢ የማይገኝ ወይም በለቀማ ቢገዛ ለኮርፖሬሽኑ የኢኮኖሚ ጥቅም የሚያስገኝ መሆኑን የተረጋገጠ የዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ ነው፤
20. **"ጨረታ"** ማለት የጨረታ ማስታወቂያው ይፋ ከሆነበት ወይም የጨረታ ግብዣ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ የጨረታው አሸናፊ ተለይቶ ውል እስኪፈረም ድረስ ያለውን የግዥ አፈፃፀም ሂደት የሚገልፅ ነው፤
21. **"የጨረታ ሠነድ"** ማለት ዕጩ ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት እንዲችሉ እንደ ግዥው አይነት ተለይቶ በኮርፖሬሽኑ የሚዘጋጅ ዝርዝር የግዥ ፍላጎትን የሚገልፅ ሰነድ ነው፤
22. **"የመጫረቻ ሠነድ"** ማለት ኮርፖሬሽኑ ለግዥው ወይም ለሽያጩ ባዘጋጀው የጨረታ ሰነድ መነሻነት ተጫራች በግዥው ወይም በሽያጩ ለመሳተፍ የሚያቀርበው ሰነድ ነው፤
23. **"የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ"** ማለት ዕቃው፣ የግንባታ ስራው፣ የምክር እና ሌሎች አገልግሎቶች ሊያሟሉ የሚገባቸውን የጥራት ደረጃ፣ ዓይነት፣ የሚሠራበትን ግብዓት፣ የሚፈለገውን የሥራ "ዝርዝር ባህሪ ወይም ተፈጥሮአዊ ሁኔታ እና ሌሎች ፍላጐቶችን የሚገልጽ ሠነድ ነው፤
24. **"የውል ሰነድ"** ማለት ኮርፖሬሽኑ የግዥውን አፈፃጸም በተመለከተ የኮርፖሬሽኑንና የአቅራቢውን መብትና ግደታን በግልጽ የሚቀመጥበት ሰነድ ነው፤
25. **"ተጫራች"** ማለት የመጫረቻ ሰነድ ያቀረበ ሰው ነው፤
26. **"አቅራቢ"** ማለት ለኮርፖሬሽኑ ዕቃ ወይም የምክርና ሌሎች አገልግሎቶች ለማቅረብ ወይም የግንባታ ዘርፍ ሥራ ለማከናወን ውል የገባ አካል ነው፤
27. **"ውስብስብ"** ማለት የመደበኛውን የግዥ አሰራር ስርዓት የተከተለ ሆኖ በተጨማሪም ግዥውን ለመፈፀም የቴክኒክ ባለሙያዎች ሙያዊ ትንታኔ የሚያስፈልገው የግዥ ባህርይ ነው።

28. **"ልዩ አስተያየት"** ማለት በልዩ ሁኔታ በአዋጁ የተገለፁት የአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት እንዲሁም የሀገር ውስጥ ተጫራቾችን ለማበረታታት የተፈቀደ የአሰራር ሂደት ነው፡፡
29. **"የገበያ ጥናት"** ማለት ኮርፖሬሽኑ ግዥ በሚያከናውንበት እና ከአቅራቢዎች ጋር ዘላቂ ግንኙነት በሚመሠረትበት ወቅት በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውሣኔ ለመስጠት እንዲረደ በዋጋ፣ በዕቃዎች፣ በግንባታ ዘርፍ ሥራዎች፣ በምክር ወይም በሌሎች አገልግሎቶች ወቅታዊ የግዢ ዋጋ ጥናት ነው፤
30. **"ለገበያ የተዘጋጀ"** ማለት ለተጠቃሚው ማህበረሰቡ ፍላጎት ተብለው የሚመረቱ ስታንዳርድን መሠረት ያደረገ የገበያ ዕቃዎች ነው፤
31. **"ጠቅላላ ዋጋ"** ማለት ኮርፖሬሽኑ ዕቃዎችን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎችን፣ የምክርና ሌሎች አገልግሎቶችን ለመግዛት ታክስን ጨምሮ ማናቸውም ሌሎች ወጪዎችን በማካተት የሚከፍለው አጠቃላይ የገንዘብ መጠን ነው፤
32. **"የማዕቀፍ ስምምነት"** ማለት የረዥም ጊዜ አቅርቦትን ታሳቢ በማድረግ በነጠላ ዋጋ እና በሌሎች የውል ሁኔታዎች ላይ በመመስረት የሚፈፀም አጠቃላይ የሆነ የግዥ ስምምነት ነው፤
33. **"መደበኛ የጨረታ ሠነድ"** ማለት የኮርፖሬሽኑ የግዥ የሥራ ክፍል አጠቃላይ ይዘቱ አንድ ወጥ ወይም ተመሳሳይ የሆነ የጨረታ ሠነድ በቀላሉ ማዘጋጀት እንዲችሉ የሚረዳ በኤጀንሲው የተዘጋጀ ሰነድ ነው፤
34. **"የጥቅም ግጭት"** ማለት የኮርፖሬሽኑ የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ወይም የቤተሰቡ ወይም የቅርብ ዘመዱ የገንዘብ ወይም ሌላ ዓይነት ጥቅም ከመደበኛ ሥራው ጋር በቀጥታ ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የሚጋጭ ወይም ግጭት ሊፈጥር የሚችል ነው፤
35. **"ስጦታ"** ማለት ለኮርፖሬሽኑ የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ከሥራው ጋር በተያያዘ የሚሰጥ ዋጋ ወይም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለው ማንኛውም ነገር ነው፡፡
36. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
37. ማንኛውም **በወንድ ፆታ** የተገለፀው የሴት ፆታንም ያካትታል፤
38. በዚህ መመሪያ ያልተተረጐመ አካራካሪ ቃላትና ሐረጐች በአዋጅ ቁጥር 649/2001 የተሰጡትን ትርጉሞች እንደ አግባብነቱ ለዚህ መመሪያ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

3. <u>የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በኮርፖሬሽኑ በሚፈፀሙ ግዥዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. የመመሪያው ዓላማ

የመመሪያው ዋና አላማ ማንኛውንም ዓይነት ግዥ በጥራት፣ በዋጋ በመጠንና በጊዜ ገምግሞ በወቅቱ ማቅረብ የሚያስችል አሰራር መዘርጋት ሲሆን ዝርዝር አላማዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

- ሀ. ግዥን ግልጽነት፣ ተጠያቂነት ወጥነት ባለው ሁኔታ እንዲፈፀም ማስቻል፤
- ለ. የግዢን ሂደት ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲከናወን ማስቻል፣
- ሐ. በግዢ ሂደት ውስጥ ለሚሣተፉ ሠራተኞች ግልጽ የሆነ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት ማስቀመጥ ፣
- መ. አጠቃላይ የግዥ ሥራ በቂ የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት የተዘረጋለት መሆኑን ማረጋገጥ፤
- ረ. የግዢ ሂደት ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለው ተመጣጣኝ ጠቀሜታ ማስገኘት መቻሉን ማረጋገጥ፣

## ክፍል ሁለት

## የግዥ ዕቅድ

5. **የግዥ ዕቅድ ስለማዘጋጀት**

   1. የኮርፖሬሽኑ የሥራ ክፍሎች የታቀዱት የሥራ ኘሮግራሞቻቸውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጋቸውን ግብአቶች የፀደቀውን በጀት መሠረት በማድረግ የግዥ ፍላጐታቸውን ለኮርፖሬት ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ያቀርባሉ፡፡ አጠቃላይ የኮርፖሬሽኑ የግዥ ዕቅዱም በኮርፖሬት ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ከተዘጋጀ በኋላ በኮርፖሬት ሰርቪስ ዘርፍ ም/ዋና ሥራ አስፈፃሚ አማካይነት ለማኔጅመንት ካውንስል ቀርቦ መጽደቅ ይኖርበታል፡፡
   2. ኮርፖሬሽኑ የሚፈፅማቸው ግዥዎች ዕቅድን መሠረት ያደረጉ መሆን አለባቸው፡፡ የሚዘጋጀው የግዥ ዕቅድ የሚከተሉትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚያስችል መሆን አለበት፤

      ሀ. በአንቀፅ 4 ላይ የተመለከቱትን የመመሪያውን ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ፣

      ለ. የኮርፖሬሽኑን የበጀት ዓመቱ ዕቅድ የሥራ ኘሮግራም ለማሳካት፣

   3. የግዥ ዕቅድ አዘገጃጀት የሚፈፀመው በግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በሚዘጋጀው የዕቅድ አዘገጃጀት ዝርዝር እና ቅጾች መሠረት ይሆናል፡፡

6. **የግዥ ፍላጎትን መለየት፣ ማሰባሰብ እና ማደራጀት**

   1. ማናቸውም የኮርፖሬሽኑ የሥራ ክፍሎች የግዥ ፍላጎት በሚያዘጋጁበት ጊዜ የሚከተሉትን ማገናዘብ ይኖርባቸዋል፡፡

      ሀ. ፍላጎቱ በኮርፖሬሽኑ ውስጥ ባለ እና ጥቅም ላይ ባልዋለ ሌላ ሀብት ወይንም ንብረት ሊሟላ የማይችል መሆኑን ማረጋገጥ፣

      ለ. ፍላጎቱ ገበያ ላይ በሚገኝ ምርት ወይንም አገልግሎት ሊሟላ የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ፣

      ሐ. የግዥ ፍላጎቱ ጥቅም ላይ የማይውሉ እሴቶችን ያላካተተ እና ኮርፖሬሽኑን ለአላስፈላጊ ወጪ የማይዳርግ መሆኑን ማረጋገጥ፣

      መ. በተለይም ለረጅም ጊዜ እንዲያገለግሉ ታስበው የሚከናወኑ ግዥዎች በሚሆኑበት ጊዜ የግዥ ፍላጎቱ ወደፊት የሚፈጠርን የፍላጎት ዕድገት ያገናዘበ መሆኑን ማረጋገጥ፣

ሠ. አስገዳጅ ሁኔታ እስካልተፈጠረ ድረስ ፍላጎቱ ገበያ ላይ በሚገኝ መደበኛ አቅርቦት ወይም ስታንዳርድ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ማረጋገጥ፣

ረ. የግዥ ፍላጎቱ የማህበረሰቡን አካባቢ ደህንነት እና ጥበቃ የማይጎዳ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

2. ኮርፖሬሽኑ በሥሩ የሚገኙ የሥራ ክፍሎችን ዓመታዊ የግዥ ፍላጎቶች ከዚህ በታች በተመለከተው ሁኔታ የኮርፖሬት ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ማሰባሰብ ይኖርበታል፡፡

ሀ. በኮርፖሬሽኑ ሥር የሚገኙ ተጠቃሚዎች ዓመታዊ የግዥ ፍላጐታቸውን እንዲያቀርቡ የበጀት ዓመቱ ከመጀመሩ በፊት ቢያንስ ከሶስት ወራት ቀደም ብሎ መጠየቅ አለበት፤

ለ. በኮርፖሬሽኑ ሥር የሚገኙ አቅራቢዎች በህትመትና በኤሌክትሮኒክስ ቅጂ (Hard Copy & Soft Copy) ማቅረብ ይኖርባቸዋል፤

ሐ. በኮርፖሬሽኑ ሥር የሚገኙ ተጠቃሚዎች የግዥ ፍላጎታቸውን ሲያቀርቡ ለዓመቱ የተያዘውን የሥራ ዕቅድና ዓመታዊ በጀትን መሠረት ማድረግ አለባቸው፤

መ. ከተጠቃሚዎች የቀረበውን ፍላጎት በግዥ ዓይነት፣ የጥራት ደረጃ በጊዜ እና በሚገኝበት ቦታ መለየት አለበት፤

ሠ. የኮርፖሬት የግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በዚህ አንቀጽ በተጠቀሰው ሁኔታ የተሰበሰበውን መረጃ በማጠናቀርና በስቶክ ከሚገኝና በግዥ ሂደት ላይ ካለ አቅርቦት ጋር እንደአስፈላጊነቱ በማቀናነስ ወይም የተቀናነሰ መሆኑን በማረጋገጥ የተጣራ ፍላጐት ያዘጋጃል፡፡

3. የኮርፖሬት የግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 2 በተጠቀሰው ሁኔታ ከተጠቃሚዎች የተሰባሰበውን ፍላጎት እና ከገበያ ጥናት የሚገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ እንዲሁም የሚከተሉትን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ግዥውን ማደራጀት አለባቸው፡፡

ሀ. በኮርፖሬሽኑ የሚገኙ የስራ ክፍሎች ዓመታዊ የግዥ ፍላጎታቸውን እንዲያቀርቡ መጠየቅ፣

ለ. ከተጠቃሚዎቹ የቀረበውን ፍላጎት በግዥ ዓይነት፣ ብዛት፣ የጥራት ደረጃ በሚገኝበት ቦታ መለየት ፣

ሐ. ኮርፖሬሽኑ ልዩ ትኩረትና ቅድሚያ የሚሠጣቸውን ዕቃዎች፣ የግንባታ ሥራንና አገልግሎቶችን መለየት ፣

መ. የቀረበው ፍላጎት በቂ አቅራቢ ያለው ወይም የሌለው መሆኑን ማጣራት፣

ሠ. በኮርፖሬሽኑ በተደረገ ጥናት ወይም ከሌሎች ምንጮች በተገኘ የገበያ መረጃ ለየግዥው የሚያስፈልገውን የዋጋ ግምት ማወቅ፣

7. **<u>የግዥ ዘዴ መምረጥ</u>**

1. የግዥ ሥራ ክፍሎች የግዥ ዕቅድ በሚያዘጋጁበት ወቅት ከተፈቀዱት የግዥ ዘዴዎች ውስጥ አግባብነት ያለውን በመምረጥ በዕቅድ ውስጥ ማመላከት አለባቸው፡፡
2. የግዥ ሥራ ክፍሎች የግዥ ዕቅዱን በሚያዘጋጁበት ወቅት የሚታወቁ የግዥ ፍላጎቶች ሁሉ በግዥ ዕቅዱ ውስጥ መካተታቸውን እና ለእያንዳንዱም ግዥ ተስማሚ የሆነ የግዥ ዘዴ መመረጡን ማረጋገጥ አለበት፡፡

8. **<u>የግዥ መፈፀሚያ ጊዜን መወሰን</u>**

1. የግዥ ሥራ ክፍል የግዥ ሂደቱ ውስጥ ዋና ዋና ተግባራት የሚያከናውኑበትን ጊዜ መወሰን አለባቸው፡፡ ለዚህም የሚከተሉትን እና እንደሚፈፀመው የግዥ ዓይነት ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ሊያስገቡ ይገባል፤

   ሀ. ግዥው በሚከናወንበት ጊዜ ከኮርፖሬሽኑ የሥራ ኘሮግራም ጋር የተጣጣመ መሆኑን፣

   ለ. በገበያ ላይ ሰፊ አቅርቦት የሚኖርበትን ጊዜ ታሳቢ ያደረገ መሆኑን፣

   ሐ. በተለይ ውስብስብ ለሆኑ እና ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ላላቸው ግዥዎች በቂ የሰነድ ማዘጋጃ፣ መገምገሚያ እና ማፅደቂያ ጊዜ የተሰጣቸው መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

2. በዚህ ግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 20 ንዑስ 20.1 በፊደል ተራ ከ"ሀ" እስከ "መ" ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ለየግዥ ዓይነቱ የሚወሰነው ጊዜ የግዥ አፈፃፀም ዋና ዋና ተግባራትን ለማከናወን ከሚያስፈልገው ጊዜ የረዘመ እንዳይሆን ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል፡፡

9. **<u>የግዥ ዕቅድ ይዘት</u>**

1. የግዥ ሥራ ክፍሎች በዚህ መመሪያ ክፍል ሦስት ስር የተዘረዘሩ ተግባራትን መሰረት በማድረግ እና በዚህ መመሪያ አባሪ የተደረገውን የግዥ ዕቅድ ማዘጋጃ ቅጽ በመጠቀም የግዥ ዕቅዳቸውን ማዘጋጀት አለባቸው፡፡ በዚህ መሰረት የሚዘጋጀው ዕቅድ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡-

   ሀ. የግዥውን ምድብና ቁጥር፣

   ለ. የግዥውን መግለጫ፣

   ሐ. የግዥውን መጠን፣

   መ. የግዥው ዝርዝር አፈፃፀም የሚከተላቸው አሠራሮች፣

   ሠ. ግዥውን ለማጠናቀቅ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት የሚፈፀሙበትን ጊዜ፣

   ረ. ለግዥው የሚያስፈልገውን የጸደቀ የበጀት እና የፋይናንስ ምንጭ፣

   ሰ. ለግዥው ተስማሚ የሆነ ውል ዓይነት፣

   ሸ. በግዥ አፈፃፀም ሂደቱ የሚሳተፉ ዋና ዋና አካላትን የተሳትፎ ሁኔታ፣

   ቀ. ሌሎች እንደ ኮርፖሬሽኑ ባህርይ ትኩረትን የሚሹ ጉዳዮችን፣

10. **<u>የግዥ ዕቅድ የሚፀድቅበትና የሚሻሻልበት ሁኔታ</u>**

1. የግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በተሰጠው የስልጣን ውክልና መሠረት ያዘጋጀውን ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ ለኮርፖሬሽኑ የኮርፖሬት ሰርቪስ ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም እርሱ ለሚወክለው ማቅረብ አለበት፣
2. የኮርፖሬሽኑ የኮርፖሬት ሰርቪስ ዘርፍ ም/ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም እርሱ የሚወክለው ሰው ዕቅዱ በዚህ መመሪያ መሰረት የተዘጋጀ መሆኑን በማረጋገጥ ለኮርፖሬሽኑ የማኔጅመንት ካውንስል አቅርቦ ያስጸድቃል፣
3. የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ የኮርፖሬሽኑ ግዥ አፈጻጸም ሂደት በፀደቀው የግዥ ዕቅድ መሠረት መመራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል አሠራር በመዘርጋት አፈጻጸሙን መከታተል አለበት፣
4. የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ የፀደቀው ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ ቅጅ ለአፈጻጸም በኮርፖሬሽኑ ለሚገኙ የሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች መላክ አለበት፣
5. በፀደቀው የግዥ ዕቅድ መሠረት የሚፈፀም ግዥ ወቅታዊ ዋጋ በዕቅዱ ከተያዘው ዋጋ ከ25 በመቶ በላይ ከጨመረ ለኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ከ50 በመቶ በላይ ከጨመረ ለኮርፖሬሽኑ ማኔጅመንት ካውንስል ቀርቦ መፅደቅ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ያልታቀደ ሥራ

በመፈጠሩ ወይም የፕሮጀክቶች አፈፃፀም በመጨመሩ ምክንያት የሚፈጠሩ የኮንስትራክሽን ሥራ ግብአቶችን ፍላጐት ለማሟላት ተጨማሪ ግዥ ማካሄድ አስፈላጊ መሆኑ በኮርፖሬሽኑ ማኔጅመንት ካውንስል ከታመነበት ግዥው ሊፈፀም ይችላል፤

6. ኮርፖሬሽኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውና በኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሲታመንበት በ 6/ስድስት/ ወር የፀደቀው የግዥ ዕቅድ በሥራ አመራር ኮሚቴ ታይቶ እንዲሻሻል ይደረጋል፡፡
7. በዚህ አንቀጽ በንዑስ 6 በተገለጸው መሠረት የተሻሻለው የግዥ ዕቅድ የመጀመሪያው ዕቅድ ለተላከላቸው በኮርፖሬሽኑ ለሚገኙ የሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች መላክ አለበት፡፡

## 11. <u>የገበያ ጥናት</u>

1. ኮርፖሬሽኑ ለሚያከናውናቸው ግዥዎች እንዲሁም ከአቅራቢዎችም ጋር ለሚመሰርታቸው ዘላቂ ግንኙነቶች ግብዓት እንዲሆን የኮርፖሬሽኑ የግዥ ሥራ ክፍሎች የገበያ ጥናት ያከናውናሉ፡፡ የገበያ ጥናቱን በግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የገበያ ጥናት ባለሙያዎች ተካሂዶ በጥናቱ የተገኙትን መረጃዎች ለሁሉም ግዥ ሥራ ክፍሎች ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ በፊት የተካሄዱ ግዥዎችንና የተጠቃሚ አካላትን ፍላጎት መሰረት በማድረግ ለሚቀጥለው የበጀት ዓመት የግዥ ፍላጎቶችን በቅድሚያ መለየት ያለበት ሲሆን የገበያ መረጃዎችንም ለመሰብሰብ የሚከተሉትን አማራጮች መከተል ያስፈልጋል፡-

    ሀ. ከዚህ በፊት ባካሄዳቸው ግዥዎች ያገኛቸው ዋጋዎች፣ የእቃ እና የአገልግሎት አይነቶች እንዲሁም ተሳታፊ አቅራቢዎችን መረጃ መሰብሰብ፣

    ለ. ተመሳሳይ ግዥ ያካሄዱ ተቋማትን በመጎብኘት በቂ መረጃ መሰብሰብ፣ እንደ አስፈላጊነቱ በሌላ አካል የተካሄዱ የገበያ ጥናቶችን እና ውጤቶችን ከጋዜጦች፣ ከፎረሞችና ተመሳሳይ ሚዲያዎች መሰብሰብ፣

    ሐ. የአቅራቢዎችን ዝርዝር የሚመለከት መረጃ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተዛምዶ ካላቸው ፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር፣ የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እና ከሌሎች ተመሳሳይ ተቋማት መሰብሰብ፣

    መ. ከዚህ በፊት ስለተገዙ ዕቃዎች፣ የግንባታ ስራዎች እንዲሁም የምክርና ሌሎች አገልግሎቶች የጥራት ደረጃ በሚመለከት አስተያየት ከተጠቃሚዎች መሰብሰብ፣

ሠ. የዕቃዎች፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ወይም የምክር እና ሌሎች አገልግሎቶች በገበያ ውስጥ ያላቸው አዳዲስ ወይም የተሻሻሉ ባህሪያትን መሰረት በማድረግ ወጥ የሆነውን የኮርፖሬሽኑን የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ለማሻሻል መረጃዎችን ማጠናቀር፤

ረ. ዕቃዎች፣ የግንባታ ሥራዎች ወይም የምክር እና ሌሎች አገልግሎቶች በገበያ ላይ ያላቸው የዋጋ ለውጥ ምን እንደሚመስል በመገምገም ግምታዊ የዋጋ ዝርዝር (Estimated price list) ማዘጋጀት፤

ሰ. ዕቃዎችን፣ የግንባታ ሥራዎችን ወይም የምክርና ሌሎች አገልግሎቶችን ሊያቀርቡ የሚችሉ አዳዲስና ነባር አቅራቢዎችን የብቃት ደረጃ በመለካት የኮርፖሬሽኑን የአቅራቢዎች ዝርዝር (Suppliers list) ለመከለስና ለሚመለከተው አካል አቅርቦ ለማፀደቅ የሚረዳ መረጃ ማዘጋጀት፡፡

# ክፍል ሶስት

## የብሔራዊ እና የዓለም አቀፍ ግዥ ዘዴዎችና አፈፃፀማቸው

### 12. የተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች

1. ኮርፖሬሽኑ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት አሰራ አንድ (11) ዓይነት የግዥ ዘዴዎች መጠቀም የሚችል ሲሆን፣ ወደፊት ሁኔታዎች ሲመቻቹ በኤሌክትሮኒክስ (e-procurement) ዘዴ መጠቀም ይቻላል፡፡

   ሀ. ግልጽ ጨረታ (Open Tender)

   ለ. ውስን ጨረታ (Restricted Tender)

   ሐ. በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀም ግዥ (Request for Quotation)

   መ. ከአንድ አቅራቢ የሚፈጸም ግዥ (Direct Purchase)

   ሠ. በለቀማ የሚፈፀም ግዥ

   ረ. በመወዳደሪያ ሃሣብ መጠየቂያ (Request for proposal) የሚፈጸም ግዥ በጥራትና በዋጋ፣ በጥራት፣ በቁርጥ በጀት፣ በዝቅተኛ ዋጋ፣ በአማካሪዎች ብቃት የተመሰረተ መረጣ፤ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም አስፈላጊ መሆኑ ሲታመን እና አንድ አማካሪ የሚመረጥበት ሁኔታ

   ሰ. በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ (Two Stage Tender)

   ሸ. በቅድመ ብቃት ማረጋገጫ የሚፈፀም ግዥ

   ቀ. በቁርጥ ዋጋ ላይ ተመስርቶ የሚካሄድ ግዥ (Fixed price procurement)

   በ. በማዕቀፍ ውል የሚፈፀም ግዥ

   ተ. የፕሮጀክት ማኔጅመንት አገልግሎት

2. በአዋጁ በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ኮርፖሬሽኑ ማናቸውንም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈፀም አለበት፡፡
3. ኮርፖሬሽኑ ከግልጽ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈጸም የሚችለው በዚህ መመሪያ የተገለጹት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ነው፡፡
4. ኮርፖሬሽኑ ከግልፅ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች በሚጠቀምበት ጊዜ በእነዚህ ዘዴዎች ለመጠቀም የመረጠበትን ምክንያት እና ሁኔታዎች የሚገልጽ ሠነድ መያዝ ይኖርበታል፡፡

5. ከላይ ከተዘረዘሩት  የግዢ ዘዴዎች  ውጪ ግዢ መፈጻም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለስራ አመራር ቦርድ ቀርቦ ሲፈቀድ ሊፈጸም ይችላል፡፡

13 .**ብሔራዊ ግልጽ ጨረታ**

በኮርፖሬሽኑ በግልፅ ጨረታ ዘዴ ግዥን ለመፈፀም በኤጀንሲው የተዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ መጠቀምና በዚህ አንቀፅ ስር የተዘረዘሩትን አፈፃፀሞች መከተል አለባቸው፡፡

1. ቅድመ ሁኔታዎች

ኮርፖሬሽኑ ብሔራዊ ግልፅ ጨረታ መጠቀም የሚችለው፡-

ሀ. በአገር ውስጥ ተጫራቾች ተሳትፎ የሚፈለገውን ግዥ ማጠናቀቅ እንደሚቻል ሲያረጋግጥ እና ግዥው በአንቀፅ 15 ንዑስ  2( ለ )በተቀመጠው መሠረት ለዓለም አቀፍ ጨረታ ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በታች ሲሆን ወይም፣

ለ. በንዑስ አንቀፅ 15 ንዑስ 2( ለ) ላይ የተገለፀው የገንዘብ ገደብ ቢኖርም ምርቱ ወይንም አገልግሎቱ ብቁ ውድድር ለማድረግ በሀገር  ውስጥ ተጫራቾች በኩል መቅረብ የሚችል መሆኑ ከተረጋገጠ ወይም ግዥው በብሔራዊ ግልፅ ጨረታ ቢፈፀም በተሻለ ጥራትና ፍጥነት እንዲሁም በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርብ መሆኑ በዝርዝር ተገምግሞ በኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሲፈቀድ በአገር ውስጥ ግልፅ ጨረታ ሊካሄድ ይችላል፡

2. የጨረታ ጥሪ

የጨረታ ጥሪው በቂ ቁጥር ያላቸው ተወዳዳሪዎች በጨረታው እንዲሳተፉ ለማድረግ አገራዊ ሽፋን  ባለው ጋዜጣ ቢያንስ ሁለት ጊዜ ታትሞ ማውጣት ወይም በብሔራዊ የሬዲዮ እና  ቴሌቪዥን ጣቢያ እንደዚሁም በኮርፖሬሽኑ ድረ-ገፅ መተላለፍ ያልበት ሲሆን የጨረታ ጥሪ ማስታወቂያ ቢያንስ የሚከተሉትን ፍሬ ነገሮች ሊይዝ ይገባል፡-

ሀ.  የጨረታው ጥሪ በማስታወቂያ እንዲወጣ ያደረገው የኮርፖሬሽኑ የሥራ ክፍል  ስምና አድራሻ፣

ለ. የሚቀርበውን ዕቃ ወይም አገልግሎት አይነት፣  ብዛት እና ርክክቡ የሚፈጸምበትን ቦታ ወይም የግንባታ ሥራዎችን ዓይነት እና የሚከናወንበትን ቦታ ወይም የአገልግሎቱን ዓይነት እና የሚሰጥበትን ቦታ፣

ሐ.በጨረታው መሣተፍ የሚችሉ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ሊያሟሉ የሚገባውን መስፈርት፣

መ. የጨረታው ሰነድ የሚገኝበት ቦታ፣ቫት ተመዝጋቢ  እና ግብር የከፈለ መሆኑ፤

ሠ. የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና መጠንና ዓይነት፣

ረ. የጨረታውን ሠነድ ለመውሰድ የሚከፈለው ዋጋ፣ በምን ሀገር ገንዘብ እንደሚከፈል እና የአከፋፈሉ ዘዴ፣

ሰ. ኮርፖሬሽኑ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሠረዝ መብት ያለው መሆኑን፣ መግለጫ፣

ሸ. የጨረታው ሠነድ የተዘጋጀበትን ቋንቋ፣

ቀ. ለተጫራቾች መገለጽ እንዳለባቸው በኮርፖሬሽኑ የታመነባቸው ሌሎች ጉዳዮች፣

በ. የጨረታው ጥሪ የጨረታ ሰነዱ በሚዘጋጅበት ቋንቋ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

3. የጨረታ ሰነድ

ሀ. ኮርፖሬሽኑ ጨረታ በሚያወጣበት ጊዜ ወጥነት ያለው  የተዘጋጀው መደበኛ የጨረታ ሰነድ ጥቅም ላይ  ሲያገኘው  እንደ ጨረታው ተጨባጭ ሁኔታ የጨረታ ሰነድ ማዘጋጀት ይችላል፡፡

ለ. የግንባታ እና የምክር አገልግሎት ግዥ ጠያቂ ክፍሎች የጨረታ ሰነድ በሚያዘጋጁበት ወቅት በኤጀንሲው ከተዘጋጀ መደበኛ የጨረታ ሰነድ ውስጥ በተጫራቾች መመሪያና አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ላይ ምንም ለውጥ ሳያደርጉ በሌሎች የሰነዱ ክፍሎች ላይ እንደግዥው ዓይነትና ባህርይ ማሻሻያ በማድረግ ሰነዱን ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

ሐ. የጨረታ ሠነድ በግዥ ጠያቂ የሥራ ክፍል ተዘጋጅቶ ለግዢ እና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ከቀረበና ከተረጋገጠ በኋላ በግዥ አጽዳቂ ኮሚቴው ጸድቆ ሥራ ላይ ይውላል፡፡

4. የተጫራቾች መመሪያ

ኮርፖሬሽኑ የሚያዘጋጀው የተጫራቾች መመሪያ የሚከተሉትን ያካተተ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡-

ሀ. ኮርፖሬሽኑ ጨረታውን የመሰረዝ መብት እንዳለው፣

ለ. የሚገዛውን ዕቃ ወይም የግንባታ ሥራ፣ የምክር እና ሌሎች አገልግሎቶች አጠቃላይ መግለጫ፣ የኮርፖሬሽኑ ሙሉ ስምና አድራሻ እንዲሁም የግዥውን የፋይናንስ ምንጭ፣

ሐ. በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች ስለሚያሟሏቸው መስፈርቶች የሚገልጽ ሆኖ ከወጣው ጨረታ ውስጥ ብር 100,000.00 /አንድ መቶ ሺህ/ እና ከዚያ በላይ

ዋጋ በማቅረብ በጨረታው የሚሳተፍ ማንኛውም የአገር ውስጥ ተጫራች በተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የተመዘገበ መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ እንዳለበት እንዲሁም የውጭአገር ተጫራቾች በሚሆኑበት ጊዜ እንደ አግባብነቱ በተቋቋሙበት አገር የተሰጣቸውን የኩባንያ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም ፈቃድ ማቅረብ መጠቀሱን፣

መ. በጨረታ ሠነድ ግልጽ ያልሆኑ ጉዳዮችን አስመልክቶ ማብራሪያ የሚጠየቅበትን አድራሻ እና የማብራሪያ ጥያቄው በጽሑፍ ማቅረብ እንደሚገባው የሚያመለክት መግለጫ፣

ሠ. ዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚያቀርቡት የመጫረቻ ሠነድ ይዘት ምን መሆን እንዳለበት፣ በምን ቋንቋ እንደሚዘጋጅ፣ በመደበኛ የጨረታ ሠነድ ውስጥ የተገለጹ እና በተጨማሪነት የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን እና ቅጾችን ዓይነት እና ብዛት፣

ረ. ተጫራቾቹ የማጭበርበር ድርጊት እና ሙስናን በሚመለከት በኢትዮጵያ ሕጎች የተደነገገውን የሚያከብር መሆኑን በማረጋገጥና ከጨረታ ሠነዱ ጋር ተያይዞ የሚገኘውን ሙስና ላለመፈጸም ቃል የሚገባበትን ቅጽ እና ሌሎች በተጫራቹ ተሞልተው እንዲቀርቡ የሚፈለጉ ቅፆችን ሞልቶና ፈርሞ ማቅረብ እንዳለበት፣

ሰ. የጨረታውን አካሄድ ለማዛባት የሚሞክሩ ተጫራቾች ከጨረታው ውጪ እንደሚሆኑ፣ ለወደፊትም በኮርፖሬሽኑ ግዥ እንዳይሳተፉ እንደሚደረግ እና ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ለኮርፖሬሽኑ ገቢ እንደሚሆን የሚያመለክት መግለጫ፣

ሸ. የዕቃዎቹ ናሙናዎች በተጨራቾች እንዲቀርቡ የሚያስፈልጉ ከሆነ ተፈላጊዎቹ ናሙናዎች የሚቀርቡበት እንደ አስፈላጊነቱ በተጫራቾች የሚታዩበትን ጊዜ እና ቦታ እንዲሁም እነዚህ ናሙናዎች በጨረታው ለተሸነፉ ተጫራቾች የሚመለሱ ወይም ሊመለሱ የማይችሉ መሆናቸውን፣

ቀ. የጨረታ ሳጥኑ የሚገኝበት ቦታ እና ጨረታው ከተዘጋ በኋላ የሚቀርብ የመጫረቻ ሠነድ ተቀባይነት እንደማይኖረው የሚገልጽ መግለጫ፣

በ. ጨረታውን ለመገምገም በሥራ ላይ የሚውሉትን ዘዴዎች፣ ለዚሁ ግምገማ የሚያገለግሉ መስፈርቶች እና እያንዳንዱ መስፈርት የሚኖረውን የነጥብ ድርሻ፣

እንዲሁም ሁለት እና ከሁለት በላይ የሆኑ ዕጩ ተወዳዳሪዎች  በግምገማው እኩል ቢሆኑ አሸናፊውን ተጫራች ለመለየት የመወዳደሪያ ሃሣብ የሚቀርብበት ሁኔታና መስፈርቶች፣

ተ. በውል አፈጻጸም ወቅት የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ መቻል አለመቻሉን እና የዋጋ ማስተካከያ  ማድረግ የሚፈቀድበት ሁኔታ ፣

ቸ. የተጠየቀውን የጨረታ ማስከበሪያ የውል አፈፃፀም ዋስትና መጠን እና ዓይነት እንዲሁም  እነዚህ ዋስትናዎች ፀንተው የሚቆዩበትን ጊዜ፣

ኀ. የመጫረቻ ሠነድ ማስረከቢያ ጊዜ የሚያበቃበትን እና ጨረታው የሚከፈትበትን ቦታ፣ ቀን እና ሰዓት፣

ነ. የጨረታው ዋጋ ጸንቶ የሚቆይበትን ጊዜ እንዲሁም የርክክቡን ቦታና ጊዜ፣

ኘ. ጨረታው በአንድ ወይም በሁለት ፖስታዎች የሚቀርብ ስለመሆኑ፣ስለ ፖስታዎቹ አስተሻሸግ፣ አንድ ወጥ የሆኑ ዋና እና ቅጂ ሠነዶች መቅረብ እንዳለባቸው የቅጂዎችን ብዛት፣ ሠነዶቹ ሥልጣን ባለው አካል የተፈረመባቸው መሆኑ እንደሚገባ እና ማህተም እንደሚያስፈልጋቸው፣ እንዲሁም ደጋፊ ማረጋገጫዎች /በአቅራቢነት ለመመዝገብ፣ ወቅታዊ ግብር ክፍያ ምስክር ወረቀት፣ የታደሰ ንግድ ፈቃድ እና ሌሎች ኮርፖሬሽኑ አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ደጋፊ ሠነዶች/ ስለሚቀርቡበት ሁኔታ፣

አ. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 29 በተደነገገው መሠረት የቅድሚያ ክፍያ የሚሰጥ ከሆነ የቅድሚያ ክፍያውን መጠን እና ተቀባይነት ያለውን የዋስትና ዓይነት፤

ከ. ተጫራቾች በጨረታ አፈፃፀም ሂደት ቅሬታ ካላቸው አቤቱታ የማቅረብ መብት እንዳላቸው እና አቤቱታው የሚቀርብበትን ቦታ፣

ኸ. ኮርፖሬሽኑ ከአሸናፊው ተጫራች ጋር ውል ከመፈረሙ በፊት በጨረታ ሠነዱ ከተገለጸው የአቅርቦት መጠን ላይ መጨመር ወይም መቀነስ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በአሸናፊው ተጫራች የቀረበው በውድድር የተገኘው ዋጋ ሳይቀር እስከ 25% /ሀያ አምስት በመቶ/መጨመር ወይም መቀነስ እንደሚችል፣ በመቶኛ የተሰላው በዕቃው ቁጥር ብዛት ሲገለጽ ከአንድ በታች ከሆነ የሚጨመረው ዕቃ አንድ ሊሆን ይችላል፣

ወ. በመደበኛው ጨረታ ሰነድ የተጫራቾች መመሪያ ይዘት ላይ ምንም ዓይነት ማሻሻያ ማድረግ አይቻልም። በተጫራቾች መመሪያ ላይ የሚደረጉ ለውጦች የሚመለከቱት በጨረታ ዝርዝር መረጃሠንጠረዥ (Bid Data Sheet) ላይ ነው፤

ዐ. ተጫራቾች የሚያቀርቡት የመወዳደሪያ ሃሣብ ሊይዝ የሚገባውን ዝርዝር ማለትም የዕቃውን ዓይነት፣ የአምራቹን ስም፣ የተመረተበት ሀገር፣ ሞዴል፣ የተመረተበትን ዓመት፣

ዘ. የሀገር ውስጥ ተጫራቾች ግብር የመክፈል ግዴታቸውን የተወጡ መሆኑን የሚያረጋግጥ ከግብር ሰብሳቢው ባለሥልጣን የተሰጠ ማስረጃ እና አግባብ ያለው የታደሰ የንግድ ፈቃድ ማቅረብ እንዳለባቸው፣

ዠ. ተጫራቾች በሚያቀርቡት የመወዳደሪያ ሃሣብ ስማቸውን፣ ፊርማቸውን፣ የድርጅት ማህተምና አድራሻቸውን ማስፈር እንዳለባቸው፤

የ. ጨረታው ከተከፈተ በኃላ ተጫራቾች ባቀረቡት የመወዳደሪያ ሃሣብ ላይ ለውጥ ወይም ማሻሻያ ማድረግ፣ ከጨረታው ራሳቸውን ማግለል እንደማይችሉ የሚያመለክት መግለጫ፣

ደ. ተጫራቾች በጨረታ ሠነድ ላይ የማብራሪያ ወይም የማሻሻያ ሲጠየቁ ጨረታውን ላወጣው የግዥ ሥራ ክፍል በፅሁፍ ማቅረብ የሚችሉ መሆኑን፤

ጀ. ለሀገር ወስጥ ምርትና ኩባንያዎች በአዋጁ የተፈቀደውን ልዩ አስተያየት ዝርዝር አፈፃፀም የሚያመለክት መግለጫ።

5 የቴክኒክ ፍላጐት መግለጫ (Technical Specification)

ሀ. ኮርፖሬሽኑ በተለይም በተፈጥሯቸው ውስብስብና ከፍተኛ ወጪ ለሚጠይቁ ግዥዎች ዝርዝር የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት አለበት፤

ለ. በሚመለከተው ዳይሬክቶሬት ወይም ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የፀደቀውን የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የጨረታው ሠነድ አንድ ክፍል መሆን የለበት ሲሆን በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ አቅራቢዎች የተሟላና ትክክለኛ የመወዳደሪያ ሃሣብ እንዲያዘጋጁ በሚያስችል ዓይነት ተሟልቶ እና በዝርዝር ተዘጋጅቶ መቅረብ አለበት። የሚዘጋጁት

ዝርዝሮች ግልጽ፣ ትክክለኛ፣ የተሟሉ እንዲሁም ገዳቢ ያልሆኑና ውድድርን የሚያበረታቱ መሆን አለባቸው፤

ሐ. ቴክኒክ ፍላጎት መግለጫዎች ኮርፖሬሽኑ በሚያካሄዳቸው የገበያ ጥናቶች ላይ በመመርኮዝ በየጊዜው ክለሳ የሚካሔድላቸው ሲሆን በክለሳውም ወቅት አዳዲስየኮርፖሬሽኑ ፍላጎቶች እና የቴክኖሎጂ ለውጦች ከግምት ውስጥ መግባት ይኖርባቸዋል፤

መ. የቴክኒክ ፍላጐት መግለጫው በጨረታው መሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች የተሟላና ትክክለኛ የመጫረቻ ሠነድ እንዲያዘጋጁ በሚያስችል ዓይነት ተሟልቶ እና በዝርዝር ተዘጋጅቶ የጨረታው ሰነድ አንድ ክፍል መሆን አለበት፤

ሠ. የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በሚዘጋጀበት ጊዜ የተወሰነን አምራች የንግድ ምልክት ወይም አገልገሎት ሰጪ ማመልከት የለበትም ። ሆኖም ፍላጎትን በትክክል ሊገለፅ የሚችል መግለጫ ማዘጋጀት አስቸጋሪ ሆኖ ሲገኝ ወይም ግዥው ለተለየ ፕላንት ወይም መሣሪያ የሚያስፈልጉ መለዋወጫዎችን የሚመለከት ሲሆን ወይም የተፈለጉትን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ማቅረብ የሚችል አንድ አምራች ወይም አገልግሎት ሰጪ ብቻ መሆኑ ሲረጋገጥ የአምራቹን ወይም የአገልግሎት ሰጪውን ስም በመጥቀስ ወይም ተመሳሳይ የሚል ሐረግ እንዲታከል ማድረግ ያስፈልጋል፤

ረ. የሚዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የኮርፖሬሽኑን የአሁን ወይም ወደፊት ሊፈጠር የሚችል ፍላጎትን ለማርካት የሚያስችሉ የጠቀሜታ ዕሴቶችን ለመግለፅ የሚያስችል እና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ዕሴቶችን የማያካትት መሆኑ መረጋገጥ አለበት፤

ሰ. ኮርፖሬሽኑ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በሚያዘጋጅበት ጊዜ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ወይም እንደግዥው ዓይነት አግባብ ያለቸው ሌሎች አካላት የሚያወጧቸውን ደረጃዎች በዝርዝሩ ውስጥ ሊያካትት ይችላል።

6. የጨረታ ቅጽና የዋጋ ማቅረቢያ ሠንጠረዥ

ሀ. ኮርፖሬሽኑ ለጨረታ በሚያዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ውስጥ በተጫራቾች ሊሞላ የሚገባውን የጨረታ ቅፅ፣ ዋጋና ተያያዥ ጉዳዩችን ማቅረቢያ ቅፅ ወይም ሠንጠረዥ እና በመደበኛ የጨረታ ሠነዱ ውስጥ እንደ ግዥው ዓይነት እና ሁኔታ መካተታቸው ተገቢ ነው ተብሎ የሚታመንባቸው ሌሎች ቅፆችን ማካተት አለበት፤

ለ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ 6(ሀ) መሠረት ኮርፖሬሽኑ የሚያዘጋጀው የዋጋ ማቅረቢያ ቅፅ ፤ ዋጋ፣ ታክስን እና ሌሎችን ከዋጋ አቀራረብ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በግልጽ ለማመልከት የሚያስችል እንዲሁም የጨረታ ግምገማን ግልፅና ቀልጣፋ ማድረግ የሚችል መሆን አለበት፤

ሐ. የሚዘጋጀው የጨረታ ቅፅ በተቻለ መጠን ዕጩ ተወዳዳሪው ግልፅ የሆነ የመወዳደሪያ ሃሣብ እንዲያቀርብ የሚያስችል፣ የጨረታ አካሄዱን መረዳቱን የሚያረጋግጥ፣ ጨረታውን የሚያደናቅፍ ድርጊቶች እንዳይፈጸሙ የሚከላከል እና ተጫራቹ ላቀረበው የመወዳደሪያ ሃሣብ ሙሉ ኃላፊነት እንዲወስድ የሚያደርግ መሆን ይኖርበታል።

7. አጠቃላይና ልዩ የውል ሁኔታዎች

ሀ. ኮርፖሬሽኑ የመደበኛ የጨረታ ሠነድ ክፍል ሆነው የተዘጋጁትን የአጠቃላይ እና የልዩ ልዩ ውል ሠነድ ቅጂዎችን የጨረታው ሰነድ ክፍል አድርጐ ለተጫራቾች መስጠት አለበት፤

ለ. በመደበኛ ጨረታ ሰነዱ አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ላይ ማሻሻያ ሊደረግባቸው አይችልም። ልዩ የውል ሁኔታዎች ግን እንደሚፈፀመው ግዥ ባህርይና ዓይነት አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ላይ የሰፈሩትን አንቀጾች ማጣቀስ አለበት፤

ሐ. በዚህ አንቀጽ ንዑሰ 7(ሀ) እና “ ለ ” የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮርፖሬሽኑ የሚያዘጋጀው ልዩ የውል ሁኔታ እንደግዥው ዓይነት ሊለያይ ቢችልም የተጫራቹንና የኮርፖሬሽኑን ግዴታና ኃላፊነት፣ በግልጽ ያመላከተና በኮርፖሬሽኑ ላይ የሚጣሉ ግዴታዎች ህጋዊ መሠረት ያላቸውና ሊፈጸሙ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣የውሉ አፈጻጸም የሚከተላቸውን ዋና ዋና ሂደቶች፣ የማስረከቢያ ጊዜ፣ አስተሻሸግ፣ የማጓጓዝ ኃላፊነት፣ የዋጋ ማስተካከያ፣ የክፍያ አፈፃፀም፣ የርክክብ እና የፍተሻ ሥነ-ሥርዓት፣ ዋስትና እና የመሳሰሉትን አተገባበር በግልጽ ያስቀመጠ መሆን ይኖርበታል።

8. የጨረታ መገምገሚያ መስፈርት አዘገጃጀት

1. ኮርፖሬሽኑ የመጫረቻ ሰነድ የሚገመገምበትን መስፈርት በመደበኛ የጨረታ ሰነዱ የብቃትና የግምገማ መስፈርቶች ክፍል ላይ በግልፅ ማሳየት ይኖርበታል

2 የጨረታ መገምገሚያ መስፈርት እንደግዥው አይነት የሚለያይ ቢሆንም ከሚከተሉት ሁለት መሠረታዊ የመምረጫ ዘዴዎች በአንዱ ተፈፅሚ መሆን ይኖርበታል፡-

ሀ. ለግዥው ተቀባይነት ያለው ዝቅተኛ የቴክኒክ መመዘኛ መስፈርት በመወሰን ዝቅተኛ የቴክኒክ መመዘኛውን ካሟሉት ተጫራቾች መካከል አነስተኛ ዋጋ ያቀረበውን ተጫራች መምረጥ፣ ወይም

ለ. ግዥው የሚኖረውን ጠቀሜታ ወይንም ኢኮኖሚያዊ እሴት ሊወስኑ የሚችሉ መስፈርቶችን እና እያንዳንዱ መስፈርት የሚኖረውን አንፃራዊ ክብደት በግልፅ በጨረታ ሠነዱ ላይ በማሳየትና በነዚህ መስፈርቶች ላይ የተመሠረተ ግምገማ በማካሄድ በአጠቃላይ ውጤት (Combined Evaluation Result) ከፍተኛ ነጥብ ያገኘውን መምረጥ፣

3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ (2) ፊደል (ሀ) እና (ለ ) ላይ በተገለጸው መንገድ ግምገማ ለማካሄድ የሚመረጥ መስፈርት ግዥው ማስገኘት የሚችለውን ከፍተኛ ጥቅም እንዲያስገኝ ከማድረግ አንፃር በተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሰረተና እስከተቻለ ድረስ በገንዘብ ሊገለጽ የሚችል ሆኖ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡-

ሀ. የሚገዛው መደበኛ ወይም ደረጃው የታወቀ አቅርቦት በሚሆንበት ጊዜ፣ ለኮርፖሬሽኑ ጠቃሚ የሆነ እና በተጫራቾች መካከል ልዩነት ሊፈጠር የሚችል የተለየ እሴት ሊቀርብበት የሚችል መሆን አለመሆኑን፤ ወይም

ለ. ኮርፖሬሽኑ ካስቀመጠው ዝቅተኛ መስፈርት በተጨማሪነት የሚቀርብ እሴትተጨማሪ ፋይዳ ማስገኘት አለማስገኘቱን፣ ወይም ተጨማሪው እሴት ለኮርፖሬሽኑ የሚሰጠውን ጥቅም ዝቅተኛነትና ከፍተኛነት፤

ሐ. የሚገዛው ዕቃ ደረጃ ያልወጣለትና ተጨማሪ ፋይዳ ከመፍጠር አንፃር ስፔስፊኬሽኑን በተለያየ ደረጃ ሊያሟሉ የሚችሉ ተቀራራቢ ዕቃዎች መኖር አለመኖራቸውን፤

መ. ዕቃው ለረጅም ጊዜ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ሆኖ የአቅርቦቱ ምንጭ በመለያየቱ ምክንያት የተለያየ መጠቀሚያ፣ የመያዣ እንዲሁም የማስወገጃ ወጪ የሚፈልግ መሆን አለመሆኑን፤

ሠ. ከላይ በተራ ፊደል “ለ” ላይ የተገለጸውን ግምት ውስጥ በማስገባት የግዥ ጠያቂው ክፍል ይህን አማራጭ ሲጠቀም የመረጠበትን ምክንያት በማስረጃ ማቅረብ አለበት፡

4 በዚህ አንቀጽ ንዑስ (3) መሠረት በተገለፀው ሁኔታ ለቢሮ መገልገያ መሣሪያዎች፣ ለኮንስትራክሽን መሣሪያዎች፣ ለተሽከርካሪና ለግንባታ ለመሳሰሉት ግዥዎች ጨረታ ግምገማና ምዘና የሚሰጠው ነጥብ ከዚህ በታች በተገለፀው መሠረት ሊሆን ይገባል፡-

ሀ. የተገምጋሚው የጨረታ ዋጋ (Evaluated Bid Price)………..ከ30-50 ነጥብ

ለ. የቴክኒክ መስፈረት (Techincial Features)……………..…...ከ45-60 ነጥብ

ሐ. ቴክኒካል ያልሆኑመስፈርቶች (Non-Techinical Features)…. ከ10-25 ነጥብ

መ. የማቅረቢያ ጊዜ (Delivery Time)………………………….....ከ0-5 ነጥብ

ሠ. የድህረ-ሽያጭ አገልግሎት (After Sales Service)…...............ከ0-10 ነጥብ

ረ. ዋስትና (Warranty)……………………………………………...ከ0-5 ነጥብ

ሰ. የተረጋገጠ ብቃት (Proven performance)……………………….ከ0-5 ነጥብ

ሸ. መሣሪያው በኮርፖሬሽኑና በአገር ውስጥአስቀድሞ ሥራ ላይ የዋለ መሆኑ (Standardization) ……………………………………….….ከ 0-5 ነጥብ

5 .በቴክኒክ ብቃት 70 (ሰባ)በመቶ በታች ያገኙ ተወዳዳሪዎች ውድቅ ተደርጐ 70 (ሰባ) በመቶ እና ከዚህ በላይ የሚያገኙት ተወዳዳሪዎች የዋጋ ማቅረቢያ ፖስታ ተጫራቾች በተገኙበት ይከፈታል፡፡ በቴክኒካል ብቃትና ቴክኒካል ባልሆኑ መስፈርቶች ተቀባይነት ያላገኙ ተጫራቾች የፋይናንሻል ሰነዳቸው ሳይከፈት ተመላሽ ይደረግላቸዋል፡፡

6 .በቴክኒካል ብቃትና ቴክኒካል ባልሆኑ መስፈርቶች ተቀባይነት ያገኙ ተጫራቾች የፋይናንሻል ግምገማ ውጤት ከቴክኒካልና ቴኒክኒካል ካልሆኑ መስፈርቶች ውጤት ጋር ተደምሮ ከፍተኛ ነጥብ ያገኘው የጨረታው አሸናፊ ተደርጎ ይመረጣል፡፡

ሀ. የሌሎች አገልግሎቶች ግዥ አፈፃፀም በሥራ ላይ የሚውለው የግምገማ ዘዴ በዚህ አንቀጽ ንዑስ 8 (4) መሠረት ላይ የተገለፀው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተፈፃሚ የሚሆንና፣ ለቴክኒካል ብቃትና ቴክኒካል ላልሆኑ መስፈርቶች የሚሰጠው ክብደት ብቃትን ለማረጋገጥ ሆኖ ውድድሩ ግን ዋጋን መሰረት ያደረገ ይሆናል፡፡

ለ. የኮርፖሬሽኑ የግንባታ ሥራ ግዥ ውድድር ዝቅተኛ ዋጋን መሰረት ያደረገ ሆኖ በዚህ አንቀፅ ንዑስ 8 (4) "ሀ" እና "ለ" መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

9 ጨረታ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበትን ጊዜ

1. ኮርፖሬሽኑ የጨረታ ሠነድ በሚያዘጋጅበት ጊዜ የመጫረቻ ሠነድ የሚቀርብበት የመጨረሻ ቀን የሚከተሉትን መሰረት አድርጎ ይወስናል፡-

ሀ. ዕጩ ተወዳዳሪዎች የጨረታ ሠነዱን ለማግኘት፣ ተቀባይነት ያለው የመጫረቻ ሠነድ ለማዘጋጀት፣ መረጃ ለማሰባሰብ፣ ለመተንተን፣ እንደአግባብነቱ ሽርክና መመስረት፣ ከአምራቹ የሚሰጥ ውክልና እና የመፈረም ሥልጣን ማረጋገጫ ለማግኘት እና ሌሎች በጨረታው ለመሳተፍ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት የሚፈጅባቸውን ጊዜ ፤

ለ. ግዥው በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የሚፈጸም ሲሆን የመጫረቻ ሠነዱን የጨረታ ማቅረቢያው ቦታ ድረስ ለመላክ የሚያስፈልገውን ጊዜ፤

ሐ. በተለይ የግንባታ ሥራ ግዥ በሚሆንበት ጊዜ ለግንባታ ቦታ ጉብኝትና ከጨረታ በፊት ለሚደረግ ቅድመ ጨረታ ውይይት የሚያስፈልገውን ጊዜ፤

መ. ጨረታ በአየር ላይ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ከዚህ በታች ከተገለፀው ቀን ያነሰ መሆን የለበትም፡-

## ሠንጠረዥ-1

| ተ.ቁ | | | የግዥው የተሳትፎ ሽፋን /በቀን/ | |
|---|---|---|---|---|
| | | | ግልፅ ጨረታ | ውስን ጨረታ |

| | የግዥው ዓይነት | ውስብስብነት (Complexity) | ዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ | ብሔራዊ ግልጽ ጨረታ | የውጭ አገር ተጫራች የሚሳተፉበት | የአገር ውስጥ ተጫራች ብቻ የሚሳተፉበት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የግንባታ | ውስብሰብ | 45 ቀናት | 30 ቀናት | 45 ቀናት | 30 ቀናት |
| | | ውስብሰብ ያልሆነ | 35 ቀናት | 21 ቀናት | 35 ቀናት | 21 ቀናት |
| 2 | የዕቃ | ውስብሰብ | 45 ቀናት | 30 ቀናት | 45 ቀናት | 30 ቀናት |
| | | ውስብሰብ ያልሆነ | 35ቀናት | 15 ቀናት | 35ቀናት | 15 ቀናት |
| 3 | የሌሎች አገልግሎት | ውስብስብ | 45 ቀናት | 30 ቀናት | 45 ቀናት | 30 ቀናት |
| | | ውስብስብ ያልሆነ | 35 ቀናት | 15 ቀናት | 35 ቀናት | 15 ቀናት |
| 4 | የምክር አገልግሎት | | | | | |
| 4.1 | የፍላጎት መግለጫ (EOI) | ውስብስብ | 14 ቀናት | 10 ቀናት | ---- | ---- |
| | | ውስብስብ ያልሆነ | 10 ቀናት | 7ቀናት | ----- | ----- |
| 4.2 | የመወዳደሪያ ሀሳብ ማቅረቢያ | ውስብስብ | 45 ቀናት | 30 ቀናት | 35 ቀናት | 30 ቀናት |
| | | ውስብስብ ያልሆነ | 35 ቀናት | 35 ቀናት | 21 ቀናት | 15 ቀናት |

ረ. ውስብስብ ያልሆኑ ግዥዎች ዝርዝር ከዚህ በታች በተገለፀው ሠንጠረዥ ሠፍሯል፡-

## <u>ሠንጠረዥ-2</u>

| ዕቃዎች | የግንባታ ሥራዎች | የምክር አገልግሎት | ሌሎች አገልግሎች |
|---|---|---|---|
| 1. ለገበያ የተዘጋጁ የፅሕፈት መሣሪያዎች<br>2. ለገበያ የተዘጋጁ የፅዳት ዕቃዎች<br>3. ለገበያ የተዘጋጁ ኮምፒውተሮች እናተጓዳኝ ዕቃዎች<br>4. ለገበያ የተዘጋጁ ፕሪንተሮች<br>5. ለገበያ የተዘጀ የቢሮ መገልገያ ዕቃዎች<br>6. የመኪና ጎማ<br>7. ለገበያ የተዘጋጁ ልዩ ልዩ መለዋወጫዎች (ለምሳሌ የተሽከርካሪ፣ የቢሮ መገልገያ ማሽኖች)<br>8. ለገበያ የተዘጋጁ የኤሌክትሪክ፣ ኤለክትሮኒክስና ኢሌክትሮሜካኒካል ዕቃዎች<br>9. ለገቢያ የተዘጋጁ የቢሮ መገልገያ ማሽኖች (ለምሳሌ ፋክስ፣ ፎቶ ኮፒ ፣ መጠረዣ ማሽን)<br>10. የግንባታ ዕቃዎች (ለምሳሌ ሲሚንቶ፣ ብረት፣ አሸዋ፣ ቧንቧ፣ ቀለም፣ እንጨት፣ ምስማር)<br>11. የምግብ ጥሬ ዕቃ እና የተዘጋጀ ምግብ<br>12. የነዳጅና ልዩ ልዩ ቅባቶች<br>13. ለገበያ የተዘጋጁ ልብሶች፣ ጨርቆች እና ጫማዎች<br>14. ለገቢያ የተዘጋጁ መድሐኒቶች እና የሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች<br>15. ኬሚካሎች እና ሪኤጀንቶች<br>16. መፃሕፍት እና ጆርናሎች<br>17. ሌሎች ተመሳሳይነት ያላቸው | 1. የህንፃ እድሳት<br>2. የቀለምቅብ ሥራ<br>3. የጊዚያዊ ቤቶች ሥራ<br>4. የአጥር ሥራ<br>5. የቢሮ መከፋፈል /ፖርትሽን ሥራ/<br>6. ሌሎች ተመሳሳይነት ያላቸው | 1. ዝርዝር የጥናት አካሄድ (Methodology) ማቅረብ የማይጠየቁ የምክር አገልግሎት ግዥዎች<br>2. ሌሎች ተመሳሳይነት ያላቸው | 1. የህትመት<br>2. የተሽከርካሪ ጥገና<br>3. የመሣሪያዎች እና ዕቃዎች ኪራይ<br>4. የቢሮ ዕቃዎች እና የቢሮ ማሽኖች ጥገና<br>5. የትራንስፖርት ኪራይ<br>6. የሆቴል መስተንግዶ<br>7. የቧንቧ እና የኤሌክትሪክ ጥገና<br>8. የስልጠና<br>9. የኦዲት አገልግሎት<br>10. የጥበቃ እና ፅዳት<br>11. የግዥ አገልግሎት<br>12. የግቢ ማስዋብና ማስተካከል<br>13. የቢሮ ማስዋብ<br>14. የቢሮ ኪራይ<br>15. ሌሎች ተመሳሳይነት ያላቸው |

ሰ. ከአንድ አቅራቢ እንዲሁም በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ በሚፈፀም ግዥ የመጫረቻ ሰነድ የማቅረቢያው ጊዜ የግዥውን ዓይነት ፣አስቸኳይነት፣ ውስብስብነት፣ የአቅራቢዎቹን የተሳትፎ ሽፋን፣ እና የመሳሰሉ ጉዳዮችን መሠረት በማድረግ በኮርፖሬሽኑ ይወስናል፤

ሸ. ግዥው የሚፈፀመው የሁለት ደረጃ ጨረታ የግዥ ዘዴን መሠረት በማድረግ በሚሆንበት ጊዜ፤በመጀመሪያ ደረጃ እንደግዥው ዓይነት በዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ ወይም በብሔራዊ ግልፅ ጨረታ ለሚፈፀም ውስብስብ ግዥ የተፈቀደው ዝቅተኛ

የጨረታ መቆያ ወይም የመጫረቻ ሰነድ የሚቀርብበት የመጨረሻ ጊዜ ተፈፃሚ የሚደረግ ሲሆን፤ በሁለተኛው ደረጃ በኮርፖሬሽኑ በውድድር ተሳታፊ እንዲሆን የተመረጡት የተወሰኑ የአገር ውስጥ ወይም የውጭ አገር ተጫራቾች ለሚሳተፉበት የውስን ጨረታ ለውስን ጨረታ የተፈቀደው ዝቅተኛ ጊዜ ተፈፃሚ ይሆናል፤

ቀ. የኮርፖሬሽኑ የግዥ ሥራ ክፍሎች ከዚህ በላይ የተገለፀው ዝቅተኛ የመጫረቻ ሰነድ ማዘጋጃና  ማቅረቢያ ጊዜ መሆኑን በመረዳት እንደ ግዥው ዓይነት እና የገበያው ሁኔታ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች እንደ አስፈላጊነቱ ተጨማሪ ጊዜ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

10. የጨረታ ሰነድ ሽያጭ

1. ለማንኛውም ጨረታ የተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ የመሸጫ ዋጋ የሚከተሉትን ግምት ውስጥ በማስገባት በኮርፖሬሽኑ የሚወሰኑ ይሆናል፡-

ሀ. የጨረታ ሰነድ መሸጫ ዋጋ ኮርፖሬሽኑ ለግዥው በርካታ ተወዳዳሪዎች እንዳያገኝ የሚያደርግ መሆን የለበትም፤

ለ. ኮርፖሬሽኑ ለማንኛውም የጨረታ ሰነድ የዋጋ ተመን በሚወሰኑበት ወቅት ትርፍን ማዕከል ያላደረገና ለሰነድ ዝግጅቱ የወጣውን ወጪ ለመተካት ብቻ ያለመ መሆን ይኖርበታል፡

2. ኮርፖሬሽኑ የሚከተሉትን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደ አስፈላጊነቱ የጨረታ ሰነድ በነፃ እንዲሰጥ ወይም ለጨረታ ሠነድ ዝግጅቱ ከወጣው ወጪ ባነሰ ለተጫራቾች እንዲሸጥ ሊፈቀድ ይችላሉ፡-

ሀ. በጨረታው በቂ ተወዳዳሪ አይኖርም ተብሎ ሲገመት፣ ወይም

ለ. ጨረታ ሠነድ ዝግጅቱ የወጣው ወጪ ግምት በጣም አነስተኛ ነው ብሎ ኮርፖሬሽኑ ሲያምን፣

ሐ. ለጨረታ ሠነድ ዝግጅቱ የወጣው ወጪ ግምት ከፍተኛ በመሆኑ ወጪውን ሙሉ በሙሉ ተጫራቾች እንዲሸፍኑ ቢደረግ የጨረታ ሰነዱ የመሸጫ ዋጋ ከፍተኛ ስለሚሆን በቂ ተወዳዳሪ እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል ብሎ ሲያምን፣

መ. ጨረታው በድጋሚ እንዲወጣ የተደረገ እና በመጀመሪያው ጨረታ ለመሣተፍ ሰነድ የገዙ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን እንደገና እንዲገዙ ማድረግ ተገቢ አለመሆኑ በኮርፖሬሽኑ ሲታመን፡፡

3. የጨረታ ሠነድን በድረ-ገፅ በሚጫንበት ወቅት የሚከተሉትን ሁኔታዎች ታሳቢ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡-

ሀ. ኮርፖሬሽኑ አስፈላጊውን ሁኔታ በማመቻቸት ለማንኛውም ጨረታ የሚያዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ በኮርፖሬሽኑ ድረ-ገጽ ላይ ሊያወጣ ይችላል፤

ለ. የጨረታ ሠነዱ ላይ ምንም ዓይነት ለውጥ እንዳይደረግ ለመከላከል በድረ-ገጽ ላይ የሚጫነው ሰነድ የኮርፖሬሽኑ ማህተም ያረፈበት፣ ሊለወጥ በማይቻል መንገድ የተዘጋጀ መሆን ይኖርበታል፤

ሐ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 10.3 /ለ/ በተገለፀው መንገድ ተዘጋጅቶ በድረ-ገጽ ላይ እንዲወጣ የተደረገው የጨረታ ሰነድ ቅጅ በግዥ ሥራ ክፍል ውስጥ በጥንቃቄ መቀመጥ ይኖርበታል፤

መ. የጨረታ ሰነዱ ጨረታው ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ እስከሚዘጋበት ጊዜ ድረስ ባሉት የሥራ ቀናት በጨረታ ማስታወቂያው በተገለፀው አኳኋን ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ዝግጁ መሆን አለበት፡፡

11. ስለ ናሙና አቀራረብ

1. የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ ወይም ከተዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በተጨማሪነት ግዥው በተሻለ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው የናሙና ምልከታ ሲኖረው መሆኑ ሲታመንበት ኮርፖሬሽኑ በተጨማሪነት ናሙና ሊያቀርብ ወይም እንዲያቀርብ ሊያደርግ ይችላል፡

2. ኮርፖሬሽኑ ናሙና ራሱ አቅርቦ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ለእይታ በቀረበው ናሙና መሠረት እንዲያቀርቡ በሚፈለግበት ወቅት፡-

ሀ. በኮርፖሬሽኑ የሚቀርበው ናሙና በአንድ አምራች ወይም የንግድ ምልክት በተሠራ ዕቃ የተወሰነ መሆን የለበትም፡፡ እስከተቻለ ድረስ ተቀባይነት ያላቸው ናሙናዎች ዓይነት ለእይታ እንዲቀርቡ ሆኖ ከቀረቡት ናሙናዎች ጋር ተመሳሳይ የሆነ የጥራት ደረጃ ያላቸው ሌሎች ዕቃዎችንም ማቅረብ እንደሚቻል ለተጫራቾች ማሳወቅ ይገባል፣

ለ. ዕጩ ተወዳዳሪዎች ናሙናውን በግልፅ የሚያዩበት ቦታ ላይ መደረጉን እና ተገቢ እሰከ ሆነ ድረስ ስለ ናሙናው መግለጫ የሚሰጥ ባለሙያ መመደቡን ማረጋገጥ፣

ሐ. ኮርፖሬሽኑ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ዕይታ ካቀረበው ናሙና በተጨማሪ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የሚያዘጋጅ ከሆነ የሚዘጋጀው መግለጫ እስከተቻለ ድረስ የቀረበውን ናሙና የሚገልፅና ለዕይታ ከቀረበው ናሙና የቴክኒክ ባሕርይ ጋር የተጣጣመ ሊሆን ይገባል፡፡

3. በተሰጣቸው የቴክኒክ ፍላጎት መሠረት ዕጩ ተወዳዳሪዎች ናሙና እንዲያቀርቡ በሚፈለግበት ወቅት፡-

ሀ. የሚቀርቡት ናሙናዎችን አይነት፣ብዛት፣ የሚቀርቡበትን ጊዜ እና አኳኋን ዕጩ ተወዳዳሪዎች በግልፅ እንዲያውቁት መደረግ ይኖርበታል፣

4 ተጫራቾች የተሟላ ናሙና በአካል ማቅረብ የማይችሉ ሲሆን እና የማይችሉበትን ምክንያት ኮርፖሬሽኑ ሲቀበለው ሰለ ናሙናው ያላቸውን መረጃ ማቀረብ እንዲችሉ ሊፈቀድ ይችላል፡፡ይህም የናሙናውን ፎቶግራፍ ወይም የተገኘውን የናሙና ክፍል ማቅረብን ይጨምራል፡፡ ሆኖም በዚህ መልኩ ተፈፃሚ ለማድረግ የሚቻለው አፈፃፀሙ የተሻለውን ተጫራች በመመረጥ ሒደት ልዩነት የማያመጣ እና በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ልዩነት ሊፈጠር የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

5 ኮርፖሬሽኑ በተጫራቾች የቀረቡ ናመናዎችን በጥንቃቄ የመያዝ እና የመፈተሽ ኃላፊነት አለበት፡፡ ሆኖም ተጫራቾች የቀረቡት ናሙና በሚመረምርበት ወቅት በዕቃው ባሕርይ ምክንያት ቢጠፋ ወይም ቢበላሽ ካሣ አይከፈላቸውም፡፡ በምርመራ ሂደት ያልጠፉ ወይም ያልተበላሹ ናሙናዎች ከምርመራ በኋላ ለተጫራቾች ተመላሽ ይደረጋሉ፡፡ ተጫራቾች ያቀረቡትን ናሙና የጨረታው ወቅት ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ በ 6 ወር ጊዜ ውስጥ ካልወሰዱ በውርስ ለኮርፖሬሽኑ ገቢ ይደረጋል፡፡

6. የአሸናፊው ተጫራች ናሙና እቃው ገቢ ሆኖ እስከ 3 ወር ድረስ በናሙናነት ተይዞ መቆየት ያለበት ሲሆን ናሙናውም በርክክብ ወቅት ለማነፃፀሪያነት እንዲያገለግል መደረግ ይኖርበታል፡፡

12. በጨረታ ሰነድ ላይ ስለሚደረግ ማብራሪያ ወይም ማሻሻያ

1. ኮርፖሬሽኑ በራሱ ወይም የጨረታ ሠነድ ከገዙት ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ መስጠት ወይም የጨረታ ሠነዶችን ይዘት ማሻሻል ይችላል ፡፡ በተጨማሪም ኮርፖሬሽኑ ባዘጋጀው የጨረታ ሠነድ ላይ ከማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ የሚቀርብ የማብራሪያ ወይም የማሻሻያ ጥያቄ ሲቀርብ ተቀብሎ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ (1) የተደነገገው ቢኖርም የሚከተሉትን ሳያሟላ ለቀረበ ማብራሪያ ወይም የማሻሻያ ጥያቄ ኮርፖሬሽኑ ምላሽ እንዲሰጥ አይገደድም፡፡

ሀ. በዚህ መመሪያ በተገለፀዉ መሰረት ጨረታው ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ዝቅተኛ ጊዜ 30 (ሰላሳ) ቀናት ለሆነ ውስብስብ የአገር ውስጥ ግዥ ለመጫረቻ ሠነድ ማቅረቢያ የተወሰነው ጊዜ ሊያበቃ ከ10 (አስር) ቀናት በታች ሲቀረው ለቀረበ ጥያቄ፣

ለ. ለዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ ለመጫረቻ ሠነድ ማቅረቢያ የተወሰነው ጊዜ ሊያበቃ ከ21 (ሃያ አንድ) ቀናት በታች ሲቀረው ለቀረበ ጥያቄ፣

ሐ. ጨረታው ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ዝቅተኛ ጊዜ 15 (አስራ አምስት) ቀናት ብቻ ለሆነ ውስብስብ ያልሆነ ግዥ ጨረታው ሊዘጋ ከ5 (አምስት) ቀናት በታች ሲቀረው ለቀረበ ጥያቄ፣

3. ዕጩ ተወዳዳሪዎች ለሚቀርብ የማብራሪያ ጥያቄ የሚሰጠው ምላሽ በጽሁፍ ሆኖ የጠያቂው ማንነት መግለጽ ሳያስፈልግ ለሁሉም በጨረታው ተሳታፊ ለመሆን ላመለከቱ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሙሉ በተመሳሳይ ጊዜ እንዲላክ መደረግ አለበት፡፡

ሀ. ኮርፖሬሽኑ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚቀርብለትን የማብራሪያ ጥያቄ መነሻ በማድረግ ቀደም ሲል ኮርፖሬሽኑ በተዘጋጀ የጨረታ ሠነድ ላይ ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የጨረታ ሠነዱን ማሻሻል ይችላል፡፡ ማንኛውም የጨረታ ሠነዱን ይዘት የሚቀይር ማሻሻያ በተጨማሪ የጨረታ ሠነድነት የጨረታውን ሠነድ ለገዙ ሁሉ በእኩል ጊዜ እንዲደርስ መደረግ አለበት፡፡

ለ. ኮርፖሬሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ (3)(መ) ላይ በተገለጸው መሰረት በጨረታ ሠነዱ ላይ ማሻሻያ ሲያደርግ ጨረታውን ለመዝጋት በቀረው ጊዜ ውስጥ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የተደረገውን ማሻሻያ አካተው የመጫረቻ ሠነድ ለማዘጋጀት እንደማይችሉ ሲገመት የጨረታ መዝጊያ ቀኑን ማራዘም ይኖርበታል፡፡

ሐ. ኮርፖሬሽኑ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን በኮርፖሬሽኑ በተዘጋጀ የጨረታ ሠነድ ላይ የጨረታ ሠነድ የገዙትን ተጫራቾች በሙሉ የማብራሪያና የማሻሻያ ገለፃና ውይይት ለማድረግ ሊጠራ ይችላል፡፡ የሚደረገው ውይይትም በቃለ ጉባኤ መያዝ ይኖርበታል፡፡

መ. ዕጩ ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ሠነዳቸውን በሚያዘጋጁበት ወቅት ማሻሻያውን መካተት እንዲችሉ በተደረገው የጨረታ ሠነድ ማሻሻያና ማብራሪያ ውይይት የተያዘው ቃለ

ጉባኤ ቅጂ የጨረታው ሠነድ ለገዙ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሙሉ እንዲደርስ መደረግ አለበት፡፡

13. የጨረታ ቋንቋ

1. የሚዘጋጀው የጨረታ ማስታወቂያ፣ የጨረታ ሰነድ እና ጨረታው የሚካሄድበት ቋንቋ በሚከተለው ሁኔታ ይወሰናል፡፡

   ሀ. የአገር ውስጥ ተጫራቾች ብቻ ለሚሳተፉበት የብሔራዊ ግልፅ ጨረታ በአማርኛ ቋንቋ ይሆናል፡፡ ሆኖም ኮርፖሬሽኑ የጨረታ ቋንቋው በእንግሊዘኛ መሆኑ የተሻለ ውድድርና ጠቀሜታ እንዳለው ሲያምን የጨረታ ማስታወቂያው፣ የጨረታ ሠነዱ እና የጨረታው ሂደት በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲሆን ሊፈቅድ ይችላል፤

   ለ. ለዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ ማስፈፀሚያ የሚዘጋጅ ማናቸውም ሰነድ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ይሆናል፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ 13.1 “ሀ” የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ሰነዶቻቸውና ደጋፊ ማስረጃዎቻቸው በጨረታ ሰነዱ ጨረታው እንዲካሄድበት ከተፈቀደው ውጭ በሌላ ቋንቋ የተዘጋጀ በሚሆንበትጊዜ የጨረታውን መሠረታዊ ይዘት ሊቀይሩ የሚችሉ ሰነዶች በሕጋዊ ተርጓሚ ከተተረጎመ ቅጂ ጋርአንድ ላይ በማድረግ ማቅረብ አለባቸው፡፡

3. ኮርፖሬሽኑ በተጫራቹ የቀረበው ሰነድ በመጀመሪያ በተዘጋጀበት እና ለጨረታው በተፈቀደው ቋንቋ ትርጉም መካከል ልዩነት እንዳለው ሲያረጋግጥ ልዩነቱ በጨረታው ይዘት ላይ መሠረታዊ ለውጥ አያመጣም ብሎ ካላመነ በስተቀር ሰነዱን ውድቅ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

14. የጨረታ ዋጋ

1. ኮርፖሬሽኑ ከተጫራቾች የሚሰጡ የመጫረቻ ዋጋዎች በሌላ ተጫራች ዋጋ ላይ ያልተመሰረቱ እና በጨረታው እና በውል አፈፃፀም ወቅት የማይለዋወጥ ፅኑ ዋጋ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ (1) የተገለፀው ቢኖርም ኮርፖሬሽኑ የሚከተሉት ሁኔታዎች መኖራቸውን ሲረዳ ለግንባታ ሥራዎች ውሉ ተፈፃሚ መሆን ከጀመረበት አስራ ሁለት ወራት በኋላ በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈፀም ግዥ ውሉ ተፈፃሚ መሆን ከጀመረበት ሶስት ወራት በኋላ ለሚኖር ግዥ የዋጋ ለውጥ መደረጉ ተገቢነቱን በሚገባ ትረጋግጦ በጨረታ ሰነዱ ላይ ሊታዩ የሚገቡ ሁኔታወች በተመለከተ፣

ሀ. በውል ስምምነት መሠረት የግንባታ ሥራውን ለማጠናቀቅ ከ18 ወራት እንዲሁም በማዕቀፍ ስምምነት ጊዜ የውል ግዴታውን ለማጠናቀቅ ከ 6 ወራት በላይ የሚፈጅ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን፤

ለ. በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈጸም ግዥ የዋጋ ማስተካከያ ለማድረግ የሚያስችል መነሻ እና የተለወጠው ወቅታዊ ዋጋ በኮርፖሬሽኑ በሚከናወነው የገበያ ዋጋ ጥናት መነሻ ወይም ማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ የሚሰጥ ሲሆን፤

ሐ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ (2) ፊደል ተራ (ለ) የተገለጸው ቢኖርም በኮርፖሬሽኑ በሚዘጋጀው የገበያ ዋጋ ጥናት መረጃ /ኢንዴክስ/ መሰጠት ባልቻለባቸው ስብስቦች ላይ ኮርፖሬሽኑ የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ ይገባል ብሎ ሲያምን ለውጥ የሚደረግባቸውን ስብስቦች በያዘው ምድብ ላይ ማስተካከያ ለማድረግ የሚያስችል የዋጋ መረጃ ከታወቀ የአገር ውስጥ አምራች ድርጅት ወይም በውጭ አገር ከሚገኝ ሕጋዊ ተቋም ማግኘት ሲቻል፡

15. ለግንባታ ሥራ ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ

1. ለግንባታ ሥራ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ በዚህ አንቀጽ ንዑስ. (12.2) ፊደል ተራ “ሀ” የተገለጹት ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ከግንባታ ሥራ እና ከመሣሪያዎች ወይም ተሽከርካሪዎች የአገልግሎት ኪራይ ግዥ ጋር በተያያዘ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ ከዚህ በታች የተገለጹትን አሠራሮች ተከትሎ በመደበኛ የጨረታ ሠነዱ ላይ የተመለከተውን ቀመር በመጠቀም መሰላት ይኖርበታል፡፡

   ሀ. በሥራቸው የተለያዩ ዕቃዎች ስብስቦችን የያዙት ዋና ዋና ግብዓቶች፣ ከግንባታ ሥራው ጠቅላላ ግብዓቶች ውስጥ የሚኖራቸውን ድርሻ በማስላት የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግባቸውን እና የማይደረግባቸውን መወሰን፣

   ለ. ጨረታው ከመዘጋቱ በፊት በሥራ ላይ ያለው የዋጋ ጠቋሚ አሃዝ /ኢንዴክስ/ በግልጽ በተቀመጠው መለኪያ መሠረት የዋጋ ማስተካከያውን ለማስላት በመነሻነት ይወሰዳል፤

   ሐ. የዋጋ ማስተካከያው ጥያቄ በዚህ አንቀጽ ንዑስ 12.2 የተገለጸውን ድንጋጌ ተከትሎ በሚቀርብበት ወቅት በተለይ ለግንባታ ሥራ ግዥ የዋጋ ልዩነት የሚሰላው በሥራ ላይ ያለውን ወቅታዊ የዋጋ ጠቋሚ አሃዝን/ ኢንዴክስ/ በመጠቀም በቀመሩ መሠረት ይሆናል፣

መ. በዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል ተራ "ሐ" መሠረት የሚለዩት ዋና ዋና ግብዓቶች የዋጋ ለውጥ ከግንባታ ሥራው አንፃር የሚኖራቸውን አንፃራዊ ዝቅተኛ እና ከፍተኛ ድርሻ ላይ ተመስርቶ መለየት፡፡

ሠ. የዋጋ ማስተካከያውን ለመሥራት መነሻ ዋጋ የሚወሰድበትን ትክክለኛ ቀን እና የዋጋ ለውጡ መረጃ የሚገኝበትን ምንጭ መለየት፣ በዚህ መሠረት የሚለየው የመነሻ ዋጋ ቀን ጨረታው ሊዚጋ ከ15 እስከ 30 ቀን ሲቀረው ባለው ጊዜ ውስጥ መሆን ይኖርበታል፡፡ ጨረታው በተለያየ ምክንያት ከ15 ቀናት በላይ የሚራዘም ከሆነ የመነሻ ዋጋ ቀኑም በተመሳሳይ መስተካከል ይኖርበታል፡፡

ረ. ዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚጠቀሙበት የዋጋ መነሻ መረጃ ምንጭ ስልጣን ያለው መንግስታዊ የሆነ አካል መሆን ይኖርበታል፡፡

ሰ. የዋጋ ማስተካከያ ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ውስጥ በማስተካከያው ምክንያት የተፈጠረው ልዩነት ከግንባታ ሥራው ጠቅላላ የውል ዋጋ 25% /ሃያ አምስት በመቶ/ በሚበልጥበት ጊዜ ለውጡን ተቀብሎ ግዥውን መቀጠሉ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚያስገኝ መሆኑን ተረድቶ ተገቢውን ውሣኔ መሰጠት እንዲችል የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ እንዲፈቅድ መደረግ አለበት፡፡

16. በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈጸም ግዥ የሚደርግ የዋጋ ማስተካኪያ

1. ኮርፖሬሽኑ የዋጋ ማስተካከያ ሊያደርግ የሚችለው በሚከተለው አኳኋን ይሆናል፡-

ሀ. የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግባቸው የሚመለከተው የመንግስት አካል ወይም ኮርፖሬሽኑ በሚያከናውነው የገበያ ዋጋ ጥናት ወቅታዊ የዋጋ መረጃ ለሚሰጥባቸው አቅርቦቶች ብቻ መሆን አለበት፣

ለ. በማዕቀፍ ስምምነት መሠረት ተፈፃሚ ለሚሆን ግዥ የሚቀርብ የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ መቅረብ የሚኖርበት ስምምነቱ ሥራ ላይ ከዋለ ከሶስት ወራት በኂላ ሊሆን `ይገባል፡፡

ሐ. የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግበትን ዕቃ ወይም አገልግሎት አስመልክቶ ጨረታው በተከፈተበት  ዕለት የነበረው ኮርፖሬሽኑ ወይም የሚመለከተው የመንግስት አካል የሚያወጣው ዋጋ እና የማዕቀፍ ስምምነቱ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግበት ጊዜ በውሉ ስምምነቱ ላይ መገለጽ አለበት፣

መ. ኮርፖሬሽኑ በውሉ ላይ በተገለጸው እና በጨረታው መክፈቻ ዕለት ተፈፃሚ በነበረው እና ወቅታዊውን ዋጋ አስመልክቶ በሚመለከተው የመንግስት አካል

ወይም በኮርፖሬሽኑ የገበያ ጥናት መሰረት በተሰጠው ዋጋ መካከል ያለውን የዋጋ ልዩነት በማስላት ልዩነቱ በአቅራቢው ዋጋ ላይ እንዲጨመር ወይም እንዲቀነስ በማድረግ የሚቀጥለው የዋጋ ማስተካከያ ጊዜ እስከሚደርስ ድረስ የተስተካከለውን ዋጋ ተፈፃሚ ማድረግ አለበት፣

ሠ. አቅራቢው በውል ስምምነቱ መሠረት ማቅረብ ሲገባው በወቅቱ ላላቀረበባቸው እና ዘግይተው ለቀረቡ አቅርቦቶች መቅረብ በነበረባቸው ወቅት በነበረው ዋጋ መሠረት ብቻ ይሆናል፡፡

17.የምክር አገልግሎት ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ

ሀ. በምክር አገልግሎት ግዥ የውል አፈፃፀም ወቅት የአማካሪው ስህተት ባልሆነ ምክንያት የውል መፈጸሚያ ጊዜው በመራዘሙ ለአማካሪው የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ኮርፖሬሽኑ ሲያምነበት የዋጋ ማሰተካከያ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ሆኖም ለአማካሪዎች የሚደረገው የዋጋ ማስተካከያ ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ አምስት ከመቶ (5%) ሊበልጥ አይችልም፡፡

ለ. ኮርፖሬሽኑ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግባቸው ዕቃዎች ወይም አቅርቦቶች ግዥ በሚዘጋጀው የጨረታ ሠነድ ላይ የሚከተሉትን ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ሁኔታዎች በግልጽ ማመልከት ይኖርበታል፡፡ በዚህ መሰረት የዋጋ ማስተካከያውን ተግባራዊ ለማድረግ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ከመጫረቻ ሠነዳቸው ጋር ማቅረብ ያለባቸውን የመረጃ ዓይነት፣ የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄው የሚቀርብባቸውን ሁኔታዎች ፣የአቀራረብ ዘዴውን እና ከዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ ማስረጃዎችን ዓይነትና መጠን፣ ሌሎች ለዋጋ ማስተካከያ አፈፃፀም ይጠቅማሉ ተብሎ የሚታመንባቸውን መረጃዎች እና ተጫራቾች ሊከተሉት ይገባል የሚላቸውን አሠራሮች፡፡

ሐ. ኮርፖሬሽኑ በጨረታ ግምገማ ወቅት ተጫራቾች ለዋጋ ማስተካከያ ዓላማ የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎች መቀበላቸውን እና ያቀረቧቸውን ማስረጃዎችም ተቀባይነት ያላቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡

መ. ኮርፖሬሽኑ እና በጨረታ ውድድሩ አሸናፊ የሆነው ተጫራች በሚያደርጉት የውል ስምምነት ላይ የሚከተሉት እና ሌሎች ተገቢ ናቸው ተብሎ የታመነባቸው ሁኔታዎች በግልጽ እንዲካተቱ መደረግ ይኖርበታል፡፡በዚህ መሰረት የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግላቸውን ግብዓቶች በመጠቀም የሚመረቱ ዕቃዎችን ወይም አቅርቦቶችን ዝርዝር አሃዝ የማስተካከያውን አፈፃፀም፣ አቅራቢው የተስማሙበት የሠነድ ዓይነት እና ምንጭ፣

ለዋጋ ማስተካከያ የሚቀርበው ማስረጃ በውሉ ላይ በተገለጸው መሠረት መሆን እንዳለበት እና ከሌላ ምንጭ የሚመጣ መረጃ ተቀባይነት እንደማይኖረው፣ አቅራቢው በውል ስምምነቱ መሠረት በወቅቱ ሥራውን ወይም አቅርቦቱን ማከናወን ባለመቻሉ የሚፈጠር የዋጋ መናር ማስተካከያ የማይደረግበት ስለመሆኑ፣

ሠ. የዋጋ ማስተካከያ ተግባራዊ ሂደት ውስጥ በማስተካከያው ምክንያት የተፈጠረው ልዩነት ከግንባታ ሥራው ጠቅላላ የውል ዋጋ 25% (ሃያ አምስት በመቶ) በሚበልጥበት ጊዜ የዋጋ ለውጡን ተቀብሎ ግዥውን መቀጠሉ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚያስገኝ መሆኑን ተረድቶ ተገቢውን ውሳኔ መወሰን እንዲችል ለኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ቀርቦ መወሰን አለበት፡

ረ. ኮርፖሬሽኑ የዋጋ ማስተካከያ ለተፈቀደበት ማንኛውም ግዥ አቅራቢው የዋጋ ማስተካከያ ጥየቄ ባይቀርብም የክፍያ ጥያቄ ሲቀርብለት የዋጋ ማሰተካከያ እንዲደረግባቸው በዉል ስምምነቱ በተፈቀዱ ግብዓቶች ላይ የዋጋ መቀነስ አለመኖሩን የማጣራትና የዋጋ ቅናሽ ካለም አስለቶ ከቀረበው የክፍያ ጥያቄ ላይ ከቀነሰ በኋላ መክፈል ይኖርበታል፡፡

18. የመጫረቻ ሠነድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ

1. ኮርፖሬሽኑ የመጫረቻ ሠነድ ፀንቶ መቆየት ያለበትን ጊዜ በጥንቃቄ በመወሰን በጨረታ ሰነዱ ውስጥ ማካተት ይኖርበታል፡፡ የመጫረቻ ሰነድ ወይም የጨረታው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንደ ግዥው አይነት ሊለያይ የሚችል ቢሆንም ጊዜውን ለመወሰን ኮርፖሬሽኑ የሚከተሉተን ማገናዘብ ይኖርበታል፡፡

   ሀ. የግዥውን ውስብስብነት እና የጨረታ አፈፃፀም ሂደቱ ሊወስድ የሚችለው ጊዜ፣

   ለ. በጨረታው ሊሳተፉ የሚችሉ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን ብዛት፣

   ሐ. ኮርፖሬሽኑ ተመሳሳይ ግዥዎችን በመገምገም ረገድ ያለው ልምድ፣

   መ. ግዥው በገበያ ላይ ያለው የዋጋ ተለዋዋጭነት ሁኔታ፣

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ 1 ላይ በተገለፀው መሠረት የሚወሰነው የጨረታ ዋጋ ፀንቶ ለማፀደቅ፣ አቤቱታ ቢነሳ ለማስተናገድ እና ከአሸናፊው ድርጅት ጋር ውል እስከ መፈራረም ድረስ የሚፈጀውን ጊዜ ታሳቢ ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ 2 ላይ በተገለጸው መሠረት የመጫረቻ ሰነድ ረዘም ላለ ጊዜ ጸንቶ የሚቆይበት ሁኔታ መኖሩን ኮርፖሬሽኑ ካላመነ በስተቀር ጨረታው ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ጨረታው ከሚከፈትበት ዕለት ጀምሮ ከ60 /ስልሳ/ ቀናት መብለጥ የሌለበት ሲሆን እንደአሰፈላጊነቱ ለስራ አስፈጻሚ ቀርቦ ቀኑ ሊጨመር ይችላል፡፡

4. ኮርፖሬሽኑ የመጫረቻ ሰነዱ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ የግዥ ሂደቱን ማጠናቀቅ እና ከአሸናፊው ድርጅት ጋር ውል መፈራም ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች የግዥ ሂደቱ ሳይጠናቀቅ ለግዥው የቀረበው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ የሚያበቃ መሆኑን ኮርፖሬሽኑ ሲረዳ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ዋጋቸው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ለተጨማሪ ቀናት እንዲያራዝምለት መጠየቅ አለበት፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ 4 ላይ በተመለከተው መሠረት ተጫራቾች እንዲያራዝሙ የሚጠየቁት ተጨማሪ ቅናት ኮርፖሬሽኑ የቀረውን የግዥ ሒደት ለማጠናቀቅ የሚበቃው ያህል ቀናት ብቻ መሆን አለበት፡፡ ሆኖም ተጫራቾች በማንኛውም ምክንያት ዋጋቸው ጸንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ለማራዘም ፈቃደኛ ባይሆኑ ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዙትን ዋስትና መውረስ ሳያስፈልግ ከጨረታው ውድድር እንዲወጡ ይደረጋል፡፡
6. ያቀረቡት ዋጋ ጸንቶ የሚቆይበትን ጊዜ የማሻሻያ ጥያቄ የተቀበሉ ተጫራቾ ጥያቄውን መቀበላቸውን እና የመቆያ ጊዜውን ያራዘሙት እስከመቼ እንደሆነ በመጥቀስ በጽሁፍ ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታም ለዚህ ጨረታ ያስያዙት የጨረታ ዋሰትና መቆያ ጊዜ ማሻሻያ ወይም አዲስ ዋስትና ማቅረብ አለባቸው፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ 6 በተገለፀው መሠረት የጨረታ ዋስትናውን ጸንቶ መቆያ ጊዜ ያላሻሻለ ተጫራች ያቀረበው ዋጋ ጸንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ለማሻሻል ፈቃደኛ እንዳልሆነ ተቆጥሮ ከጨረታው ውድድር ውጭ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

**19.** የጨረታ ማስከበሪያ

1. ከምክር አገልግሎት ግዥ በስተቀር ኮርፖሬሽኑ በግልፅ ወይም በውስን ወይም የሁለት ደረጃ ጨረታ የግዥ ዘዴዎችን በሚጠቀምበት ጊዜ በጨረታው ሠነድ ውስጥ ለእያንዳንዱ ግዥ የሚጠየቀውን የጨረታ ማስከበሪያ ዋሰትና በግልፅ መወሰንና ማመልከት አለበት፡፡ሆኖም በተለያዩ ምክንያቶች አስፈላጊነቱን ኮርፖሬሽኑ ካመነበት ለምክር አገልግሎት ግዥም ቢሆን ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና እንዲያሲዙ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ የተወሰኑ አቅራቢዎች በአሉበት ሁኔታ በሚፈጸሙ የውስን ጨረታ ግዥዎች የጨረታ ማስከበሪያ ማግኘት የማይቻል ሲሆን በሚመለከተው የግዥ ጨረታ ኮሚቴ ሲፈቀድ ያለጨረታ ማስከበሪያ መግዛት ይቻላል፡፡
2. ኮርፖሬሽኑ የጠቅላላ ግዥውን ግምታዊ ዋጋ መሠረት በማድረግ ከ0.5% ያላነሰናከ 2% ያልበለጠ የጨረታ ማስከበሪያ የገንዘብ መጠን ወስኖ በጨረታ ጥሪው እና በጨረታ ሰነዱ

ውስጥ መገለፅ ይኖርበታል፡፡ በዚህ መሠረት የሚወሰነው የጨረታ ማስከበሪያ መጠን ከብር 500,000.00 /አምስት መቶ ሺህ ብር/ የበለጠ መሆን የለበትም፡፡

3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ 2 በተገለጸው መሠረት ኮርፖሬሽኑ የጨረታ ማስከበሪያ መጠን ለመወሰን የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡

ሀ. የሚገዛው ዕቃ/አገልግሎት የዋጋ ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ ተለዋዋጭ መሆን፣

ለ. በጨረታው የሚሳተፉ በቂ ተወዳዳሪዎች መኖር፣

ሐ. ተጫራቾች እንዲያቀርቡ የሚጠየቀው ዋስትና በጨረታው እንዳይሳተፉ እንቅፋት እንደማይሆን፣

መ. አሸናፊ ሆኖ የሚመረጠው ተጫራች ውሉን ለመፈረም ፈቃደኛ እንዲሆን የሚገፋፋ፣

ሠ. አሸናፊ ሆኖ የሚመረጠው ተጫራች ውሉን ለመፈረም ፈቃደኛ ባይሆን ዋስትናው በኮርፖሬሽኑ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለማካካስ የሚመጥን መሆኑን፡

4. የሚቀርበው የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና እንደተጫራቹ ምርጫ ከታወቀ ባንክ በሚሰጥ የክፍያ ማዘዣ ቼክ (CPO) ወይም የባንክ ዋስትና ወይም በባንክ የተረጋገጠ ሌተር ኦፍ ክሬዲት ሊሆን ይችላል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ 4 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በግንባታ ሥራ ዘርፍ የተሠማሩ የአገር ውስጥ ሥራ ተቋራጮች ለጨረታ ማስከበሪያ በሁኔታ ላይ የተመሠረተ የመድን ዋስትና ማቅረብ አለበት፡፡

6. አነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋማት እንደ ጨረታ ማስከበሪያ ሆኖ የሚያገለግል የፅሁፍ ዋስትና ካቋቋማቸው እና በበላይነት ከሚቆጣጠራቸው አካል የሚሰጣቸውን የተለየ ዋስትና ማረጋገጫ ካቀረቡ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

7. ከተጫራቾች የሚቀርበው የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ጸንቶ የመቆያ ጊዜ የጨረታው ዋጋ ጸንቶ ከሚቆይበት የመጨረሻ ቀን በኋላ ቢያንስ ለተጨማሪ 28 ቀናት ጸንቶ መቆየት ይኖርበታል፡፡

8. የውጭ አገር ተጫራቾች የሚያቀርቡት ከኢትዮጵያ ውጭ ባሉ ባንኮች የተሠጠ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በአገር ውስጥ ባንኮች ማረጋገጫ ያገኘና በሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ መሆን ይኖርበታል፡

9. ማንኛውም ተጫራች የሚከተሉትን ተግባራት ባለመፈጸሙ ምክንያት ያስያዘው ዋስትና በኮርፖሬሽኑ ሊወረስበት ይችላል፡፡

ሀ. በጨረታ ሠነዱ የተገለጸው የመጫረቻ ሠነድ ማቅረቢያ የመጨረሻ ጊዜ ካለፈ በኂላ ወይም በመጫረቻ ሠነዱ ላይ በተገለጸው የጨረታ ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ተጫራቹ ራሱን ከጨረታው ካገለለ፣

ለ. በጨረታው ውድድር አሸናፊ በመሆኑ ውል እንዲፈርም እና የውል ማስከበሪያ እንዲያሲይዝ ተጠይቆ ውል ለመፈረም እና የተጠየቀውን የውል ማስከበሪያ ለማስያዝ ፈቃደኛ ካልሆነ፣

20. የጨረታ መክፈቻ ጊዜን ስለማራዘም

ኮርፖሬሽኑ በሚከተሉት ምክንያቶች የጨረታ መክፈቻ ጊዜን ሊያራዝም ይችላል፡-

ሀ. በግዥ የሥራ ክፍልም ሆነ በተጫራቾች በኩል ጊዜውን ለማራዘም የሚያስችል አሳማኝ ምክንያት ሲቀርብ፣

ለ. ጨረታውን ለመክፈት የማይቻልበት ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥም በዚህ ጊዜ ኮርፖሬሽኑ ጨረታው የሚከፈትበትን ቀን በግዥ አፅዳቂው ውሳኔ ለሚመለከታቸው ሁሉ በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡

21. የመጫረቻ ሠነድ መረከብ

1. ኮርፖሬሽኑ ተጫራቾች የጫረታ ሰነዶቻቸውን የሚያስገቡበት የጨረታ ሳጥን ማዘጋጀት አለበት፡፡ የጨረታ ሳጥኑም የጨረታ ጥሪው ላይ በተገለፀው ቦታ ጥሪ ከተደረገበት ዕለት ጀምሮ እስከ መጨረሻው የመዝጊያ ሰዓት ድረስ ክፍት ሆኖ መገኘት ይኖርበታል፤
2. የጨረታ ሳጥን ደህንነት የተጠበቀ መሆን ያለበት ሲሆን ጨረታው እስከሚከፈት ድረስ መታሸግ እና ቁልፍ በግዥ የሥራ ክፍል ኃላፊ ተይዞ መቆየት ይኖርበታል፤
3. በአንድ የጨረታ ሳጥን የተለያዩ ዓይነት ጨረታዎች በአንድ ጊዜ መስተናገድ የለባቸውም፤
4. እስከተቻለ ድረስ ማንኛውም የመጫረሻ ሰነድ ለጨረታው በተዘጋጀ ሳጥን ውስጥ ገቢ መደረግ አለበት፡፡ ሆኖም ለግዥው የሚቀርው የመጫረቻ ሰነድ በሳጥኑ ውስጥ ሊገባ የማይችል በሚሆንበት ጊዜ ኮርፖሬሽኑ የጨረታ ጥሪ ከተደረገበት ዕለት ጀምሮ የመጫረቻ ሰነድ የሚረከብ ሠራተኛ በመመደብ በተጫራቾች የሚቀርብን የመጫረቻ ሰነድ መረከብ ይኖርበታል፤
4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ 4 ላይ በተገለፀው መሠረት ኮርፖሬሽኑ ለሚረከበው የመጫራቻ ሰነድ መረከቡን የሚያረጋግጥ የመተማመኛ ሰነድ ሊሰጥ ይገባል፡፡ በዚህ መሠረት ገቢ የተደረጉ የመጫረቻ ሰነዶች ደህንነት መጠበቁን ግዥውን ለመፈፀም የተመደበው ኃላፊ ማረጋገጥ ይኖርበታል፤

5. ከመጫረቻ ሰነድ ማስረከቢያ የመጨረሻ ቀንና ሰዓት በኋላ ዘግይቶ የደረሰ የመጫረቻ ሰነድ እሽጉ ሳይከፈት ለተጫራቾቹ ወዲያውኑ ተመላሽ መደረግ አለበት፡፡

22. የጨረታ አከፋፈት

1. ጨረታ የሚከፈተው በጨረታው ጥሪ ወይም ማሻሻያ ተደርጎ ከሆነ በማሻሻያ ሰነዱ ላይ በግልፅ በተቀመጠው ቀን፣ ሰዓትና ቦታ ይሆናል፡፡ ጨረታው ሲከፈትም፡-

ሀ. ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይሆናል፡፡ ሆኖም ተጫራቾች በራሳቸው ምርጫ ጨረታው በሚከፈትበት ጊዜ ሳይገኙ ቢቀሩ የጨረታው መከፈት አይስተጓጎልም፣

ለ. የጨረታ አከፋፈት ሂደቱን እስካላወከና የቦታ ጥበት እስከሌለ ድረስ በጨረታው አከፋፈት ሂደት ላይ መገኘት የሚፈልግ ማንኛውም የመገናኛ ብዙሐን፣ ድርጅት ወኪል ወይም ሌላ ፍላጎት ያለው ሰው በታዛቢነት መገኘት ይችላል፤

ሐ. በጨረታው መክፈቻ ጊዜ ከሶስት ያላነሱ የግዥ ሥራ ክፍል ባለሙያዎች ፣ የውስጥ ኦዲት እና የተጠቃሚው የስራ ክፍል አባላት መገኘት አለባቸው፤

መ. በጨረታ አከፋፈት ሥነ-ሥርዓት ላይ ከተገኙት የግዥ ሥራ ክፍል ባለሙያዎች በመጫረቻ ሰነዶች ዋና ዋና ክፍሎች ላይ ይፈራረማሉ፡

2. በአንድ ፖስታ እንዲቀርብ የተጠየቀ ጨረታ ከሆነ ኮርፖሬሽኑ እያንዳንዱ ዕጩ ተወዳዳሪው ያቀረበውን የመጫረቻ ሰነድ በመክፈት የተጫራቹን ስም፣ ለውድድር ያቀረበውን ዋጋ፣ የዋጋ ቅናሽ መጠንና ሁኔታውን፣ የጨረታ ማስከበሪያ ዓይነትን እና መጠንን እንዲሁም ማናቸውንም ዕጩ ተወዳዳሪዎች አንፃራዊ ደረጃቸውን ለማወቅ ይረዳቸዋል ተብለው የሚታሰቡ ሌሎች ሁኔታዎችን በንባብ ማሰማት አለበት፡፡

3. ጨረታው በሁለት ፖስታዎች እንዲቀርብ የተጠየቀ ከሆነ፤

ሀ. በጨረታው መክፈቻ ሥነ-ስርዓት የቴክኒክ ዶክመንቱን የያዘው ፖስታ እንዲከፈት ተደርጎ የተጫራቹን ማንነት ጨምሮ በወቅቱ ሊገለፁ የሚችሉ ነጥቦችን በንባብ ማሰማት አለበት፤

ለ. የሁሉም ዕጩ ተወዳዳሪዎች የዋጋ ኤንቬሎኘ ሳይከፈት አንድ ላይ በሌላ ኤንቨሎኘ ታሽጎ እና በእሽጉ ላይ የጨረታው መለያ ቁጥር ተጽፎበት፣ የዋጋ ኤንቬሎፖች መሆናቸው ተገልፆ እና ጨረታውን የከፈቱት የኮርፖሬሽኑ ባልደረቦች ተፈራርመውበት ሁለተኛው ዙር የጨረታ መክፈቻ ሥነ-ስርዓት እስከሚካሄድ

ድረስ የታሸገው ፖስታ በጨረታ ሳጥን ውስጥ ተመልሶ በማሸግ በግዥ ሥራ ክፍል ወይም ኃላፊነት በተሰጠው አካል በጥንቃቄ ተይዞ መቆየት ይኖርበታል፤

ሐ. የቴክኒክ ግምገማ ተደረጎ የተገኘው ውጤት ሥልጣን በተሰጠው አካል ከጸደቀ በኋላ ውጤቱ በጨረታው ለተሳተፉ ተጫራቾች በሙሉ በተመሳሳይ ጊዜ በጽሑፍመገለጽ ይኖርበታል፤

መ. የቴክኒክ ግምገማውን ላላለፉት ጫራቾች የሚፃፈው ደብዳቤ በጨረታው የተሸነፉበትን ምክንያት የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡ ተጫራቾቹም አቤቱታ ካላቸው አቤቱታቸውን ማቅረብ ይችላሉ፤

ሠ. የቴክኒክ ውጤታቸው ተቀባይነት ላገኙ ተጫራቾች የሚጻፈው ደብደቤ የዋጋ ፖስታ የሚከፈትበትን ዕለት፣ ሰዓትና ቦታ የሚገልጽ መሆን ይኖርበታል፡፡ ደብዳቤውም በእኩል ጊዜ እንዲደርሳቸው መደረግ እና ሁሉም ፈቃደኛ ተጫራቾች በጨረታው የዋጋ ኤንቬሎፐ መክፈቻ ሥነ-ሥርዓት ላይ እንዲገኙ የሚያስችላቸው በቂ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ሆኖም በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ አቤቱታ የቀረበ ከሆነ አቤቱታው ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ የዋጋ ኤንቬሎፑ መከፈት የለበትም፤

ረ. በዚሁ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሠ" መሠረት የሚደረግላቸውን ጥሪ ተከትለው የቴክኒክ ግምገማውን ያለፉ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሚገኙበት የዋጋ መወዳደሪያቸውን የያዘው ኤንቬሎኘ በግልጽ እንዲከፈት ይደርጋል፤

ሰ. ለዋጋ ውድድር ያለፉ ተወዳዳሪዎችን ኤንቬሎኘ በዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል ተራ "ረ" ላይ በተገለጸው መሠረት በመክፈት የተጫራቹን ሥም፣ ለግዥው ያቀረበውን ዋጋ፣ የዋጋ ቅናሽ ካለው መጠኑን እና ሁኔታውን፣ እንዲሁም ከዋጋ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ተጫራቾች እንዲያውቁ መደረግ አለበት፣

ሸ. የቴክኒክ ግምገማው ውጤት እንደታወቀ በቴክኒክ ውድድሩ ተቀባይነት ያላገኙ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና እንዲሁም የዋጋ መወዳዳሪያቸውን የያዘው ኤንቬሎፕ ሳይከፈት ተመላሽ ይደረግላቸዋል፡፡ ሆኖም በዚህ አንቀጽ ንዑስ 3 ፊደል ተራ "መ" መሠረት በቴክኒክ ግምገማው ውጤት ላይ አቤቱታ የቀረበ ከሆነ በአቤቱታው ላይ የሚሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ እስኪታወቅ

ድረስ በቴክኒክ የወደቁት ተጫራቾች የዋጋ ማወዳደሪያ ኤንቬሎፖችም ሆኑ ያስያዟቸው የጨረታ ዋስትናዎች ተመላሽ አይደረጉም፡፡

ቀ. የኮርፖሬሽኑ የግዥ ሥራ ክፍል የጨረታ አከፋፈት ሂደት ቃለ-ጉባኤ መያዝ አለበት፡፡ ይህም ቃለ-ጉባኤ የተጫራቾቹን ስም፣ ያቀረቡትን ዋጋ እና በጨረታው አከፋፈት ሂደት ላይ የተነሱ ሌሎችንም አስፈላጊ ነጥቦች የሚይዝ ይሆናል፡፡ቃለ-ጉባኤው እና ተጫራቾች ያቀረቡት ዋናው የመጫረቻ ሰነድ በጨረታ አከፋፈት ሂደቱ ላይ በተገኙት በግዥ ሥራ ክፍል አባላት ይፈረማል፡፡ ጨረታው በተከፈተበት ጊዜ የተገኙ ተጫራቾች መገኘታቸውን በሚያረጋግጠው ሰነድ ላይ እንዲፈርሙ ይደረጋል፡

4. ማንኛውም በጨረታ መክፈቻ ሥርዓት ላይ ያልተከፈተና ለተጫራቾች ያልተነበበ የመጫረቻ ሰነድ ለቀጣይ ውድድር ሊያገለግል አይችልም፡

5. ማንኛውም ተጫራቾች በጨረታ መክፈቻ ሂደት ወቅት ከጨረታው ውጭ ሊደረግ አይገባም፡፡

23. ጨረታን መገምገምና ማወዳደር

1. የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ

ኮርፖሬሽኑ ጨረታውን የተሟላ ነው ብሎ ለቀጣዩ ዝርዝር የግምገማ ሂደት ሊያሳልፈው የሚችለው በተጫራቹ የቀረበው የመጫረቻ ሠነድ በመክፈቻ ሥነ-ሥርዓቱ ወቅት የተከፈተ እና በጨረታ ሠነዱ ላይ የተዘረዘሩትን ቅድመ ሁኔታዎች ተፈላጊ ነጥቦች የሚያሟላ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡ ይሆንና ኮርፖሬሽኑ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የማያሟሉ ተጫራቾችን ወደ ዝርዝር ግምገማ ማሳለፍ የለበትም፡-

ሀ. በጨረታው የተወዳደረው አቅራቢ ኮርፖሬሽኑ የሚፈልገውን አነስተኛውን የጥራት መመዘኛ እና ሌሎች መሰረታዊ መስፈርቶችን ያላሟላ በመሆኑ ብቃት የሌለው ሆኖ ሲገኝ፣

ለ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ 3 መሠረት የተደረገው የሂሳብ ስህተት ማስተካከያ የማይቀበል አቅራቢ ሲሆን፣

ሐ. ተጫራቹ የተጠየቀውን የጨረታ ማስከበሪያ ያላስያዝ ወይም የውል ማስከበሪያ ለማስያዝ ፈቃደኛ ያልሆነ ከሆነ ፣

መ. በመሥሪያ ቤቱ የተጠየቁትን አስፈላጊ ማስረጃዎች ያላቀረበ ከሆነ፣

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ 1 ላይ የተመለከተው ቢኖርም ኮርፖሬሽኑ በምርመራ ወቅት የተገኙ የሒሳብ ስህተቶችን ማረም ይችላል፡፡ እንዲዚህ ያሉትን የማስተካከያ እርምጃዎች ኮርፖሬሽኑ በአፋጣኝ ለሚመለከተው ተጫራቹ በፅሑፍ ማስታወቅ አለበት፡፡ ተጫራቹ በሒሳብ ማስተካከያው የማይስማማ ከሆነ ከጨረታው እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

3. በጨረታ ሰነዱ ከተዘረዘሩት ባህርይዎች፣ የውል ሁኔታዎች እና ከሌሎች ተፈላጊ ነጥቦች ጋር መሠረታዊ የሆነ ለውጥ እና ልዩነት እስከሌለው ድረስ ወይም የጨረታው ቁም ነገር ሳይለወጥ ኮርፖሬሽኑ ጨረታውን እንደተሟላ አድርጎ ሊቀበል ይችላል፡፡ ሆኖም ማናቸውም ልዩነት በገንዘብ ተገልፆ በጨረታው ግምገማ እና ውድድር ወቅት ከግምት ውስጥ እንዲገባ መደረግ አለበት፡፡

24. ዕጩ ተወዳዳሪዎችን ከጨረታ ውጭ ስለማድረግ

1. ኮርፖሬሽኑ በሚያወጣቸው የግዥ ጨረታዎች ዕጩ ተወዳደሪዎች ከሚከተሉት ሁኔታዎች በአንዱ ምክንያት ከጨረታ ውድድር ውጭ ሊደረጉ ይችላሉ፤

ሀ. ቀደም ሲል በመንግስት በወጡ ጨረታዎች የገባውን ግዴታ ሳያስከብር በመቅረቱ በኤጀንሲው ጥቁር መዝገብ ላይ የተመዘገበ ከሆነ፤

ለ. የተለየ አስተያየት ለማግኘት ወይም ጨረታውን ለማሸነፍ መደለያ ለማናቸውም የኮርፖሬሽኑ ባለሥልጣን ወይም ሠራተኛ መስጠቱ ወይም የመስጠት ሃሣብ ማቅረቡ በአሳማኝ ሁኔታ ሲረጋገጥ፤

ሐ. ተጫራቹ በጨረታው ሠነድ ላይ የማጭበርበር ተግባር መፈጸሙ፣ወይም ከሌላ ዕጩ ተወዳዳሪ ጋር መመሳጠሩ በአሳማኝ ሁኔታ ሲረጋገጥ፣

መ. የኢትዬጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የንግድ ግንኙነቶች ላለማድረግ ክልከላ ከጣለበት አገር የሚመጣ ዕቃና አገልግሎት ከሆነ፤

ሠ. በተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ጥበቃ ምክር ቤት ውሳኔ ከዚያ አገር ዕቃዎችንና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ማስመጣት ወይም ለዚያ አገር ሰዎች ወይም ድርጅቶች ማንኛውንም ክፍያ መፈፀም የተከለከለ ከሆነ፤

ረ. የኮርፖሬሽኑን የግዥ እና ንብረት አስተዳደር መመሪያ የሚጥሱ ድርጊቶችን መፈፀሙ የተረጋገጠ እንደሆነ፤

ሰ. የምክር አገልግሎት ግዥ ላይ አንድ ባለሙያ በተመሳሳይ ጨረታ ላይ ለሚሳተፉ ከአንድ በላይ ለሚሆኑ ከተለያዩ ተጫራቾች ጋር ለመስራት ተስማምቶ ሲቪ ማስገባቱ በግምገማ ወቅት ቢገኝ በተጫራቾቹ መካከል የሚደረገውን ውድድር የሚጎዳ በመሆኑ ከአሸናፊው ተጫራች የሰው ሀይል ዝርዝር እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

25. ዝርዝር ግምገማ ማድረግና አሸናፊውን መለየት

1. ኮርፖሬሽኑ አሸናፊውን ተጫራች ለመምረጥ በመጀመሪያ ደረጃ የተቀበላቸውን የመጫረቻ ሠነዶች እና በጨረታ ሠነዱ ላይ የተገለፁትን መስፈርቶች ተጠቅሞ ዝርዝር ግምገማ ማድረግ አለበት፡፡ በጨረታ ሠነዱ ውስጥ ከተገለጹት የኮርፖሬሽኑ መስፈርት ወጭ ግምገማ ማድረግ አይፈቀድም፡፡ በጨረታ ሰነዱ በሚገለጸው መሠረት አሸናፊውን ተጫራች ለመመረጥ ከሚከተሉት የግምገማ ስርዓቶች በአንዱ መጠቀም ይኖርበታል፤

   ሀ. በአንድ ኤንቬሎፕ የቀረበን ጨረታ የቴክኒክ ግምገማ መመዘኛዎችን ማሟላቱ የተረጋገጠ እና አነስተኛ ዋጋ ያቀረበን ተጫራች፣

   ለ. በሁለት ኤንቬሎፖች የቀረበን ጨረታ የግዥውን የጠቀሜታ እሴት የሚወስኑ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ በሚካሄድ የቴክኒክና የፋይናንስ አጠቃላይ ግምገማ ድምር ውጤት ከፍተኛ ነጥብ ያገኘውን ተጫራች በመምረጥ ይሆናል፤

   ሐ. ኮርፖሬሽኑ ውስብስብ ላልሆኑ ዕቃዎችና የግንባታ ሥራ ግዥ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" የተገለፀውን የግምገማ ዘዴ መጠቀም ይኖርበታል፡፡ ሆኖም መለስተኛ ላልሆኑ የግንባታ ሥራዎች፣ ለቢሮ መገልገያ መሣሪያዎች፣ ለኮንስትራክሽን መሣሪያዎችና ተሽከርካሪዎች ግዥዎች በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ለ" የተገለፀውን የግምገማ ዘዴ መጠቀም ይችላል፡፡

2 ዝርዝር ግምገማ በሚደረግበት ወቅት ተጫራቾች የሰጡት በሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ የዋጋ ቅናሽ ታሳቢ ይደረጋል፤

3. እንደአስፈላጊነቱ የተመረጠው ተጫራች ህጋዊነት፣ የፋይናንስና የቴክኒክ አቋም በመጫረቻ ሰነዱ ላይ በተቀመጠው መሠረት መሆኑ በድህረ ግምገማ ሊረጋገጥ ይችላል፤

4. ግዥው በዓለም አቀፍ የጨረታ ዘዴ የሚፈጸም ሆኖ ለግምገማ ዓላማ ሲባል በተለየ ሁኔታ እንዲቀርብ በጨረታ ሠነዱ ካልተገለጸ በስተቀር በተጫራቾች የሚቀርበው ዋጋና የሚካሄደው የጨረታ ግምገማ ታክስን ማካተት ይኖርበታል፤

5. ዕቃዎች፣ የግንባታ ሥራዎች፣ የምክርና ሌሎች አገልግሎቶች በጥራትና በዋጋ ተመሣሣይ ሆኖ ተጫራቾች በግምገማ እኩል ነጥብ ሲያገኙ ለአገር ውስጥ ምርቶች፣ አገልግሎቶች ወይም ኩባንያዎች ቅድሚያ ይሰጣል፤

6. በዚህ አንቀፅ ንዑስ 5 ላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ እኩል ነጥብ ያመጡ ወይም እኩል ተመራጭ የሆኑ ተጫራቾች በሚኖሩበት ጊዜ አሸናፊውን ለመለየት ኮርፖሬሽኑ እኩል የወጡት ተጫራቾች በተወሰኑ መስፈርቶች ላይ የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሐሳባቸውን እንዲሰጡ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይህንንም ተፈፃሚ ለማድረግ፡-

   ሀ. እኩል የሚወጡ ተጫራቾች የሚወዳደሩባቸው መስፈርቶች ቁጥር ከሶስት ያልበለጠ እና በአኃዝ ሊገለፅ የሚችል መሆን ይኖርበታል፤

   ለ. መስፈርቶቹ በጨረታ ሠነዱ ላይ በተለይ በጨረታ ዝርዝር መግለጫው ላይ መገለጽ ይኖርባቸዋል፤

   ሐ. እኩል የወጡት ተጫራቾች እኩል መሆናቸው ሲረጋገጥ ይኸው ተገልጾላቸው መጀመሪያ በጨረታ ሰነዱ ላይ በተገለፁት መስፈርቶች መሠረት የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሀሳባቸውን እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ፤

   መ. እኩል የወጡት ተጫራቾች ያቀረቡት የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሀሣብ እስከተቻለ ድረስ እኩል የወጡት ተጫራቾች በተገኙበት ተከፍቶ የሰጡት የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሃሣብ እንዲነብብላቸው ያደርጋል፤

   ሠ. እኩል የሆኑት ተጫራቾች ያቀረቡት የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሃሣብ ተገምግሞ የተሻለ ሐሳብ ያቀረበው ተጫራች የጨረታው አሸናፊ ተደርጎ ይመረጣል፤

   ረ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ 6 ፊደል ተራ /ሠ/ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ እኩል የወጡት ተጫራቾች የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሐሳብ ባለማቅረባቸው ወይም ባቀረቡት የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሐሳብ መሠረት በተደረገ ግምገማ በድጋሚ እኩል ቢሆኑ እስከተቻለ ድረስ እኩል የሆኑት ተጫራቾች በተገኙበት አሸናፊው ተጫራች በእጣ እንዲለይ ይደረጋል፡፡

7. ኮርፖሬሽኑ የጨረታውን አሸናፊ በሚመርጥበት ጊዜ መለኪያው ተለይቶ የሚታወቅ እስከሆነ ድረስ በእያንዳንዱ ዕቃ ወይም አገልግሎት መለኪያ የተሰጠውን የነጠላ ዋጋ ወይም ሌሎች የውል ቃሎች እና ሁኔታዎችን  ሳይለውጥ እንደ አስፈላጊነቱ የዕቃው ወይም አገልግሎቱን ብዛት /መጠን/እስከ 25% /ሃያ አምስት በመቶ/ድረስ ሊቀነስ ወይም ሊጨመር የሚችል ስለመሆኑ በጨረታ ሠነዱ ላይ መገለጽ ይኖርበታል፡፡

8. ኮርፖሬሽኑ የማናቸውም ጨረታ ግምገማ በተጫራቾች የተሰጠው የጨረታው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ የመጨረሻ ቀን ከማለፉ በፊት ግምገማውን በማጠናቀቅ ውጤቱን ለተጫራቾች መግለጽ አለበት፡፡ ሆኖም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ግምገማውን በጊዜ ማጠናቀቅ ካልቻለ ተጫራቾች ዋጋው ፀንቶ የሚቆይበትን የጊዜ ገደብ እንዲያሻሽሉ በዚህ አንቀፅ ንዑስ 4 መሠረት መጠየቅ ይገባዋል፡፡

9. ኮርፖሬሽኑ ሁለት ጊዚ ጨረታ አውጥቶ የቀረበው አንድ ተጫራች ያቀረው የመወዳደሪያ ሃሣብ አጥጋቢ እና ዋጋውም ተወዳዳሪ የገበያ ዋጋ መሆኑን እንዲሁም የሌሎች ተወዳዳሪዎችን ተሳትፎ የሚገድቡ ምክንያቶች በጨረታ ሰነድ ላይ ያለመኖራቸውን ካረጋገጠ ድጋሚ ጨረታ ማውጣት ሳያስፈልግ የቀረበውን አንድ ተጫራች አሸናፊ ሊያደርግ ይችላል፡፡ አጥጋቢ ዋጋ ማለት ተወዳዳሪው ያቀረበው የመጫረቻ ዋጋ ከገበያ ዋጋ ላይ ለጨረታው ማስኬጃ ሊወጣ የሚችል ተጨማሪ እስከ 10% ወጪን ሊጨምር ይችላል፡፡

10. ግምገማውን ለማከናወን እና ለማወዳደር የሚረዳ ሆኖ ሲገኝ ኮርፖሬሽኑ አቅራቢዎች ባቀረቡት የጨረታ ሠነድ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጡት ሊጠየቅ ይችላል፡፡

11. በዚህ አንቀጽ ንዑስ 11 የተመለከተው ቢኖርም ኮርፖሬሽኑ በግምገማው ወቅት የነጠላ ዋጋውን ሳይነካ የሂሣብ ስህተቶችን ማረም ይችላል፡፡ እንደዚህ ያሉትን የማስተካከያ እርምጃዎች ኮርፖሬሽኑ የጨረታ ሰነዱን ላቀረበው ተጫራች በአፋጣኝ ማሳወቅ አለበት፡፡

12. በጨረታው ሠነድ ከተዘረዘሩት ባህሪዎች፣ የውል ቃሎች፣ ሁኔታዎች እና ሌሎችም ተፈላጊ ነጥቦች ጋር በተወሰነ ደረጃ ልዩነት ቢኖረውም መሠረታዊ የሆነ ለውጥ እና ልዩነት እስከሌለው ድረስ ወይም የጨረታው ቁም ነገር ሳይለወጥ ሊታረም የሚችል ጥቃቅን ግድፈት ቢኖረውም በሚመለከተው የጨረታ አፅዳቂ ኮሚቴ ከታመነበት ኮርፖሬሽኑ ጨረታውን እንደተሟላ አድርጎ ሊቀበል ይችላል፡፡

13. ማናቸውም ልዩነት እስከተቻለ ድረስ በአሃዝ ተገልጾ በጨረታው ግምገማ እና ውደድር ወቅት እንዲታሰብ መደረግ አለበት፡፡

14. ኮርፖሬሽኑ የጨረታ ግምገማን ለማካሄድ በኮርፖሬሽኑ ውስጥም ይሁን ከኮርፖሬሽኑ ውጭ ያሉ ባለሙያዎችን መጠቀም የሚችል ሲሆን ገምጋሚ ቡድኑ በሚቋቋምበት ወቅት ግን ባለሙያዎቹ በፍላጎት መግለጫ ዝርዝር ዝግጅት ላይ ያልተሳተፉ እንዲሁም በግዥው ርክክብ ወቅት በሚካሄድ ምርመራ ላይ የማይሳተፉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

26. ጨረታን ስለመሰረዝና ድጋሚ ስለማውጣት

1. በሚከተሉት መሠረታዊ ምክንያቶች ኮርፖሬሽኑ ያወጣውን ጨረታ በመሠረዝ ድጋሚ ጨረታ ሊያወጣ ይችላል፡-

    ሀ. ኮርፖሬሽኑ በጨረታ ሰነዱ ላይ የሚፈለገውን መሠረታዊ ጉዳይ ያላካተተ መሆኑን ሲያውቅ፣

    ለ. በአሸናፊው ተጫራች የቀረበው ዋጋ ጨረታው ከመውጣቱ በፊት ከተገመተው ጋር ሲነፃፀር በከፍተኛ ልዩነት የሚበልጥ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ባለመሆኑ አዲስ ጨረታ ማውጣት የሚሻል መሆኑ ሲታመንበት፣

    ሐ. የቀረበው አንድ ተጫራች ብቻ ሲሆንና ይህን ተጫራች በብቸኝነት እንዲቀርብ ያስቻለው በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩትን ሥርዓቶች ያልጠበቀ አሠራር /ሁኔታ/ በመኖሩ ምክንያት መሆኑ ሲረጋገጥ ወይም በጨረታ ሠነዱ ላይ ለውጥ ማድረግ በርካታ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን ማግኘት የሚያስችል መሆኑ ሲታመንበት፣

    መ. ተጫራቾች በመመሳጠር አንዱ ተጫራች እንዲያሸንፍ ለማድረግ ሲሞክሩና ኮርፖሬሽኑ ሲደርስበት፤

    ሠ. ሁሉም ተጫራቾች ያቀረቡት ሰነድ ኮርፖሬሽኑ ባዘጋጀው ዝርዝር የጨረታ መመሪያ ወይም የቴክኒክ ፍላጎት (Technical Specification) ጋር ፈፅሞ የማይጣጣም ሆኖ ከተገኘ፤

    ረ. ተጫራቾች የጨረታ ሕግና ደንብን ያልተከተለ አካሄድ ያሳዩ ወይም ተገቢ ያልሆነ ግንኙነት የፈጠሩ መሆኑ ከተረጋገጠ፤

2. ሌሎች አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚደረግ የጨረታ ግምገማ እና ውድድር ከዚህ በታች እንደተገለፀው በዋጋ ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1 | የቴክኒክ ባህርያት | የሚሰጠው ክብደት ከ100% ሆኖ ወደ ፋይናንስ ግምገማ ለማለፍ የማንኛውም ተጫራች የቴክኒክ ግምገማ ውጤት 70% እና ከዚያ በላይ መሆን አለበት |
| 2 | የመወዳደሪያ ዋጋ | በቴክኒክ ግምገማ ውጤት 70% እና ከዚያ በላይ ያመጣ እና ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበ ተጫራች የጨረታው አሸናፊ ይሆናል |

27. ልዩ አስተያየት

1. ጥራቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በዋጋ ማቅረቢያና ከአንድ አቅራቢ ከሚፈጸም ግዥ በስተቀር በማናቸውም ግዥ ላይ በአዋጁ መሰረት በኢትዮጵያ ውስጥ ለተመረቱ ዕቃዎች፣ ለተቋቋሙ አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት፣ በኢትዮጵያ ኩባንያዎች ለሚከናወኑ የግንባታ ዘርፍ እና የምክር አገልግሎት ሥራዎች ልዩ አስተያየት ይደረጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ 1 መሠረት የሚደረገው ልዩ አስተያየት በቴክኒክና ግምገማ ላይ በሚደረግ ውድድር ወቅት በሚከተለው መሠረት ተፈፃሚ መደረግ አለበት፡፡ ይኸውም፡-

   ሀ. ለመድኃኒት እና የህክምና መሣሪያዎች ግዥ 25% /ሀያ አምስት በመቶ/፣

   ለ. ለሌሎች ዕቃዎች ግዥ 15% /አስራ አምስት በመቶ/፣ እና

   ሐ. ለግንባታ ሥራና ለምክር አገልግሎት ግዥዎች 7.5% /ሰባት ነጥብ አምስት በመቶ/፡

3. በዚህ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" እና "ለ" መሠረት የሚደረገው ልዩ አስተያየት መድኃኒቱን ወይም የሕክምና መሣሪያውን ወይም ዕቃውን ለማምረት ከወጣው ጠቅላላ ወጪ 35%/ ሠላሣ አምስት በመቶ/ እና ከዚህ በላይ በኢትዩጵያ ውስጥ የታከለ እሴት መሆኑን የሚያስረዳ በተመሰከረለት ኦዲተር የተረጋገጠ ማስረጃ ሲቀርብ ይሆናል፡፡ ለዚህ ንዑስ አንቀጽ አፈፃፀም የታከለ ዋጋ ማለት፣ ከጠቅላላ ወጪ ላይ ከውጭ አገር ለሚመጡ ጥሬ ዕቃዎች እና ለሎች አቅርቦቶች እንዲሁም ከውጭ አገር ለተገኘ አገልግሎት የተደረገ ወጪ ተቀንሶ የሚቀረው ወጪ ሲሆን፣ በምርት ላይ የሚከፈሉ ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶችን አይጨምርም፡፡
4. ማናቸውም የግንባታ ወይም የምክር አገልግሎት ሥራ በዚህ አንቀጽ ንዑስ 2 ፊደል ተራ "ሐ" መሠረት የተፈቀደው ልዩ አስተያየት ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች በሙሉ ሲሟሉ ይሆናል፡፡

   ሀ. ኩባንያው በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተቋቋመ እና ዋና መ/ቤቱ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፣

   ለ. ከኩባንያው አክስዮን ወይም የካፒታል ድርሻ ከ50% /ሃምሣ በመቶ/ በላይ በኢትዮጵያውያን የተያዘ ከሆነ፤

   ሐ. ከኩባንያው ቁልፍ ሠራተኞች መካከል ቢያንስ 50% /ሃምሣ በመቶ/ ኢትዮጵያውያን ከሆኑ፤

መ. ከኩባንያው ቁልፍ ሠራተኞች መካከል ቢያንስ 50% /ሃምሣ በመቶ / በላይ ኢትዮጵያውያን ከሆኑ፡

5. በአምራች አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት አዋጅ መሠረት ተቋማት፡-

ሀ. ከአገር ውስጥ አቅራቢዎች ጋር በሚያደርጉት በቴክኒክ ውድድር 3% /ሶስት በመቶ/ ልዩ አስተያየት ይደረግላቸዋል፡፡

ለ. ግዥው በዓለም አቀፍ የግዥ ዘዴ የሚፈጸም ሲሆን በዚህ አንቀጽ ንዑስ 2 ላይ የተፈቀደው ልዩ አስተያየት ብቻ ተፈፃሚ ይደረጋል፣

ሐ. በጨረታ ማስከበሪያ፣ በውል ማስከበሪያ እና በቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ምትክ ተቋማቱን ካደራጃቸው አካል የሚሰጥ የዋስትና ደብዳቤ ተቀባይነት ይኖረዋል፣

መ. ለጨረታው የተዘጋጀው የጨረታ ሠነድ በአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋምነት የተቋቋመበትን የሕጋዊነት ማስረጃ በማሳየት ያለ ክፍያ በነፃ ይሰጣቸዋል፡፡

28. **የተጫራቹ ድህረ መረጣ የብቃት ማረጋገጫ** (Post Qualification Evaluation)

1. ጨረታ ከተከፈተ በኂላ የመወዳደሪያ ሃሣብን ለመገምገም በሚያስችሉ ነጥቦች ላይ ማብራሪያ ከመጠየቅና ውል ከመፈፀም ጋር ተያይዞ ድርድሮችን ለማድረግ ካልሆነ በስተቀር በግዥ ሂደት በማናቸውም ደረጃ ከተጫራቾች ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ማድረግ አይቻልም፡
2. ኮርፖሬሽኑ በጨረታው የተመረጠውን ተጫራች ማሸነፉን የሚገልፅ ደብዳቤ ከመስጠቱ በፊት እንደ አስፈላጊነቱ አሸናፊው ተጫራች ውሉን በአጥጋቢ ሁኔታ ለመፈፀም ብቃት እንዳለ የሠራቸውን ሥራዎች፣ የአቅራቢውን አደረጃጀት ወዘተ በመመልከት ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
3. የአሸናፊው ተጫራች የድህረ-መረጣ ብቃት ማረጋገጫ ውጤት ብቁ ሆኖ ካልተገኘ ኮርፖሬሽኑ የተጫራቾችን የጨረታ ማስከበሪያ በመውሰድ በሁለተኛ ደረጃ ወደ ተገመገመው ተጫራች ውጤቱን በማስተላለፍ ተመሳሳይ የሆነ የድህረ-መረጣ ብቃት ማረጋገጫ ግምገማ ያደርጋል፡፡

29. ከተጫራቾች ጋር ስለሚደረግ ውይይት

1. በግዥ ሂደት በማናቸውም ደረጃ ከተጫራቾች ጋር ውይይት ሊደረግ የሚችለው የተለየ ሁኔታ ሲያጋጥም ብቻ ይሆናል፡፡ በኮርፖሬሽኑ እና በአቅራቢዎች መካከል የሚደረጉ ውይይቶች በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ይሆናሉ፡፡ እነዚህም፡-

ሀ. በጥቃቅን ጉዳዮች ላይ ለመወያየት፣

ለ. የሁለት ደረጃ ጨረታ በሚሆንበት ጊዜ ጨረታው በሚያካትታቸው የግዥ ዓይነቶች ላይ ድርድር ለማድረግ፣

ሐ. ግዥ ከአንድ አቅራቢ በሚፈፀም ጊዜ፣

መ. ከተወዳደሩት ተጫራቾች መካከል የቴክኒክ ግምገማን ወይም የድህረ-መረጣ ብቃት ማረጋገጫን አልፎ ለፋይናንሺያል ውድድር ያለፈው አንድ ተጫራች ብቻ ሲሆን፣

ሠ. በጨረታ ውድድሩ የቀረበው አንድ ተጫራች ብቻ ሲሆን፣

ረ. የማዕቀፍ ውል ለመፈፀም ሲፈለ

30. የጨረታን ውጤት ማጽደቅ

1. የጨረታ ግምገማውን የሚያከናውነው የቴክኒክ ኮሚቴ በተጨራቾች የተሠጠው የጨረታ ዋጋ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ግምገማውን በማጠናቀቅ ውጤቱን ከአስተያየት ጋር ግዥውን ለማጽደቅ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ለውሳኔ ማቅረብ አለበት፡፡

2. ከግምገማው ውጤት ጋር የሚከተሉት ሰነዶች ተያይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

ሀ. የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ቃለ-ጉባኤ፣

ለ. የዋጋ ንባብ ዝርዝር፣

ሐ. ከተጠቃሚዎች የቀረቡ የዕቃዎች/አገልግሎቶች ጥያቄ ዝርዝር

መ. የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ ሪፖርት፣

ሠ. በግዥ ጠያቂ ስራ ክፍሎች የተዘጋጀ የጨረታ ግምገማ መስፈርት ፣

ረ. የቴክኒክ ኮሚቴ ሪፖርት

ሰ. ተጫራቾች ማብራሪያ የተጠየቁበትና ምላሽ የሰጡበት ደብዳቤዎች፣

ሸ. ሙሉ የጨረታ ሰነድና የጨረታ ማስታወቂያ፣

3. ግዥውን እንዲያጸድቅ ሥልጣን የተሰጠው አካል ግዥው የኮርፖሬሽኑን ግዥ አፈፃፀም ሥርዓት የተከተለና የጨረታ ግምገማው በጨረታ ሰነዱ በተገለፀው መስፈርት መሠረት መሆኑን በማረጋገጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ውሣኔውም ከሚከተሉት አንዱ ሊሆን ይችላል፡፡

ሀ. የግምገማ ሪፖርቱን ሙሉ በሙሉ በመቀበል ቀጣይ አፈፃፀሞችን እንዲያከናውኑ መፍቀድ፣

ለ. የግምገማ ሪፖርቱ የኮርፖሬሽኑን ግዥ አፈፃፀም ሥርዓት የተከተለና የጨረታ ግምገማው በጨረታ ሰነዱ በተገለፀው መስፈርት መሠረት ካልተሰራ እርማቱን

ገልፆ የማስተካከያ ስራ እንዲሰራ ለቴክኒክ ኮሚቴው ወይም ለግዥ አፅዳቂው ኮሚቴ መመለስ፣

ሐ. ሪፖርቱን ባለመቀበል ግምገማው እንደገና እንዲከናወን ወይም ጨረታው እንዲሰረዝ ማድረግ፣

መ. ግዥውን እንዲያፀድቅ ሥልጣን የተሰጠው አካል ግምገማው እንደገና እንዲከናወንም ሆነ ጨረታው እንዲሰረዝ ሲወስን ምክንያቶቹን በጽሁፍ ማስቀመጥ አለበት፡

4. ግዥውን የሚያጸድቀው አካል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በቀረበው የግምገማ ሪፖርት ላይ ግምገማውን የሰራው አካል ማብራሪያ እንዲሰጠው ሊያደርግ ይችላል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ 3 ፊደል ተራ "መ" ላይ በተገለፀው መሠረት በግዥው ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጠው አካል የቀረበውን የግምገማ የውሳኔ ሃሣብ ያልተቀበለ ከሆነ ምክንያቱን በመግለፅ ከዚህ በፊት ግምገማውን ላከናወነው የቴክኒክ ወይም የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ እንዲመለስ የሚያደርግ ሲሆን የቴክኒክ ወይም የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴም በተሰጠው አቅጣጫ መሠረት ግምገማውን እንደገና አከናውኖ የተስተካከለውን ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ 5 ላይ የተመለከተው ቢኖርም የቴክኒክ ኮሚቴው የግዥ አፅዳቂው ኮሚቴ በሰጠው አቅጣጫ ወይም በግምገማ ውጤቱ ላይ የማይስማማ ከሆነ በግምገማ ሪፖርቱ ላይ ያልተስማማበት ተገልፆ የግዥ አፅዳቂው ኮሚቴ በሰጠው ውሳኔ መሠረት እንዲፈፀም ይደረጋል፡፡

31. የጨረታውን አሸናፊ ማሳወቅ

1. ኮርፖሬሽኑ የጨረታውን ውጤት በጨረታው ተሳታፊ ለሆኑት ተጫራቾች በሙሉ በእኩል ጊዜ በፅሁፍ ውጤትን መግለፅ አለበት፡፡ ለተሸነፉ ተጫራቾች የሚገለፀው የተሸነፉበትን ምክንያትና አሸናፊ የሆነውን ተጫራች ማንነት የሚገልፅ መሆን አለበት፡

2. በጨረታው አሸናፊ ለሆነው ተጫራች የሚላከው ደብዳቤ ኮርፖሬሽኑ እና በተጫራቹ መካከል እንደውል ሆኖ ሊያገለግል አይችልም፡፡ በኮርፖሬሽኑ እና በተጫራቹ መካከል ውል እንደተፈጸመ የሚቆጠረው ዝርዝር ጉዳዮችን ያካተተ ውል በኮርፖሬሽኑ ኃላፊ እና በተጫራቹ ሲፈረም ብቻ ነው፡፡

3. ለአሸናፊ ተጫራቾች ውል እንዲፈርም የሚላክበት ማስታወቂያ የሚከተሉትን ያካተተመሆን አለበት፡፡

ሀ. ኮርፖሬሽኑ በተጫራቾቹ የቀረበውን የመጫረቻ ሐሳብ የተቀበለ መሆኑን፣

ለ. ውሉ የሚፈጸምበትን ጠቅላላ ዋጋ (ማንኛውንም ግብር አካቶ)፣

ሐ.ተጫራቹ ማስያዝ የሚገባውን የውል ማስከበሪያ መጠን እና የማስከበሪያውን የመጨረሻ ቀን፣

4. የተለየ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር አሸናፊው ተጫራች ማሸነፉ ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ 7(ሰባት) የሥራ ቀናት ከመሙላቱ በፊት የግዥ ውል መፈረም የለበትም፡

5. ኮርፖሬሽኑ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ካረጋገጠ ተወዳዳሪዎች ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ተመላሽ ማድረግ አለበት፡-

ሀ. ከአሸናፊ ተጫራቾች ጋር ውል ፈርሞ ተጫራቹ የውል ማስከበሪያ ዋስትና ያቀረበከሆነ፣

ለ. የተሸናፊ ተጫራች ወይም የጨረታ ማስከበሪያውን የመጠቀሚያ ጊዜ ለማራዘም ፈቃደኛ ያልሆነ ተጫራች የጨረታ ማስከበሪያ ፀንቶ መቆያ ጊዜያበቃ ከሆነ፡፡

32. በጨረታው አሸናፊ የሆነው ተጫራች ውል ለመፈረም ፈቃደኛ ካልሆነ ከ15ኛው ቀን በኋላ ኮርፖሬሽኑ በቅድሚያ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ በመገምገም በውድድሩ ሁለተኛ የወጣው ተጫራች አሸናፊ ማድረግ ወይም አዲስ ጨረታ ማውጣት ይችላል፡፡

## 14. <u>ዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ</u>

የዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ የሚፈፀመው አገር በቀል እና የውጪ አቅራቢዎች እንዲወዳደሩ የሚጋበዙበት የግልፅ ጨረታ ዓይነት ሲሆን፡-

1. ኮርፖሬሽኑን ዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ መጠቀም የሚችለው ኮርፖሬሽኑ የውጪ ኩባንያዎች በጨረታው ተሳታፊ እንዲሆኑ ካልተደረገ በአገር ውስጥ ግልፅ ጨረታ ውጤታማ የሆነ ውድድር ሊኖር እንደማይችል ሲያምንበት ወይንም ግዥው በዚህ አንቀጽ ከተመለከተው የገንዘብ መጠን በላይ ሲሆን የዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታን መጠቀም የሚቻል ሲሆን በዓለም አቀፍ ግልፅ የጨረታ ዘዴ ግዥ ሊፈፀም የሚችለው፤

ሀ. ለግንባታ ዘርፍ ሥራ ከብር 150,000,000.00 (አንድ መቶ ሀምሳ ሚሊዮን ብር) በላይ፣

ለ. ለዕቃ ግዥ ከብር 50,000,000.00 (ሀምሳ ሚሊዮን ብር) በላይ፤

ሐ. ለምክር አገልግሎት ከብር 8,0000,00.00 (ስምንት ሚሊዮን ብር) በላይ፤

መ. ለሌሎች አገልግሎቶች ከብር 20,000,000.00 (ሃያ ሚሊዮን ብር) በላይ፤

2. ብቁ ሃገሮች (Eligible Countries)

ሀ. በመንግስት የሚታወቅ ተጫራቾች ብቁ አለመሆናቸውን በጨረታ ሰነዱ ላይ መግለፅ ይኖርበታል፤

ለ. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ክልከላው ለዕቃዎች ወይም ተያያዥ አገልግሎቶች አቅርቦት ውጤታማ ውድድሮችን እንደማይከለክል አምኖበት ክልከላው ከተጣለበት ሀገር ጋር የንግድ ግንኙነቶች እንዳይደረግ ይፋ በሆነ ሕግና ደንብ የከለከለ ከሆነ በኮርፖሬሽኑ ጨረታ ላይ መወዳደር አይችልም፤

ሐ. በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተር ምዕራፍ 7 ስር ከተወሰደው የፀጥታው ጥበቃ ምክር ቤት ውሳኔ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ከዚያ አገር ዕቃዎችንና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ማስመጣት ወይም ለዚያ ሀገር ሰዎች ወይም ድርጅቶች ማንኛውንም ክፍያ መፈፀም በኢትዮጵያ መንግሥት የተከለከለ ከሆነ በኮርፖሬሽኑ ጨረታ ላይ መሳተፍ አይችልም።

3. የዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ የሥራ ፍሰት

በዚህ መመሪያ ለብሔራዊ ግልፅ ጨረታ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪም በዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

ሀ. የጨረታ ጥሪ ማስታወቂያ እና የጨረታ ሠነድ የሚዘጋጀው በእንግሊዝኛ ቋንቋ መሆን አለበት፤

ለ. የጨረታው ጥሪ በቂ የሥርጭት ሽፋን ባለውና የውጭ ተጫራቾችን ሊጋብዝ በሚችል ጋዜጣ ላይ መውጣት አለበት። በተጨማሪም በርካታ ተጫራቾችን ለማግኘት እንዲቻል እንደ አስፈላጊነቱ በኮርፖሬሽኑ ድረ-ገጽ ላይ ማውጣት እና ለኤምባሲዎች የጨረታውን ጥሪ ማስተላለፍ፤

ሐ. ተጫራቾች ተገቢ የመጫረቻ ሰነድ ማዘጋጀት እንዲችሉ አርባ አምስት ቀን መሠጠት አለበት፣

መ. የሚዘጋጀው የፍላጎት መግለጫ የአገር ውስጥ ደረጃን ያሟላ እና ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው መሆን አለበት፤

ሠ. የውጭ አገር ተጫራቾች የሚያቀርቡት የመጫረቻ ዋጋና የጨረታ ማስከበሪያ በአገር ውስጥ በቀላሉ ሊመነዘር በሚችልና በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሚሠራበት የገንዘብ ዓይነትመሆን እንደሚገባው መገለፅ አለበት፤

ረ. የግዥ ፍላጎቱን ለማሟላት አሸናፊው የውጭ አገር ተጫራች ከአገር ውስጥ የሚጠቀመው ግብአት በሚኖርበት ጊዜ ከአጠቃላይ የውሉ ክፍያ በብር ሊከፈል የሚገባው መጠን በዋጋ ማቅረቢያው ሠንጠረዥ ላይ መመልከት ይኖርበታል፤

ሰ. ሌላ አማራጭ ካልተገኘ በስተቀር በውል አፈፃፀም ወቅት የሚነሱ አለመግባባቶች በኢትዮጵያ ሕግ የሚዳኝ ስለመሆናቸው መገለፅ አለበት፤

ሸ. በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ በሚፈፀም የዕቃ ግዥ ተሳታፊ የሚሆኑ ተጫራቾች ራሳቸው የዕቃው አምራቾች ካልሆኑ በኮርፖሬሽኑ ሲጠየቁ ከአምራቹ የተሰጣቸውን ውክልና ማቅረብ አለባቸው፡፡ በዓለም አቀፍ ጨረታ ሂደት የውጭ አገር ተጫራቾች ኮሚሽን ኤጀንት እንዲኖራቸው ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ በኮርፖሬሽኑ ሲታመንበት ኮሚሽን ኤጀንቱ መወከሉን የሚያሳይ ሕጋዊ የውክልና ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅበታል፤

ቀ ከዓለም አቀፍ ገበያዎች በግልፅ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ ኤል.ሲ. (L/C) ሊከፈትለት ይገባል፡፡

4. ሌሎች ዓለም አቀፍ ግዥዎች፡

ሀ. ከዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች በመጠቀም ዓለም አቀፍ ግዥ መፈጸም የሚቻለው ለየግዢ ዘዴው የተመለከተውን ሁኔታ እና የተፈቀደውን የገንዘብ መጠን መሰረት በማድረግ ይሆናል፡፡

ለ. ግዥው የሚፈፀመው በኮርፖሬሽኑ ዓለም አቀፍ የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ወይም ለዚሁ ሲባል በሚቋቋም እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች የተውጣጡና ከሦስት የማያንሱ አባላት የሚኖሩት በዋና ሥራ አስፈፃሚ አማካኝነት የሚቋቋም ይሆናል፡፡

ሐ. ለግዥው የሚወጣውን ወጪና ጊዜ ለመቀነስ ወይም ጥራቱን የጠበቀ ግዥ ለመፈፀም የተሻለ መሆኑ ሲታመንበት ከዓለም አቀፍ ገበያዎች በቀጥታ ግዥ መፈፀም ይቻላል፡፡

## 15. <u>የዓለም አቀፍ ጨረታ ግዥ የመወሰን ሥልጣን</u>

ማንኛውም ዓለም አቀፍ ግዥ በኮርፖሬሽኑ የዓለም አቀፍ የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ታይቶ እና ተገምግሞ በሚቀርበው የውሣኔ ሃሣብ መሰረት እስከ ብር 2,000,000,000 (ሁለት ቢሊዮን ብር) በዋና ሥራ አስፈፃሚ የመወሰን ሲሆን ከዚህ በላይ ከሆነ ለፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ሥራ አመራር ቦርድ ቀርቦ የመወሰን ይሆናል፤

16 .<u>የብሔራዊ ግልፅ ጨረታ ግዥ የመወሰን ሥልጣን</u>

1 በብሔራዊ ግልፅ ጨረታ ግዥ የሚከናወኑ የነጠላ ወይም የአንድ ጊዜ ግዥዎችን በገንዘብ መጠን የመወሰን ሥልጣን እንደሚከተለው ነው፡-

ሀ. ማንኛውም ከ 5,000,000.00 (አምስት ሚሊዮን ብር) በላይ የብሔራዊ ግልፅ ጨረታ ግዥ በኮርፖሬሽኑ የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ታይቶ እና ተገምግሞ በሚቀርበው የውሣኔ ሃሣብ መሰረት በዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም እርሱ በሚወክለው ይሁንታን ካገኘ በኂላ የሚፀድቅ ይሆናል፤

ለ. ማንኛውም በዕቅድና በጥቅል የሚፈጸም እና ግምታዊ ዋጋው እንደግዥው አይነት ዋጋው እስከ 5,000,000.00 (አምስት ሚሊዮን ብር) ድረስ የሆነ የታቀደ የብሔራዊ ግልፅ ጨረታ ግዥ በኮርፖሬሽኑ የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ታይቶ እና ተገምግሞ በሚቀርበው የውሣኔ ሃሣብ መሠረት ለዋና ሥራ አስፈፃሚ ቀርቦ አስተያየት ከተሰጠበት በኂላ በኮርፖሬት ሰርቪስ ዘርፍ ም/ዋና ሥራ አስፈፃሚው ወይም እርሱ በሚወክለው የጽሑፍ ይሁንታን ካገኘ በኂላ የሚፀድቅ ይሆናል፤

ሐ. ማንኛውም የግንባታና የምክር አገልግሎት የብሔራዊ ግልፅ ጨረታ ግዥ በኮርፖሬሽኑ በሚቀቋመው የቴክኒክ ኮሚቴ አማካኝነት የቴክኒካል ግምገማ ተደርጎ ከፋይናንሻል ውጤቱ ጋር ተደምሮ በሚቀርበው የውሣኔ ሃሣብ መሠረት በኮርፖሬሽኑ የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ታይቶ እና ተገምግሞ በሚቀርበው የውሣኔ ሃሣብ መሠረት ለዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም እርሱ ለሚወክለው ቀርቦ ይሁንታን ካገኘ በኂላ የሚፀድቅ ይሆናል፤

መ. በሚሰጥ ውክልና ማንኛውም በዕቅድና በጥቅል የሚፈጸሙ ግምታዊ ዋጋው እስከ ብር 1,000,000.00 (አንድ ሚሊዮን ብር) ድረስ የሆኑ የብሔራዊ ግልፅ ጨረታ ግዥ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴዎች ታይተውና እና ተገምግመው በሚቀርበው የውሣኔ ሃሣብ መሰረት በቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጆች የሚፀድቁ ይሆናል፤

ሠ. ማንኛውም በዕቅድና በጥቅል የሚፈጸሙ ግምታዊ ዋጋው እስከ ብር 500,000.00 (አምስት መቶ ሽህ ብር) ድረስ የሆኑ የብሔራዊ ግልፅ ጨረታ ግዥ በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴዎች ታይተውና እና ተገምግመው በሚቀርበው የውሣኔ ሃሣብ መሰረት በኮርፖሬት ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በሚሰጥ ውክልና መሰረት የሚፀድቁ ይሆናል፡፡

17. <u>**የውስን ጨረታ ግዥ አፈፃፀም**</u>

ኮርፖሬሽኑ የዕቃዎች፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎችና የምክር ወይም ሌሎች አገልግሎቶች ባህሪና የዋጋ መጠን ላይ ተንተርሶ ከታች ከተዘረዘሩት አንዱ ሲሟላ በአቅራቢዎች ዝርዝር ከያዛቸው ውስጥ ለተመረጡ ተወዳዳሪዎች በደብዳቤ በመጋበዝ በውስን ጨረታ አወዳድሮ ግዥ ሊፈፅም ይችላል፤

1. ግዥውን ለመፈፀም የግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ ለሁለት ጊዜ ወጥቶ ምንም ተጫራች ያልቀረበ ሲሆን፣
2. በግልፅ ጨረታው የቀረቡት ተጫራቾች በኮርፖሬሽኑ የተዘጋጀውን የቴክኒክ ፍላጎት የሚያማሉት አነስተኛ ከሆነ፣
3. የግልጽ ጨረታ ጥሪው፣ የተጠየቀው የጨረታ ማስከበሪያ መጠን እና አይነት እንዲሁም ሌላ ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪዎች ለመሳተፍ እንዳይችሉ የሚገድብ ሁኔታ በአሰራሩ ወይም በጨረታ ማስታወቂያው እና ሰነዱ ውስጥ አለመኖሩ ሲረጋገጥ ወይም፣
4. ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራውና የምክር ወይም ሌሎች አገልግሎቶች ከተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ የሚገኙ መሆኑ ሲረጋገጥ ወይም፣
5. በርካታ የጨረታ ሠነዶችን ለመመርመር እና ለመገምገም የሚጠይቀው ከፍተኛ ወጪና ጊዜ ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ስራው፣ የምክር ወይም ሌሎች አገልግሎቶች ካላቸው አነስተኛ ዋጋ ጋር የማይመጣጠን ሆኖ ሲገኝ፣ ወይም
6. ዕቃው፣ የግንባታ ስራው፣ የምክር ወይም ሌሎች አገልግሎቶቹ በአስቸኳይ የሚፈለጉ በመሆናቸው ምክንያት በግልጽ ጨረታ ለመግዛት አዳጋች መሆኑ ለኮርፖሬት ዘርፍ ም/ዋና ሥራ አስፈፃሚ እስከ 3,000,000 (ሶስት ሚሊዮን) እና ቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጆች ሲታመንበት እስከ ብር 1,000,000 (አንድ ሚሊዮን) ሲፈቀድና ሲፀድቅ፣
7. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 6 በተጠቀሰው መሠረት በዋና መሥሪያ ቤት በኮርፖሬት ሰርቪስ ዘርፍ እና በቅርንጫፎች መጠኑ ከብር 3,000,000 (ሶስት ሚሊዬን) በላይ ለሚሆኑ ግዥዎች በኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሲፈቀድና ሲፀድቅ፤
8. ኮርፖሬሽኑ በመስኩ የተሰማሩት አቅራቢዎች በውስን ጨረታ ቢጋበዙ ለመሳተፍ ፈቃደኛ ሊሆኑ እንደሚችሉ ሲያምን፤
9. የሚገዙት ዕቃዎች፣ አገልግሎት እና የግንባታ ሥራዎች ከበርካታ አቅራቢዎች የሚገኙ ቢሆንም ግዥው አስቸኳይ በመሆኑ የተነሳ ተጫራቾችን በግልፅ ጨረታ ለመጋበዝና ለማወዳደር በቂ ጊዜ በማይኖርበት ጊዜ እና የሚገዙትን ዕቃዎች ጥራት በገለልተኛ አካል

በላብራቶሪ ምርመራ ማረጋገጥ የማይቻል በመሆኑ የተነሳ ዕቃዎችን ከታወቁ አምራቾች ወይም ከዋና ዋና አቅራቢዎች መግዛቱ የተሻለ ሆኖ ሲገኝ ወይም ጥራቱን የጠበቀ ግዥ ለመፈፀም የተሻለ መሆኑ ሲታመንበት፤

10. በዚህ አንቀፅ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 9 የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው በውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ መጠቀም የሚቻለው የገንዘብ መጠን ለአንድ ጊዜ

    ሀ. ለግንባታ ዘርፍ ሥራ ግዥ ከብር 50,000,000.00 (ሀምሳ ሚሊዮን ብር) ያልበለጠ፣

    ለ. ለዕቃ ግዥ ከብር 10,000,000.00 (አስር ሚሊዮን ብር) ያልበለጠ፣

    ሐ. ለምክር አገልግሎት ግዥ ከብር 20,000,000,00 (ሀያ ሚሊዮን ብር) ያልበለጠ

    መ. እና ለሌሎች አገልግሎቶች ግዥ ከብር 5,000,000,00 (አምስት ሚሊዮን ብር) ያልበለጠ ሲሆን ብቻ ነው፡፡

11. በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ ከ"ሀ" እስከ ፊደል ተራ "መ" የተገለፀው ቢኖርም ዕቃው፣ የግንባታ ሥራው ወይም አገልግሎቱ በውስን ጨረታ ቢገዛ በተሻለ ጥራትና ፍጥነት እንዲሁም በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርብ መሆኑ በሚመለከተው አካል በዝርዝር ተገምግሞ የውሣኔ ሃሣብ ሲቀርብና በዋና ሥራ አስፈፃሚ ሲፀድቅ ግዥው ይፈፀማል፡፡

12. በውስን የጨረታ ዘዴ ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራውና የምክር ወይም ሌሎች አገልግሎቶች ከተወሰኑ አቅራቢዎች አወዳድሮ መግዛቱ ከሚሰጠው ኢኮኖሚያዊ እሴት እንዲሁም ለኮርፖሬሽኑ ለሚኖረው አስፈላጊነት (Criticality) አኳያ ተመዝኖ በገበያ ላይ በመስኩ ከተሰማሩት አቅራቢዎች በተፈላጊው መስፈርት የተወሰኑትን በመጋበዝ ግዥውን መፈጸም የተሻለ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን በቅደሚያ የውስን ጨረታ ግዢ ዘዴ ምክረ ሃሳብ ቀርቦ በኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሲታመንበት እና ሲፀድቅ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ 10 ላይ ከተገለፀው ገንዘብ መጠን  በውስን ጨረታ ግዢ መፈፀም ይችላል፡፡

13. የውስን ጨረታ ግዥ ዘዴው የሥራ ፍሰት

    ሀ. የውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ የስራ ፍሰት ለግልፅ ጨረታ የተፈቀደውን  ዝርዝር የአፈፃፀምሥርዓት ተከትሎ የሚከናወን ይሆናል፣

    ለ. የጨረታ ጥሪው በቀጥታ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች በአድራሻቸው የሚላክ ሆኖ፡ ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው ወይም አገልግሎቱ ከተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ የሚገኝ ሲሆን የጨረታ ጥሪው ደብዳቤ ለሁሉም አቅራቢዎች በተመሳሳይ ሰዓት

በአድራሻቸው ተዘጋጅቶ መላክ ይኖርበታል፡፡ በጨረታው ተሳታፊ ሊሆኑ የሚችሉ አቅራቢዎች ቁጥር በርካታ ቢሆንም ግዥው በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ከተመዘገቡት መካከል ፍትሐዊ በሆነ ምርጫ ቢያንስ አምስት ዕጩ ተወዳዳሪዎች ተጋብዘው የቀረበው አንድም ተጫራች ቢሆን ያቀረበው የመጫረቻ ሰነድ የቴክኒክ ፍላጎቱን የሚያሟላና ዋጋውም የገበያ ዋጋ መሆኑ ከተረጋገጠ ጊዜ ለመቆጠብ እንዲቻል ግዥው ሊፈፀም ይችላል፡፡

ሐ. ኮርፖሬሽኑ በውስን ጨረታ ለሚፈፀም ግዥ የሚመረጡትን አቅራቢዎች ከኮርፖሬሽኑ የአቅራቢዎች ዝርዝር፣ ከመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የአቅራቢዎች ዝርዝር እንዲሁም ከማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የአቅራቢዎች ዝርዝር መምረጥ አለበት፡፡

መ. ኮርፖሬሽኑ ለግዥው ለተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ በዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍያ መከፈል አያስፈልግም ብሎ ሲያምን ከጨረታ ጥሪው ደብዳቤ ጋር የጨረታ ሰነዱን አያይዞ ሊልክይችላል፡፡

ሠ. ኮርፖሬሽኑ በውስን ጨረታ የተጋበዙ ተጫራቾችን ማንነት ለሌሎች ዕጩ ተወዳዳሪዎች ማሳወቅ የለበትም፡፡

ረ. በውስን ጨረታ የተጋበዙት ተጫራቾች በሙሉ ከጨረታ መቆያ ጊዜ ገደቡ በፊት የመጫረቻ ሰነዳቸውን ካቀረቡ የጊዜ ገደቡ እስከሚጠናቀቅ መጠበቅ ሳያስፈልግ ኮርፖሬሽኑ ጨረታው እንዲከፈት በመወሰን ጊዜውን ለሁሉም ተጫራቾች በማሳወቅ እና እንዲገኙ በመጋበዝ ጨረታው እንዲከፈት ሊያደርግ ይችላል፡፡

ሰ. በመወዳደሪያ ሐሳብ መጠየቂያ የሚፈፀመው የውስን ጨረታ የምክር አገልግሎት ግዥ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 21 ላይ የተገለጹትን ተጨማሪ አሰራሮች ተከትሎ መፈጸም ይኖርበታል፡፡

## 18. <u>በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀም ግዥ</u>

1. ኮርፖሬሽኑ አስቀድሞ ማቀድ እስከቻለ ድረስ ግዥ በግልፅ ጨረታ ዘዴ በጅምላ መፈፀም አለበት፡፡ ሆኖም ኮርፖሬሽኑ ወዲያውኑ ጥቅም ላይ የሚውሉ ወይንም በጅምላ ሊገዙ ያልቻሉ እና ዋጋቸው በንዑስ አንቀፅ 18.2 በተመለከተው ገደብ ውስጥ ይሆናል ተብሎ የሚገመቱ ግዥዎችን በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ መፈፀም ይችላል፡፡ ከላይ በተገለጸው መሠረት ግዥ መፈጸም የሚቻለው ቀጥሎ ከፊደል ተራ "ሀ" እስከ "ሠ" በተመለከተው ሁኔታ ጥያቄው ሥልጣን ላለው አካል ቀርቦ ሲፈቀድ ብቻ ነው፡-

ሀ. ውክልና ከዋና ስራ አስፈጻሚ ሲሰጥ ለግንባታ ሥራ ግዥ እስከ ብር 500,000.00 (አምስት መቶ ሽህ) የሆኑ ግዥዎችን በኮርፖሬት ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፤ ከዚያ በላይ እስከ ብር 1,000,000.00 (አንድ ሚሊዮን ብር) ድረስ በኮርፖሬት ሰርቪስ ዘርፍ ም/ዋና ሥራ አስፈጻሚ፤

ለ. ውክልና ከዋና ስራ አስፈጻሚ ሲሰጥ ለዕቃ ግዥ ለማዕከልና ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ለእያንዳንዳቸው በዓመት ውስጥ ከብር 2,000,000 (ሁለት ሚሊዮን ብር) የማይበልጥና የአንድ ጊዜ ግዥው እስከ ብር 300,000.00 (ሶስት መቶ ሺህ) ድረስ በኮርፖሬት ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወይም በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ፣ ከዚያ በላይ እስከ ብር 500,000.00 (አምስት መቶ ሺህ) ድረስ ለዋና አስፈጻሚ ቀርቦ ከፀደቀ በኋላ ግዥ መፈፀም ይችላል፤

ሐ. ውክልና ከዋና ስራ አስፈጻሚ ሲሰጥ ለምክር አገልግሎት ግዥ እስከ ብር 240,000 (ሁለት መቶ አርባ ሺህ) ድረስ በኮርፖሬት ሰርቪስ ዘርፍ ም/ዋና ሥራ አስፈጻሚ፤

መ. ውክልና ከዋና ሰራ አስፈጻሚ ሲሰጥ ለሌሎች አገልግሎቶች ግዥ እስከ ብር 300,000 (ሶስት መቶ ሽህ) ድረስ በኮርፖሬት ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወይም በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ፤

ሠ .ውክልና ከዋና ስራ አስፈጻሚ ሲሰጥ ለዕቃና ለሌሎች አገልግሎቶች ግዥ እስከ ብር 100,000.00 (መቶ ሺህ) ድረስ የግዥ አፈፃፀም ቡድን መሪ ወይም የግዥና ንብረት አስተዳደር ቡድን መሪ በኮርፖሬት ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወይም በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ ቀርቦ ታምኖበት ከፀደቀ በኋላ ግዥ መፈፀም ይችላል፤

2. ከሚመለከተው ገንዘብ መጠን የማይበልጥና በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ የሚፈፀም ለግዥ አፀዳቂ ኮሚቴ ማቅረብ ሳያስፈልግ በኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም እርሱ በሚወክለው ሰው እንዲፀድቅ በማድረግ ግዥን መፈፀም ይችላል፤

ሀ. ለግንባታ ስራ ግዥ...............................1,000,000.00

ለ. ለዕቃ ግዥ......................................... 500,000.00

ሐ. ለምክር አገልግሎት ግዥ....................... 240,000.00

መ. ለሌሎች .........................................300,000.00

ሠ. የግንባታ ዕቃዎችን የማቅረብ ኃላፊነት ኮርፖሬሽኑ በሚሆንበት ጊዜ ለግንባታ ዕቃዎች ግዥ ተግባራዊ የሚሆነው ለግንባታ ሥራ ግዥ የተፈቀደው ገንዘብ ይሆናል፡፡

3. የሚገዛው ዕቃ ወይም አገልግሎት ወይም የግንባታ ሥራ ዋጋ በዚህ  አንቀጽ ንዑስ 2 ከ"ሀ" እስከ "ሠ" ከተገለፀው በላይ ቢሆንም የግዥው በአስቸኳይ አለመፈፀም በኮርፖሬሽኑ ሥራ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል ከሆነ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም እርሱ በሚወክለው  ግዥው ሊፈፀም ይችላል፡፡

4. የዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ የሥራ ፍሰት

ግዥው ለገበያ የተዘጋጁ ወይም የታወቀ ገበያ ያላቸው ዕቃዎች፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ወይም አገልግሎቶች ግዥ ሲሆን፣

1. ኮርፖሬሽኑ በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ግዥ ሲፈፅም በውድድሩ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚመረጡት አቅራቢዎች ከኮርፖሬሽኑ የአቅራቢዎች ዝርዝር፣ በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ሆኖ ቢያንስ ከሦስት አቅራቢዎች የዋጋ ማቅረቢያ በመሰብሰብ ወይም በቂ አቅራቢዎች ማግኘት በማይቻልበት ጊዜ ተመሣሣይ ዕቃ ወይም አገልግሎት የሚያቀርቡ አቅራቢዎች ዕቃው ወይም አገልግሎቱ እንደሌላቸው በድርጅቱ ሕጋዊ ማህተምና ፊርማ ከተረጋገጠ የዋጋ ማቅረቢያ እንደተሰበሰበ ይቆጠራል፡፡ ውድድሩንም ፍትሃዊ ለማድረግ፡-

   ሀ. በኮርፖሬሽኑ የአቅራቢዎች ዝርዝር፣ በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡት ሁሉም ተሳታፊዎች እስከተቻለ ድረስ በዙር የመወዳደር ዕድል ማግኘታቸውን እና ለኮርፖሬሽኑ ጠቃሚ የሆነ የተለየ ሁኔታ መኖሩ ካልተረጋገጠ በስተቀር አንድን ወይም የተወሰኑ አቅራቢዎችን ብቻ በተደጋጋሚ ውድድር መጋበዝ የለበትም፤

   ለ. ዋጋ ማቅረቢያ ግዥ በተለይ የዋጋ ማቅረቢያ በመስጠት እና ዋጋ በመወሰን ሒደት ሊፈጠር የሚችል መመሳጠርን ለመከላከል የሚያስችል አሠራር መከተል እና በየጊዜው ቁጥጥር ማድረግ ይገባል፤

ሐ. እያንዳንዱ ዕጩ ተወዳዳሪ እንዲያቀርብ የሚፈቀድለት አንድ የመወዳደሪያ ዋጋ ብቻ ሲሆን፣ ያቀረበውን ዋጋ መለወጥ አይፈቀድለትም፤

መ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ 4 ከፊደል ተራ ከ “ሀ” እስከ “ሐ” የተገለፀው ቢኖርም ኮርፖሬሽኑ በዋጋና በጥራት ተቀባይነት ያላቸውን የዕቃ፣ የአገልግሎት እና የግንባታ ሥራ ግዥዎች ከመንግስት መ/ቤቶች ወይም የልማት ድርጅቶች ወይም መሠል ተቋም ካላቸው አትራፊ ካልሆኑ ወይም ለትርፍ ከተቋቋሙ ሕዝባዊ ድርጅቶች ጋር የገበያ ትስስር በመፍጠር በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ መፈጸም ይቻላል፡፡ ሆኖም ግዥውን ከእነዚህ ድርጅቶች መፈፀም ካልተቻለ ከአምራቾች ወይም ከአምራቾች ሕጋዊ ውክልና ካላቸው ድርጅቶች ተወዳድረው መግዛት ይቻላል፤

ሠ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ (4) “መ” በተገለጸው መሠረት ግዥውን መፈፀም ካልተቻለ በአቅራቢነት ከተመዘገቡና በዘርፉ ፍቃድ ካላቸው ማናቸውም ድርጅቶች ግዥውን መፈፀም ይቻላል፤

2 እያንዳንዱ እጩ ተወዳዳሪ እንዲያቀርብለት አንድ የመወዳደሪያ ዋጋ ብቻ ሆኖ ያቀረበውን ዋጋም መለወጥ አይፈቀድለትም፡፡ ዕጩ ተወዳዳሪው በሰጠው የመወዳደሪያ ዋጋ ላይ ኮርፖሬሽኑ እና በዕጩ ተወዳዳሪው መካከል ምንም ዓይነት ድርደር ሊደረግ አይችልም፤

3 ከፍተኛ የዋጋ ልዩነት ሊያመጡ የሚችሉ የጥራት ደረጃዎችን በመለየት በዋጋ የሚወዳደሩት ተቀራራቢ የጥራት ደረጃ ያላቸው አቅርቦቶች መሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባል፡፡ የተለየ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር ኮርፖሬሽኑ የሚፈልገውን የጥራት ደረጃ የሚያሟሉ አቅርቦቶችን በማወዳደር ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበውን አቅራቢ አሸናፊ አድርጎ መምረጥ አለበት፡፡

4 በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈፀም ግዥ የሚደረገው የዋጋ ውድድር በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ተመሳሳይ ይዘት ያለው የዋጋ ስሌት መሆን ያለበት ሲሆን ውድድሩ ታክስን ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡፡

5 ኮርፖሬሽኑ በዋጋ ማቅረቢያ በተደጋጋሚ ለሚፈፅማቸው ግዥዎች የግዥ ሥራ ክፍሉ የገበያ ጥናት ማድረግ፣ የወቅቱን የገበያ ዋጋ ማወቅ እና ኮርፖሬሽኑ ዝቅተኛ ብሎ የሚመርጠው ዋጋ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሆኑን ማመን ይኖርበታል፡፡

6 ኮርፖሬሽኑ በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀሙ ግዥዎችን በተሻለ ለመቆጣጠር ያስችለኛል ብሎ የሚያምንባቸውን አፈፃፀሞች ተግባራዊ ማድረግ የሚችል ሲሆን በተለይ የሚከተሉትን ያሟላ መሆኑ ተረጋግጦ የዋጋ መጠየቂያ ለመላክ እና የዋጋ ማቅረቢያ ለመቀበል የሚያስችል የኤሌክትሮኒክስ የመረጃ መለዋወጫ ዘዴ በመፍጠር ተግባራዊ ማድረግ ይችላል፡፡

ሀ. የሚዘረጋው የኤሌክትሮኒክ የመረጃ መለዋወጫ ዘዴ መረጃ ሊደርሰው ከሚገባው አካልእና መረጃው ሊታወቅ ከሚገባው ቀን እና ሰዓት ውጪ በማንኛውም አካል ሊታይ እንደማይችል የሚያረጋግጥ የተሟላ የመረጃ ደህንነት ሲኖረው፣

ለ. በዋጋ ማቅረቢያ ሊወዳደሩ የሚችሉ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሙሉ በዘዴውለመጠቀም የሚያስችል ዕውቀት እና ዝግጁነት ያላቸው መሆኑሲረጋገጥ፣

ሐ. በዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል ተራ “ለ” የተቀመጠው ቢኖርም በኤሌክትሮኒክስ የመረጃ መለዋወጫ ዘዴ ዋጋ መስጠት የማይችሉ በተለመደው አሰራር በፖስታ ዋጋ ሊሰጡ እንዲችሉ አማራጭ የተዘጋጀላቸው እና ይህም የተገለፀላቸው ሲሆን፣

መ. በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ለሚከናወኑ ግዥዎች አቅራቢው የሰጠ የመወዳደሪያ ዋጋ (ፕሮፎርማ) እና መስሪያ ቤቱ ለአቅራቢው የግዥ ትዕዛዝ የሰጠበት ደብዳቤ እንደውል ስለሚቆጠሩ ተጨማሪ ውል መዋዋል አስፈላጊ አይሆንም፡፡ በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ለሚከናወኑ ግዥዎች አቅራቢው የሰጠው የመወዳደሪያ ዋጋ /ፕሮፎርማ/ እና ኮርፖሬሽኑለአቅራቢው የግዥ ትዕዛዝ የሰጠበት ደብዳቤ እንደውል ይቆጠራል፡፡

7 በዚህ የግዥ ዘዴ ለመጠቀም ሲባል ኮርፖሬሽኑ በአንድነት ሊፈፀሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ከፋፍሎ መግዛት አይችልም፡፡

## 19. ከአንድ አቅራቢ የሚፈጸም ግዥ

ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱ ሲያጋጥም ኮርፖሬሽኑ ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈጸም ይችላል፡-

1. ኮርፖሬሽኑ በዓይነት እና በዋጋ አንድ የሆኑ ዕቃዎችን፣ የግንባታ ሥራዎችን የምክር ወይም ሌሎች አገልግሎቶችን ቀደም ሲል እነዚህን ካቀረበ ተጫራች መግዛት ጠቃሚ መሆኑ ሲታመንበት እና አቅራቢው ፈቃደኛ ከሆነ ኮርፖሬሽኑ የሚከተሉትን አሠራሮች ተከትሎ ተጨማሪ ግዥ ሊፈፅም ይችላል፡፡

   ሀ. በተጨማሪነት የሚታዘዘው ዕቃ፣ የግንባታ ሥራ፣ የምክር ወይም ሌሎች አገልግሎቶች ግዥ መጠን ቀደም ሲል ከተገዛው ከ 25% (ሃያ አምስት በመቶ) መብለጥ የለበትም፡፡

   ለ. ተጨማሪ ግዥ ለማዘዝ የቀድሞው ግዥ ውል ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ወይም ከተጠናቀቀበት ቀን አንስቶ በሚቀጥሉት 6 ወራት ባለው ጊዜ ውስጥ የግዥ ትዕዛዙ መተላለፍ ይኖርበታል፡፡

   ሐ. በዚህ መሠረት ለሚፈፀም ግዥ በመጀመሪያው ከነበረው ውል የተለየ የዋጋ ጭማሪ ማድረግ አይፈቀድም፡፡

   መ. በንዑስ አንቀጽ 19(1)(ሐ) ከላይ የተቀመጠው ቢኖርም የመጀመሪያው ውል የዋጋ ማስተካከያ የሚፈቅድ ከሆነ እና የዋጋ ማስተካከያ ይደረግባቸዋል የተባሉት ግብአቶች በተጨማሪው ውል ውስጥ የሚገኙ ከሆነ በመጀመሪያው ውል ላይ በነበረው የዋጋ ማስተካከያ አሰራር እና ስሌት መሰረት ዋጋ ማስተካከያ በማድረግ ግዥው ሊፈፀም ይችላል፡፡

2. ያልታሰቡ ሁኔታዎች በማጋጠማቸው ምክንያት በመጀመሪያው ውል ውስጥ ያልተካተቱ ተጨማሪ የግንባታ ሥራዎች ሲኖሩ ኮርፖሬሽኑ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን አረጋግጦ ማሠራት ይችላል፡፡

   ሀ. ኮርፖሬሽኑ በተጨማሪነት እንዲሰሩ የታሰቡት ስራዎች በመጀመሪያው ውል ውስጥ መካተት ይገባቸው የነበሩ እና ስራዎቹን ነጣጥሎ ማሰራት ለአፈፃፀም አስቸጋሪ ወይም የኮርፖሬሽኑን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚጎዳ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

ለ. በተጨማሪነት የሚታዘዘው የግንባታ ስራ የገንዘብ መጠን ከመጀመሪያው ውል ጠቅላላ ዋጋ ከ 30% የበለጠ መሆን የለበትም፡፡

ሐ. በተጨማሪነት የሚታዘዙት የግንባታ ሥራዎች የነጠላ ዋጋ በመጀመሪያው ውል ውስጥ ሊገኝ የሚችል ከሆነ የተጨማሪው ስራ በመጀመሪያው ውል ውስጥ ባለው ነጠላ ዋጋ መሠረት ተፈፃሚ የሚሆን ሲሆን የነጠላ ዋጋው በመጀመሪያው ውል ውስጥ የማይገኝ ከሆነ በድርድር ስምምነት ላይ የሚደረስበት ዋጋ የገበያ ዋጋ መሆኑን ኮርፖሬሽኑ ማረጋገጥ አለበት፡፡

3. ኮርፖሬሽኑ ለሚጠቀምበት ዕቃ የሚያስፈልገው መለዋወጫ የሚገኘው ቀደምሲል ዕቃውን ከሸጠው አቅራቢ ብቻ መሆኑ ሲረጋገጥ፣ ለዚህም

ሀ. ኮርፖሬሽኑ በቂ የገበያ ጥናት በማድረግ እና ሌላ የተሻለ አማራጭ ገበያው ላይ የሌለ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

ለ. ኮርፖሬሽኑ ለሚጠቀምበት ዕቃ የሚገዛው መለዋወጫ ብዛት፣ ተደጋጋሚነት እና የገንዘብ መጠን አንፃር ወደፊት ሌላ አማራጭ መፈለግ የሚያስፈልገው መሆኑንና አለመሆኑን መወሰን ይኖርበታል፡፡

4. ግዥው ከሌላ አቅራቢ ቢፈፀም የሚገዛው ዕቃ ወይም አገልግሎት ኮርፖሬሽኑ ከሚጠቀምበት መሣሪያ ወይም አገልግሎት ጋር ተጣጥሞ የማይሄድ መሆኑ በባለሙያ ሲረጋገጥ፡፡

5. የማሽነሪ እና የተሽከርካሪ መለዋወጫ ከአምራቹ ወይም ከአምራቹ ብቸኛ ወኪል ከሆነ ድርጅት በቀጥታ ለመግዛት ይቻላል፡፡

6. የመለዋወጫ ግዥ ከመሣሪያዎቹ አምራቾች ወይም ከአምራቾች ውክልና (Manufacturer Authorization) ከተሰጣቸው አቅራቢዎች እና የአምራቾቹ ወይም የአቅራቢዎቹ ቅርንጫፍ በሌሉባቸው ቦታዎች ከአምራቾቹ ወይም ከአቅራቢዎቹ ውክልና ከተሰጣቸው አከፋፋዮች (Dealers) ጋር በሚደረግና በየዓመቱ የሚታደስ ውል በመግባት ውል መግባት ካልተቻለም በቀጥታ ግዥ መፈፀም ይቻላል፡፡

7. የግንባታ ሥራው፣ የምክር ወይም ሌሎች አገልግሎቶቹ የሚገኙት ከአንድ አቅራቢ ብቻ በመሆናቸው ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ፤ ወይም አገልግሎቱን ለመስጠት አቅራቢው ብቸኛ መብት ያለው ሲሆን፡፡

8. ግዥው አስቸኳይ በመሆኑ ምክንያት በጨረታ ሥርዓት ወይም ሌሎች የግዥ ዘዴዎችን በመጠቀም ተግባራዊ ሊሆን የማይችል ሲሆን እና ጉዳዩን በኮሚቴ ለማየት ጊዜ ስለማይኖር በዋና ስራ አስፈጻሚ ሲፈቀድ የሚፈፀም ይሆናል፣

9. ኮርፖሬሽኑ ይህ የግዥ ዘዴ በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ውድድር እንዳይኖር ወይም በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ልዩነት ለመፍጠር ታስቦ ጥቅም ላይ ያልዋለ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበ

10. ከዚህ በታች በተመለከቱት ምክንያቶች ከአምራቹ ወይም የአምራቹ ውክልና ካለው አቅራቢ ጋር በመደራደርና የረጅም ጊዜ ኮንትራት በመፈራረም ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ ግዥ መፈፀም ይቻላል፡፡

   ሀ. የቴክኖሎጂ ችግርን ለመቋቋም፣

   ለ. የአቅርቦት አስተማማኝነትና ለማረጋገጥ፣

   ሐ. በሌሎች አማራጭ የግዥ ስልቶች ከመጠቀም ይልቅ ከአንድ አቅራቢ መግዛት የተረጋገጠና ዘላቂነት ያለው የዋጋና የጥራት ጠቀሜታ ሊገኝ መቻሉ ሲረጋገጥ፣

   መ. ሌሎች ተጨባጭ ጥቅሞችን እንደሚያስገኝ ሲታመን፣

11. በኮርፖሬሽኑ በግዥ ዕቅድ ውስጥ ያልተካተቱ ዋጋቸዉ ከብር 5,000 (አምስት ሺህ ብር) ያልበለጠ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ወይም በጉዞ ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ከመፍታት ጋር የተያያዙ የቀጥታ ግዥዎችን ከማናቸውም ሻጭ ድርጅት መፈፀም ይችላል፡፡ ሆኖም በዚህ ዓይነት የሚፈፀሙ ጥቃቅን ግዥዎች ድምር በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ከብር 100,000 (አንድ መቶ ሽህ ብር) መብለጥ አይኖርበትም፤

## 20. <u>በለቀማ የሚፈጸም ግዥ</u>

ኮርፖሬሽኑ ከገበያ በለቀማ የሚፈፀመውን ግዥ ከመደበኛ አቅራቢዎች የማይገኝ ወይም በለቀማ ቢገዛ ለኮርፖሬሽኑ፣ ቅርንጫፎች ጽ/ቤቶች የኢኮኖሚ ጥቅም እንደሚያስገኝ ሲረጋገጥ የሚከተሉትን አሠራሮች በመከተል የለቀማ ግዥ መፈፀም ይቻላል፡፡

1. ግዥውን በለቀማ መፈፀም ያስፈለገበትን ምክንያት የሚያስረዳ ማስታወሻ በዋና መ/ቤት ለግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት፣ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ለቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጆች ቀርቦ መፈቀድ ይኖርበታል፡፡

2. ኮርፖሬሽኑ ግዥውን በለቀማ ሊገዙ የሚችሉ ብዛታቸው ከሦስት ያላነሱ አባላት ያሉት ጊዜያዊ ኮሚቴው መሠየም ይኖርበታል፡፡ ኮሚቴው የሚሰየመው በዋና መ/ቤት ለግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት፣ በቅርንጫፍ ደግሞ የቅርንጫፉ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ የኮሚቴው አባላት ስብጥር ከግዥ ጠያቂው ክፍል፣ ከግዥ የሥራ ክፍል፣ ከንብረት አስተዳደር የሥራ ክፍል የሚዋቀር ይሆናል፡፡

3. የተቋቋመው ጊዜያዊ ኮሚቴ ግዥውን በጋራ በመሆን ማከናወን ያለበት ሲሆን ግዥውን ለማከናወን በቂ አቅርቦት የሚኖርበትን ገበያ እና የገበያ ዕለት በመምረጥ ለሚመለከተው ኃላፊ ያሳውቃል፡፡

4. ጊዜያዊ ኮሚቴው በጋራ በመሆን በገበያው ውስጥ ካለው አቅርቦት የተሻለ ጥራት እና ዋጋ ያለውን ወይም ያላቸውን ሻጮች በመምረጥ ዋጋ ተደራድሮ ግዥውን ይፈፅማል፡፡

5. በግዥው አፈፃፀም ሂደት የተፈፀሙትን ግዥዎች ብዛትና ዓይነት፣ ግብይቱ የተፈፀመበትን ቦታ፣ የተከፈለውን የገንዘብ መጠን፣ የሻጮችን ሙሉ ስምና አድራሻ የሚገልፅ ሠነድ ተዘጋጅቶ ሻጮች በፊርማቸው እንዲያረጋግጡ መደረግ ይኖርበታል፡፡

6. ጊዜያዊ ኮሚቴ አጠቃላይ የለቀማ ግዥ አፈፃፀሙን የሚገልፅ ቃለ ጉባኤ በማዘጋጀት ተፈራርሞ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ሪፖርቱም ኮሚቴውን ባቋቋመው የሥራ ኃላፊ መፅደቅ ይኖርበታል፡፡

## 21. በመወዳደሪያ ሐሳብ መጠየቂያ የሚፈፀም ግዥ

21.1 ቅድመ ሁኔታዎች

21.1.1 ኮርፖሬሽኑ የምክር ግዥን የመወዳደሪያ ሐሣብ በመጠየቅ መፈፀም የሚኖርበት ሲሆን የግዥው ግምታዊ የገንዘብ መጠን ከብር 500,000. (አምስት መቶ ሺ) በላይ ሲሆን ተጫራቾችን ለመምረጥ የፍላጎት መጠየቂያ ጨረታ በቅድሚያ ማውጣት ይኖርበታል፡፡

21.1.2 ኮርፖሬሽኑ በመዳደሪያ መጠየቂያ ግዥ መፈፀም የሚቻለው ለምክር አገልግሎት ወይም ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ ውስጥ የምክር አገልግሎቱ ዋጋ ከ 50 በመቶ በላይ ለሚሆን ግዥ ነው፤

21.1.3 የመወዳደሪያ ሃሳብ ለማቅረብ የሚጋበዙት አማካሪዎች አመራረጥ የሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ ይፈጸማል፡፡

ሀ. በወጣው የፍላጎት መግለጫ መጠየቂያ መሰረት ፍላጎታቸውን ከገለፁ አማካሪዎች ውስጥ የተሻለ ብቃት ያላቸውን በመምረጥ፣

ለ. የሚፈለገውን የምክር አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ አማካሪዎች ውስን ሲሆኑ እነዚህን አማካሪዎች በሙሉ በመጋበዝ፣

ሐ. የግዥው ግምታዊ መጠን ከብር 500,000. (አምስት መቶ ሺህ) በላይ ሲሆን ከኮርፖሬሽኑ፣ ከመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ዝርዝር ውስጥ በመምረጥ፣

21.1.4 በንዑስ አንቀፅ 21.1.3 ፊደል ተራ “ሐ” መሰረት የመወዳደሪያ ሐሳብ ለማቅረብ የሚጋበዙት አማካሪዎች ቁጥር እስከተቻለ ድረስ ከሦስት ያላነሱ እና ከሰባት ያልበለጡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

21.1.5 የፍላጎት መግለጫ ጥሪው የሚፈለገውን የምክር፣ የአገልግሎት አይነት፣ የሚጠበቀውን ውጤት፣ ጊዜውን፣ አማካሪው ሊኖረው የሚገባውን ብቃት፤ የስራ ልምድ እና የመሳሰሉትን የያዘ እና ዕጩ ተወዳዳሪዎች ሊያቀርቡት የሚገባውን መረጃ ዝርዝር እና የሚያቀርቡበትን ቦታና ጊዜ የሚገልፅ መሆን አለበት፡፡

21.1.6 ኮርፖሬሽኑ የመወዳደሪያ ሐሳብ እንዲያቀርቡ ለተመረጡ አማካሪዎች የጥሪ ደብዳቤ በአድራሻቸው መላክ ያለበት ሲሆን ለግዥው ለተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ በዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍያ መክፈል አያስፈልግም ብሎ ሲያምን ከጨረታ ጥሪው ደብዳቤ ጋር የጨረታ ሰነዱን ሊልክ ይችላል፡፡

21.1.7 ለመወዳደሪያ ሐሳብ መጠየቂያ የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ በዚህ መመሪያ ለብሔራዊ ግልፅ ጨረታ የተዘረጋውን ሥርዓት በመከተል የሚዘጋጅ መሆን ይኖርበታል፡፡

21.1.8 ኮርፖሬሽኑ ከተመረጠው አማካሪ ጋር የሚያደርገው ድርድር መሰረታዊውን የጨረታ ይዘትና የሥራ ጥናት የማይቀየር ሆኖ ስለሥራው ይዘት፣ ስለአሠራር ዘዴው ስለሚሠማራው የሰው ኃይል እና መሣሪያ፤ ስለሪፖርት አቀራረብ እና ይዘት በመሳሰሉት ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል፡፡

21.1.9 በንዑስ አንቀጽ 21.1.8 መሰረት የሚደረገው ስምምነት የኮርፖሬሽኑን ጥቅም የሚጎዳ ወይም ለተመረጠው አማካሪ ከሌሎች ተጫራቾች አንፃር ፍትሐዊ ያልሆነ ጥቅም የሚያሰጠው መሆን የለበትም፡፡

21.1.10 በንዑስ አንቀጽ 21.1.9 ሥር የተገለፁት የመረጣ ዘዴዎች እንደተጠበቁ ሆነው ሌሎች የጨረታ አፈጻጸም ሂደቶች የግልጽ ጨረታ አሠራሮችን በመከተል የሚፈጸሙ ይሆናል፡፡

"ከዚህ በታች በንዑስ አንቀጽ 21.2፣21.3፣21.4፣21.5፣21.6፣21.7 በተገለጹት የመምረጫ ዘዴዎች ለሚፈጸሙ ግዥዎች የሚቀርብ የመጫረቻ ሠነድ በቴክኒክና በዋጋ ማቅረቢያ ተለይቶ በሁለት ኤንቨሎኘ ታሽጎ መቅረብ የሚኖርበት ሲሆን ለምክር አገልግሎቱ የሚዘጋጀው የመምረጫ መስፈርት እና የሚደረገው ግምገማ የሚከተለውን አሠራር ተከትሎ ይፈጸማል፡፡

21.2 በሚከናወነው የሥራ ጥራት እና በዋጋ ላይ የተመሠረተ መረጣ

21.2.1 ኮርፖሬሽኑ ለምክር አገልግሎት የጨረታ ሰነድ በሚያዘጋጅበት፣ በዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚቀርበውን እያንዳንዱን የቴክኒክ ሃሳብ በሚገመግምበት እና በሚያወዳድርበት ወቅት ከግምት ውስጥ ሊያስገባቸው ከሚገቡ መስፈርቶች መካከል፡-

ሀ. ከሚሰጠው ሥራ ጋር በተገናኘ አማካሪው ያለውን ልምድ፣

ለ. በሥራ ላይ እንዲውል የቀረበውን የጥናት ዘዴ ደረጃ፣

ሐ. ምክሩ ለኮርፖሬሽኑ የሚያስገኘውን ዕውቀት፣

መ. የውጭ ተወዳዳሪዎች በሚያቀርቧቸው የመወዳደሪያ ሃሳቦች ኢትዮጵያውያን ዜጐች በምክር ሥራው ሂደት በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ የሚኖሯቸው ተሳትፎ፣

21.2.2 በንዑስ አንቀፅ 21.2.1 ላይ ለተገለፁት መስፈርቶች ኮርፖሬሽኑ እንደሚገዛው የምክር አገልግሎት ዓይነት ለእያንዳንዱ መስፈርት ከዚህ በታች በተገለጸው መሠረት ነጥብ መስጠት ይኖርበታል፡፡

ሀ. የአማካሪው ልዩ ልምድ ........................................ከ20---50% ነጥብ

ለ. ሥራ ላይ ይውላል ተብሎ የቀረበው የምክር ዘዴ ............ከ5---100% ነጥብ

ሐ. ዕውቀት የማሸጋገር ችሎታ .................................. ከ5---10% ነጥብ

መ. በምክር አገልግሎቱ ለሚሳተፉ ቁልፍ ባለሙያዎች .........ከ30---60% ነጥብ

ሠ. የኢትዮጵያውያን ተሳትፎ .......................................ከ0---10% ነጥብ

21.2.3 በቴክኒክ ብቃት 70% ከመቶ ሰባ በታች ያገኙ ተወዳዳሪዎች ውድቅ ተደርገው 70% እና ከዚያ በላይ የሚያገኙት ተወዳዳሪዎች የዋጋ ማቅረቢያ ፖስታ ተጫራቾች በተገኙበት ይከፈታል፡፡

21.2.4 በቴክኒክ ብቃት ግምገማ ለዋጋ ውድድር የሚያበቃቸውን ዝቅተኛ ውጤት ያላመጡ ተጫራቾች የዋጋ ፖስታ ሳይከፈት እንዲመለስ መደረግ አለበት፡፡

21.2.5 የምክር አገልግሎቱ የሚገኘው ከውጭ አማካሪዎች ካልሆነ በስተቀር የአገር ውስጥ አማካሪዎች የሚያቀርቡት ዋጋ ለግምገማ ሲባል የአገር ውስጥ ታክስን ይጨምራል፡፡ ከዚህ በላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የአገር ውስጥ እና የውጭ አማካሪዎች የሚያቀርቡት ዋጋ የመጓጓዣ፣ የትርጉም፣ የፅሕፈት ሥራ ወጪን እና የመሳሰሉትን ሊጨምር ይችላል፡፡

21.2.6 ዝቅተኛ የመጫረቻ ዋጋ ላቀረበው ተወዳዳሪ ለዋጋ ሙሉ ነጥብ የሚሰጠው ሲሆን፣ በተነፃፃሪ ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበው ተወዳዳሪ አነስተኛ ነጥብ ይሰጣል ሌሎች

ተወዳዳሪዎችም የሚያገኙት ነጥብ ባቀረቡት ዋጋ ላይ በመመስረት ተሰልቶ የሚወሰን ይሆናል፡፡

21.2.7 የቴክኒክ ግምገማ የነጥብ ድርሻ 70% (ሰባ በመቶ)፣ የዋጋ ግምገማ የነጥብ ድርሻ ደግሞ 30% (ሰላሳ በመቶ) ይሆናል፡

21.2.8 ለቴክኒክ ብቃት ደረጃ እና ለዋጋ የተሰጡት ነጥቦች በማዳመር በአጠቃላይ ውጤት ከፍተኛ ነጥብ ያገኘው ተወዳዳሪ የጨረታው አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል፡፡

21.2.9 በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የሚፈፀም የምክር አገልግሎት ግዥ በዚህ መመሪያ ክፍል ሦስት የተገለጸውን የግዥ አፈጻጸም ሂደት በተጨማሪነት መሠረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

21.3 ጥራት ላይ የተመሰረተ መረጣ

21.3.1 በሥራ ጥራት ላይ የተመሰረተ መረጣ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የምክር አገልግሎቱ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ሲያሟላ ይሆናል፡፡

ሀ. የምክር አገልግሎቱ ውስብስብና የተለየ የሙያ ብቃት የሚጠይቅ በመሆኑ ለዚሁ ግዥ የተሟሉ ማጣቀሻ ሠነድ ወይም ቢጋር ማዘጋጀት የማይቻል ሲሆን ወይም ከአማካሪ የሚገኘውን የምክር አገልግሎት ዓይነት ለይቶ ማወቅ የማይቻል ሲሆን ወይም አማካሪው የራሱን የፈጠራ ችሎታ ተጠቅሞ የመወዳደሪያ ሃሳብ ማቅረብ የሚኖርበት ሲሆን፣

ለ. ከፍተኛ ችሎታ ያላቸውን አማካሪዎች ማግኘት አስፈላጊ በሚሆንባቸው እና የወደፊት ውጤታቸው አሳሳቢ የሚሆን ከፍተኛ ጉዳዮች ሲሆኑ፣

ሐ. የምክር አገልግሎቱ በተለያዩ አማራጭ መንገዶች ሊቀርብ የሚችል በመሆኑ ምክንያት የሚቀርቡትን ሃሳቦች በተመሣሣይ ሁኔታ ማወዳደር አስቸጋሪ እንደሚሆን ሲታመን፡፡

መ. የቴክኒክ ሀሳቦችን የያዙ ፖስታዎች ተጫራቾች በተገኙበት እንዲከፈቱ ይደረጋል፡፡

ሠ. በቴክኒክ ግምገማ ከፍተኛ ውጤት ያገኘው ተጫራች የጨረታው አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል፡

ረ. በዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል ተራ “ሠ” የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በውድድሩ አሸናፊ የሆነው ተጫራች ያቀረበው ዋጋ ከኮርፖሬሽኑ የመክፈል አቅም በላይ ከሆነና በድርድር በበጀቱ መሥራት ካልቻለ በቴክኒክ ግምገማው ውጤት ሁለተኛ የወጣው ተጫራች ያቀረበው ዋጋ ከኮርፖሬሽኑ የመክፈል አቅም ጋር የሚመጣጠን ከሆነ ግዥውን ሁለተኛ ከወጣው ተጫራች መፈፀም ይቻላል፡፡

ሰ. በጨረታው አሸናፊ ከሆነው ተጫራች ጋር የውል ስምምነት እንደተፈረመ የሌሎች ተወዳዳሪዎች የዋጋ ማቅረቢያ ፖስታ ሳይከፈት ለተጫራቾቹ ተመላሽ መደረግ አለበት፡፡

21.4 በቁርጥ በጀት ላይ ተመስርቶ የሚከናወን መረጣ

ሀ. በቁርጥ በጀት ላይ ተመስርቶ የሚከናወን መረጣ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የሚፈለገው የምክር አገልግሎት ውስብስብነት የሌለው፤ በትክክል ሊገለፅ የሚችል ሲሆን እና ለዚሁ ተግባር የተፈቀደው በጀት ጣሪያ ከሆነ ነው፡፡

ለ. የቴክኒክ ሀሳቦችን የያዙ ኤንቬሎፖች ተጫራቾች በተገኙበት እንዲከፈቱ ይደረጋል፡፡

ሐ. የቴክኒክ ግምገማው በንዑስ አንቀጽ 21.2.1፣21.2.2፣21.2.3፣21.2.4 ላይ የተመለከቱትን ሥርዓቶች ተከትሎ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

መ. በቴክኒክ ግምገማው ተፈላጊውን መስፈርት ያሟሉት ተጫራቾች የዋጋ ማቅረቢያ ኤንቬሎፕ ተጫራች የቀረበውን ዋጋ በመክፈቻው ሥነ-ስርዓት ላይ የተገኙ ተጫራቾች እንዲያውቁ መደረግ አለበት፡፡

ሠ. ለጨረታው ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በላይ ያቀረቡት ተጫራቾች ከጨረታው ውጭ እንዲሆኑ ይደረጋል፤

ረ. ለጨረታው ከተፉቀደው የገንዘብ መጠን ያልበለጠ ዋጋ ያቀረበና በአጠቃላይ ውጤት ከፍተኛ ነጥብ ያገኘ ተጫራች የውድድሩ አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል፤ እንደአስፈላጊነቱም ዋጋን ያልጨመረ ድርድር ሊደረግ ይችላል፡፡

21.5 በዝቅተኛ ዋጋ ላይ የተመሠረተ መረጣ

21.5.1 በዝቅተኛ ዋጋ ላይ የተመሠረተ መረጣ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የሚገዛው የምክር አገልግሎት የባለሙያውን ልዩ ችሎታ የማይጠይቅ፣ ውስብስብ ያልሆነና ስታንዳርድ ያለው ወይም በተመሳሳይና ወጥ በሆነ አሠራር ሊከናወን የሚችል ሲሆን ነው፡፡

21.5.2 ኮርፖሬሽኑ በዚህ የመረጣ ዘዴ ተጫራቾችን ለመገምገም ሲፈልግ ዝቅተኛውን የቴክኒክ መመዘኛ ነጥብ በመወሰን ከአቅራቢዎች ዝርዝር ለተመረጡት ተጫራቾች በሚሰጠው ሃሳብ መጠየቂያ ሰነድ ላይ ይህንኑ ነጥብ በግልፅ ማመልከት አለበት፡፡

21.5.3 የቴክኒክ ሀሳቦችን የያዙ ፖስታዎች ተጫራቾች በተገኙበት እንዲከፈቱ በማድረግ የቴክኒክ ግምገማው መከናወን ይኖርበታል፡፡

21.5.4 በግምገማው ውጤት ለቴክኒክ ብቃት የተቀመጠውን ዝቅተኛ መስፈርት ያላሟሉ ተወዳዳሪዎች ከጨረታው ውጭ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

21.5.5 በቴክኒክ ብቃት ግምገማ ለውድድር የሚያበቃቸውን ዝቅተኛ ውጤት ያላመጡ ተጫራቾች የዋጋ ኤንቨሎኘ ሳይከፈት እንዲመለስ መደረግ አለበት፡፡በቴክኒክ ግምገማው ውጤታቸው ለዋጋ ውድድር ያለፉት ተወዳዳሪዎች የዋጋ ኤንቬሎኘ ተጫራቾች በተገኙበት እንዲከፈት ይደረጋል፡፡ ለጨረታው በእያንዳንዱ ተጫራች የቀረበውን ዋጋ በመክፈቻው ሥነ-ሥርዓት ላይ የተገኙ ተጫራቾች እንዲያውቁ መደረግ አለበት፡፡

21.5.6 በቴክኒክ ግምገማ ለብቃት ማረጋገጫ የተቀመጠውን ዝቅተኛ መስፈርት ካሟሉት ተወዳዳሪዎች መካከል አነስተኛ ዋጋ የሰጠው ተጫራች የውድድሩ አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል፡፡

21.6 በአማካሪዎች ብቃት ላይ የተመሰረተ መረጣ

ሀ. በአማካሪዎች ብቃት ላይ የተመሰረተ መረጣ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው ለአማካሪው የሚሰጠው ሥራ አነስተኛ በመሆኑ ምክንያት የመወዳደሪያ ሃሳቦችን ለማዘጋጀት እና ለመገምገም የሚያስፈልገው ጊዜና ወጪ ከሥራው ጋር የማይመጣጠን ሲሆን ነው፡፡

ለ. ይህ ዘዴ ጥቅም ላይ የሚውለው የምክር አገልግሎቱ ወጪ ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ) የማይበልጥ በሚሆንበት ጊዜ ብቻ ነው፡፡

ሐ. ለዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚዘጋጀው ማጣቀሻ /ቢ.ጋር/ አማካሪው ያለውን የሥራ ልምድና የብቃት ደረጃ እንዲገልጽ የሚጠይቅ መሆን አለበት፡፡

መ. ከአቅራቢዎች ዝርዝር ወይም ኮርፖሬሽኑ ያለውን ደረጃ በመጠቀም በውድድሩ እንዲሳተፉ በመረጣቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች የቀረበውን መረጃ መሰረት በማድረግ በሚከናወን ግምገማ የተሻለ ሆኖ የተመረጠው እጩ ተወዳዳሪ የቴክኒክና የዋጋ ማቅረቢያ ሃሳቡን በአንድ ላይ እንዲያቀርብ በማድረግና በመደራደር በሚደረስበት ስምምነት መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

21.7 አንድ አማካሪ የሚመረጥበት ሁኔታ

ኮርፖሬሽኑ የምክር አገልግሎት ግዥን ከአንድ አማካሪ ሊፈጽም የሚችለው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 19 የተገለጹት ሁኔታዎች መሟላታቸው ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

## 22. <u>በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ</u>

22.1. ኮርፖሬሽኑ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች ዕቃዎችን እና አገልግሎቶችን እንደአስፈላጊነቱ በአገር አቀፍና በዓለም አቀፍ የሁለት ደረጃ ጨረታ አወዳድሮ ግዥ ሊፈፅም ይችላል፡፡

ሀ. ለሚገዙ ዕቃዎች፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች የምክርና ሌሎች አገልግሎቶች በቂ ዝርዝር የፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት በኮርፖሬሽኑ ደረጃ የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ወይም አገልግሎቶችን በሚመለከት ባህሪያቸውን ለይቶ ለማሳየት የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ እና ኮርፖሬሽኑ የግዥ ፍላጎቱን በበቂ ሁኔታለማሟላ የሚያስችል መፍትሔ ለመፈለግ፤

ለ. ግልፅ ጨረታ እንዲወጣ ተደርጎ በሚገዙ ዕቃዎች፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች፣ የምክርና ሌሎች አገልግሎቶች ባህርይ ወይም ተፈጥሮ ግልፅ አለመሆን ወይም ውስብስብነት ምክንያት ተጫራቾች ያልቀረቡ እንደሆነ ወይም የቀረቡት ተጫራቾች የመወዳደሪያ ሃሳብ ውድቅ ሲደረግ እና ይህም የሆነው ኮርፖሬሽኑ የተሟላ ዝርዝር ማዘጋጀት ባለመቻሉ መሆኑ ሲታመን፤

ሐ. ኮርፖሬሽኑ የምርምር፣ የሙከራ፣ የጥናት እና የልማት ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስችል ውል መፈጸም ሲፈልግ፣

መ. በሚገዙ ዕቃዎች፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች፣ የምክርና ሌሎች አገልግሎቶች ባህርይ ወይም ተፈጥሮ ውስብስብነት ምክንያት ከአቅራቢዎች ጋር ድርድር ማድረግ ሲያስፈልግ፣

22.2 የሁለት ደረጃ የግዥ ዘዴው የሥራ ፍሰት ለብሔራዊ ግልፅ ጨረታ የግዥ ዘዴ የተዘረጋውን ሥርዓት የሚከተል ሲሆን በተጨማሪ የሚከተሉትን የስራ ፍሰቶች ያካትታል፡፡

ሀ. የጨረታ ጥሪው የሁለት ደረጃ ጨረታ ግዥ መሆኑን መግለፅ ይኖርበታል፡፡

ለ. በመጀመሪያው ዙር ጨረታ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የጨረታ ዋስትና እንዲያቀርቡ አይጠየቁም፡፡

ሐ. በመጀመሪያ ዙር የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ የኮርፖሬሽኑን አጠቃላይ ፍላጎት የሚገልፅ ሆኖ አላማው ከዕጩ ተወዳዳሪዎች በሚቀርቡ ኃሳቦች መሠረት ዝርዝር የፍላጎት መግለጫ ለማዘጋጀት የሚያስችል መሆን ይኖርበታል፡፡ ለዚህም ሰነድ አስፈላጊ ናቸው የሚባሉትን መጠይቆች እና መግለጫዎች ማካተት ይኖርበታል፡፡

መ. የጨረታ ሠነዱ በመጀመሪያው ደረጃ ተጫራቾች ዋጋን ያልጨመረ የመወዳደሪያ ሃሳብ እንዲያቀርቡ የሚጋብዝ ሲሆን ተጫራቾች ከቴክኒክ ጋር ግንኙነት ያላቸው መግለጫዎች፣ ጥራት፣ የዕቃውን ወይም የአገልግሎቱን ሌሎች ባህሪያት፣ የአቅርቦቱን የውል ቃሎችና ሁኔታዎች፣ የአቅራቢዎቹን የሙያ፣ የቴክኒክ ችሎታና ሌሎችንም ሁኔታዎች በጨረታው ሃሳብ እንዲካተቱ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

ሠ. በመጀመሪያው ዙር ጨረታ ላይ የተጫራቾች መገኘት ሳያስፈልግ በዕጩ ተወዳዳሪዎች የቀረበው የቴክኒክ ሐሳብ ማቅረቢያ ሰነድ በጨረታ ጥሪው በተገለፀው ሁኔታ እንዲከፈት ይደረጋል፡፡

ረ. የመጀመሪያው ዙር ግምገማ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች የቀረበውን ሃሳብ በመመርመር ለሁለተኛው ዙር ጨረታ የሚያገለግለውን የፍላጎት መግለጫ እና በጨረታው ሊሳተፉ የሚገባቸውን ተጫራቾች መለየት የሚያስችል መሆን ይኖርበታል፡፡

ሰ. ከላይ በፊደል ተራ "ረ" የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በግምገማው ወቅት ከተወሰኑ ወይም ከአንድ ከተለየ እጩ ተወዳዳሪ ጋር ኮርፖሬሽኑ ውይይት ሊያደርግ እና ተጨማሪ መረጃዎችና ማብራሪያዎች ሊጠይቅ ይችላል፤

ሸ. ከላይ በፊደል ተራ "ሰ" በተገለፀው መሰረት የሚደረገው ውይይት እጩ ተወዳዳሪዎች የሰጡትን ሐሳብ ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ እና የተሻለ የዳበረ ሐሳብ ለማመንጨት ያለመ ሊሆን ይገባል፤

ቀ. ከላይ በፊደል ተራ "ሸ" ላይ በተገለፀው መሰረት የሚደረገው ውይይት ኮርፖሬሽኑ በሁለተኛው ዙር ለመሳተፍ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ማሟላት ይኖርባቸዋል ያላቸውን እና ዕጩ ተወዳዳሪ ያላሟላውን ዝቅተኛ መስፈርት እንዲያሟላ ለማድረግ መሆን የለበትም፡፡

በ. በሁለተኛው ዙር የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ እስከተቻለ ድረስ ለግልፅ ጨረታ የተገለፀውን አሠራር መከተል የሚኖርበት ሲሆን በተጨማሪም የጨረታ ዋስትና መጠን ተሰልቶ ለሁለተኛው ዙር ጨረታ እንዲሳተፉ የተመረጡት ዕጩ ተወዳዳሪዎች እንዲያቀርቡ መጠየቅ ይኖርባቸዋል፡፡

ተ. በመጀመሪያው ዙር ተቀባይነት ያገኙ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሁለተኛው ዙርውድድር እንዲሳተፉ ጥሪ የሚደረግላቸው ሲሆን፣ የጨረታ ዋስትና እንዲያቀርቡም ይደረጋል፡፡

ቸ. ከዕጩ ተወዳዳሪዎች የተገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ ኮርፖሬሽኑ የመጨረሻውን የመወዳዳሪያ ሃሣብ ሲያዘጋጁ በመጀመሪያው የጨረታ ሠነድ ውስጥ ከተቀመጡት ማናቸውም የዕቃው፣ የግንባታ ሥራው የምክር ወይም ሌሎች አገልግሎቶች የቴክኒክ ወይም የጥራት ባህሪያት እና ሠነዶቹን ለመገምገም እና ለማወዳደር እንዲሁም አሸናፊውን ለመምረጥ ከተቀመጡት

መስፈርቶች ውስጥ ማናቸውንም ለመሠረዝ፣ ለማሻሻል ወይም ከዚህ መመሪያ ጋር የሚስማሙ አዳዲስ ባህሪያትንና መስፈርቶችን ለመጨመር ይችላል፡፡

አ. ኮርፖሬሽኑ የመጀመሪያ ደረጃ ሃሣባቸው ተቀባይነት ያገኘ ተጫራቾችንየመጨረሻውን የመወዳደሪያ ሃሣብን መሠረት ያደረገ ዋጋ እንዲያቀርቡ ይጋብዛል፡፡ ማናቸውም ሥራዎች፣ ማሻሻያዎች ወይም ጭማሪዎች የመጨረሻው የመወዳደሪያ ሃሳብ እንዲቀርብ በሚተላለፈው ጥሪ ውስጥ ለኮርፖሬሽኑ ተጫራቾች መገለጽ አለባቸው፡፡

ከ. ኮርፖሬሽኑ ለሁለተኛው ዙር የተዘጋጀውን የጨረታ ሠነድ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች መላክ ወይንም ዕጩ ተወዳዳሪዎች ቀርበው እንዲወስዱ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

ዐ. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 22.2 ፊደል ተራ “ሸ” ላይ በተገለጸው መሰረት ለዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚተላለፈው ጥሪ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የጨረታ ሠነዱን ለመውሰድ ሊያሟሉ የሚገባቸውን ሁኔታዎች በግልጽ ሊያመለክት ይገባል፡፡

ነ. በሁለተኛው ዙር ጨረታ የጨረታ መወዳደሪያ ሃሳብ ለማቅረብ ያልፈለገ ማንኛውምተጫራች ከጨረታው ውድድር ራሱን ሊያገል ይችላል፡፡

ኘ. ኮርፖሬሽኑ በጨረታው የመጨረሻ ደረጃ ግምገማ ላይ ከፍተኛ ውጤት ካገኙ ተጫራቾች ጋር እንደ ውጤታቸው ቅደም ተከተል ድርድር ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 23. <u>የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ የሚፈጸም ግዢ</u>

23.1. ኮርፖሬሽኑ ግዥው ከሚኖረው የተለየ ባሕርይ አንፃር በቅድሚያ የተወዳዳሪዎችን ብቃት መሰረት በማድረግ ግምገማ ማድረግ አለብኝ ብሎ ሲያምን እንደግዥው አይነት ብሔራዊ ወይም ዓለም አቀፍ የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ ሊያወጣ ይችላል፡፡

23.2 የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ የሚያስፈልጋቸው ግዥዎች ከሚከተሉት ሁኔታዎች ቢያንስ አንዱን የሚያሟሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

ሀ. ከፍተኛ ዋጋ ያለው ወይም በባህሪው ውስብስብ የሆነ የዲዛይን፣ የማምረትና የተከላ ሥራ በአንድ ድርጅት መጠናቀቅ ያለበት የግንባታ የማምረቻ መሳሪያ ወይም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ግዥ ሲሆን፣ ወይም

ለ. የሚቀርበው እቃ ወይም መሳሪያ ጥራትና ጠቀሜታ ከፍተኛ ተፈላጊነት ያለው እና የተከላ አገልግሎትን ያካተተ ሲሆን፣ ወይም

ሐ. የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ግዥ በመሆኑ ብቃታቸው በቅድመ ብቃት ምዘና የሚረጋገጥ ተጫራቾች ብቻ በውድድሩ ተካፋይ መሆን እንደሚገባቸው ሲታመንበት፡፡

23.3 ጨረታው የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ ጥሪ መሆኑ በማስታወቂያው ላይ መገለጽ ይኖርበታል፡፡

23.4 የቅድመ ብቃት ግምገማ ለማድረግ የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ የቅድመ ብቃት ጨረታ በኮርፖሬሽኑ የተዘጋጀውን የቅድመ ብቃት ጨረታ መደበኛ የጨረታ ሠነድ መሰረት በማድረግ ይሆናል፡፡ የቅድመ ብቃት መምረጫ መስፈርት እንደግዥው ባህሪና ዓይነት ሊለያይ የሚችል ቢሆንም ተወዳዳሪ ድርጅቶቹ እንዲያቀርቡ የሚጠየቁት ማስረጃ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማካተት ይኖርበታል፡፡

ሀ. በተመሳሳይ ስራ ወይም እቃ ማምረት ላይ ድርጅቱ ያለው ልምድ፣

ለ. ድርጅቱ ሥራውን ለማከናወን ወይም እቃውን ለማምረት የሚያስችል በቂ የሰው ኃይል፣ መሣሪያ፣ የማምረቻ መሳሪያ ብዛት እና የተሟላ መሰረተ ልማት ያለው መሆኑን፣

ሐ. ድርጅቱ አሁን በመስራት ላይ ያለው የግንባታ ሥራ ወይም በማምረት ላይ ያለው እቃ ብዛት ወይም መጠን፣

መ. ድርጅቱ የውል ግዴታውን ለማጠናቀቅ የሚያስችል በቂ የገንዘብ አቅም እና መልካም ዝና ያለው መሆኑን፡፡

23.5 የተጫራቾች ግምገማ የሚከናወነው ለቅድመ ብቃት ማረጋገጫ በኮርፖሬሽኑ የተዘጋጀውን መስፈርት መሰረት በማድረግ ይሆናል፡፡

23.6 ለቅድመ ብቃት ውድድሩ ያመለከቱ ተጫራቾች በሙሉ የግምገማ መስፈርቱን እስካሟሉ ድረስ ምንም ዓይነት የቁጥር ገደብ ሳይደረግ በሚቀጥለው ውድድር እንዲሳተፉ መደረግ አለበት፡፡

23.7 ኮርፖሬሽኑ በቅድመ ብቃት ውድድር የሚሳተፉ ድርጅቶች በሽርክና ወይም በጋራ መወዳደር እንዲችሉ ሊፈቅድ ይችላል፡፡ ሆኖም የቅድመ ብቃት ውድድሩን በግል ያለፉ ተወዳዳሪዎች በግዥው ሂደት የሚኖራቸውን ዉድድር እንደሚያጠብ በኮርፖሬሽኑ ካልታመነ በስተቀር በጋራ ወይም በሽርክና የመጫረቻ ሰነዱን እንዲያቀርቡ መፈቀድ የለበትም፡፡

23.8 በንዑስ አንቀጽ 23.6 የተገለጸው የተጠበቀ ሆኖ በጋራ ወይም በሽርክና ለቅድመ ብቃቱ ውድድር ቀርበው ይህንኑ መሠረት በማድረግ በተካሄደ ግምገማ ለሚቀጥለው ጨረታ ያለፉና የተመረጡ ተጫራቾች በጨረታው በግል እንዲወዳደሩ አይፈቀድላቸውም፡

23.9 የቅድመ ብቃቱ ግምገማ ውጤቱ እንደታወቀና በኮርፖሬሽኑ ተቀባይነት እንዳገኘ ውጤቱ በጨረታው እንዲሳተፉ ለተመረጡትና ላልተመረጡት ተጫራቾች በእኩል ሁኔታ ሊገለጽላቸው ይገባል፡፡

23.10 አንድ ተጫራች በጨረታው ግምገማ አሸናፊ ለመሆን ቢችልም ለቅድመ ብቃትውድድር የሰጠው መረጃ የተሳሳተ ከሆነ ወይም በቅድመ ብቃት ውድድሩ ወቅት የነበረው ብቃት ባለመኖሩ ውሉን የሚጠበቅበት ሁኔታ ለመፈጸም አለመቻሉ በበቂ ሁኔታ ከተረጋገጠ ኮርፖሬሽኑ ድርጅቱ ውሉን እንዲፈርም ላይፈቅድ ይችላል፡፡

23.11 በዚህ መመሪያ ለብሔራዊ ወይም ለአለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የተመለከተውን ስርዓት በመከተል የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ በቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ውድድሩ ተቀባይነት ላገኙት ተጫራቾች በየአድራሻቸው እንዲላክላቸው ወይም ወደ ኮርፖሬሽኑ ቀርበው እንዲወስዱ የሚደረግ ሲሆን ቀሪው የግዥ አፈፃፀም ስርዓት በዚህ መመሪያ የተደነገገውን አሰራር ተከትሎ ይፈጸማል፡፡

## 24. <u>በቁርጥ ዋጋ ላይ ተመስርቶ የሚከናወን ግዥ</u>

24.1. የኮርፖሬሽኑ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት እስካረጋገጠ ድረስ በቁርጥ ዋጋ ግዥዎችን መፈፀም ይቻላል፡፡

24.2. የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችና ማሽነሪዎች፣ የግንባታ ሥራዎች በተናጠል ወይም በጥቅል፣ የግንባታ ሙያተኞች፣ የቀን ሠራተኞች እንዲሁም ልዩ ልዩ የምህንድስና ሙያተኞች ግዥ በቁርጥ ዋጋ ሊፈፀም ይችላል፡፡

24.3. ኮርፖሬሽኑ የሚገኙ የሥራ ክፍሎች በቁርጥ ዋጋ ለሚያሠራቸው ግንባታዎችና ሥራዎች ተገቢነት ያለው ነጠላ ዋጋ ለመወሰን ዝርዝር ወቅታዊ የገበያዋጋ ጥናት በማካሄድ በኮርፓሬት ዘርፍ ም/ በዋና ሥራ አስፈፃሚ ማፀደቅ አለበት፡፡

24.4. በቁርጥ ዋጋ ላይ ተመስርቶ የሚከናወን ግዥ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የሚፈለገው የምክር ወይም የግንባታ አገልግሎት ውስብስብነት የሌለው፣ በትክክል ሊገለፅ የሚችል ሲሆን እና ለዚሁ ተግባር የተፈቀደው በጀት ያለው ከሆነ ነው፡፡

24.5. ተጫራቾች ያቀረቡት የቴክኒክና የዋጋ የመወዳደሪያ ሃሣብ ዝርዝር ትንታኔ ተካሂደ ከዝቅተኛው ወደ ከፍተኛው በቅደም ተከተል ይለያሉ፡፡ ሆኖም ተጫራቾ የሚያቀርቡት ዋጋ የሚውለው ለውድድር ብቻ ነው፡፡

24.6. በቴክኒክ እና በዋጋ ግምገማው ተፈላጊውን መስፈርት ያሟሉት ተጫራቾች በኮርፖሬሽኑ ተዘጋጅቶ በፀደቀው ቁርጥ ዋጋ የኘሮጀክት ምህንድስና ግምት ኤንቬሎኘ ተጫራቾች በተገኙበት እንዲከፈት ይደረጋል፡፡

24.7. የቁርጥ ነጠላ ዋጋው ላይ ተጫራቾች የራሳቸውን የዋጋ መወዳደሪያ ሃሣብ ማቅረብ አይችሉም፡፡

24.8. በቅደም ተከተል የተሻለ የሆነው ተጫራች በተቆረጠው ቁርጥ ዋጋ እንዲሠራ አሸናፊ ተደርጐ ይመረጣል፡፡ ፈቃደኛ ካልሆነ በቅደም ተከተል ወደ ሚቀጥለው ተጫራች ፈቃደኝነቱን በመጠየቅ አሸናፊውን መምረጥ ይቻላል፡፡ እንደ አስፈላጊነቱም ዋጋን ያልጨመረ ድርድር ሊደረግ ይችላል፡፡

24.9. ተጫራቾች ያቀረቡት ዋጋ ከትንታኔ በኋላ ከቁርጥ ዋጋው በሚኖረው ልዩነት (Range) ቅደም ተከተል ይለያል፡፡ እንደ ሥራው መጠን ኘሮጀክቱ በምደባ በቁርጥ ነጠላ ዋጋው ላይ በተመሠረተ ኮንትራት ውለታ እንዲፈፀም ይደረጋል፡፡

## 25. <u>በማዕቀፍ ውል የሚፈፀም ግዥ</u>

25.1. በኮርፖሬሽኑ ዋና መ/ቤት እና በቅርንጫፎች በጋራ የሚፈለግ ዕቃና አገልግሎት ግዢ የሚፈፀመው የማዕቀፍ ስምምነት መሠረት በማድረግ ሲሆን የሚከተሉተን አሠራሮች ተከትሎ መፈፀም ይኖርበታል፡፡

ሀ. በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችን አገልግሎቶች በመለየት ዝርዝር ያወጣል ፡ ዝርዝሩን በየጊዜው ያዳብራል ፣ እንዲሁም ለቅርንጫፎች ያሳውቃል፡፡

ለ. በኮርፖሬሽኑ ዋና መ/ቤት እና በቅርንጫፎች የግዥ ፍላጎት በማሰባሰብ የግዢ ዕቅድ ከተያዘለት በጀት ጋር አጠናቅሮ ለግዥ ፈፃሚ አካል ያቀርባል፡፡ ግዥ ፈፃሚ አካል ያዘጋጀውንም ዕቅድ በኮርፖሬሽኑ የሥራ አመራር ኮሚቴ በማፀደቅ የግዥውን ዕቅድ ለኮርፖሬሽኑ ዋና መ/ቤት እና ለቅርንጫፎች ያሳውቃል፡፡

25.2. የማዕቀፍ ግዥ የሚፈጸመው የኮርፖሬሽኑ ግዥ ፈፃሚ አካል የሚከተሉት ተጨማሪ ዝርዝሮች ያካተተ የግዥ ማስታወቂያ ማውጣት አለበት፡፡

ሀ. የማስታወቂያው ጥሪ የተደረገው የማዕቀፍ ግዥ ለመፈጸም እንዲቻል መሆኑን ፤

ለ. በማዕቀፍ ስምምነቱ የሚፈፀመው ግዥ አይነት ግመታዊ መጠን እና የርክክብ ሁኔታ፤

ሐ. የማዕቀፍ ስምምነቱ የሚቆይበት ጊዜ፤

መ. በማዕቀፍ ስምምነቱ የሚጠቀሙትን በዋና መ/ቤት የሚገኙ የስራ ክፍሎች፣ ቅርንጫፎችና ዝርዝር የማስረከቢያ ቦታ እና እስከተቻለ ጊዜ ግምታዊ የማስረከቢያ ጊዜ ፤

ሠ. በማዕቀፍ ስምምነቱ የግዥ ትዕዛዝ የሚተላለፍበትን፤ ርክክብ የሚደረግበትን ክፍያ የሚፈጸምበትን እና ክትትል የሚደረግበትን ሥርዓት

25.3. የግዢው ዘዴ የግልጽ ጨረታ ወይም የውስን ጨረታ ፍሰቶችን የሚከተል ሲሆን በኮርፖሬሽን ደረጃ በቂና ግልጽ የሆነ የውስጥ አደረጃጀት በመፍጠር የጨረታ ሰነድ በማዘጋጀት፣ የመገመገም፣ የማጽደቅ እና ውል የማስተዳደር ሥራዎችን በተለያዩ አካላት እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡

25.4. ቅርንጫፎች የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጸም በኮርፖሬሽኑ ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የተላለፈላቸውን የማዕቀፍ ስምምነት ቅጺ በመጠቀም በውሉ ላይ የተገፁትን አቅርቦቶች ለመግዛት የሚያስችል የግዥ ትዕዛዝ ለማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው ያስተላልፋሉ፡፡ ቅርንጫፎች ተገቢ ሆኖ ሲያገኙት የማዕቀፍ ስምምነት ግዢ እንዲፈጸም ከኮርፖሬሽኑ ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ጋር በመመካከር ተጨማሪ ትዕዛዝ ለአቅራቢው ማስተላለፍ ይችላሉ ፡፡

25.5. የግዥ ትዕዛዙ ወይም ተጨማሪው የግዥ ትዕዛዝ በአጠቃላይ ውሉ ውስጥ የተካተቱ መሠረታዊ የሆኑ ዋጋ እና ሌሎች የውል ሁኔታዎችን አይለውጥም ሆኖም፣ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሚከተሉት እና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ከማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው ጋር ሊስማሙ ይችላሉ፡፡

ሀ. ዕቃው የሚቀርብበትን እና ክፍያ የሚፈጸምበትን ጊዜ ለማሳጠር

ለ. በአንድ ግዥ ትዕዛዝ የሚቀርበውን ዕቃ ብዛት ለመወሰን ፤

ሐ. ዕቃው የሚቀርብበትን ቦታ ለማሳወቅ ወይም ለመቀየር

25.6. በማዕቀፍ ስምምነቱ አፈፃፀም ወቅት ቅርንጫፎችና የሚከተሉትን አሠራሮች መከተለ ይኖርባቸዋል፡፡

ሀ. የግዥ ትዕዛዙን የሚሰጡት በማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ለሚፈጽሙ የኮርፖሬሽኑ አካል የገለፁትን ፍላጎት መሠረት በማድረግ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥው የተፈፀመው ዕቃ ብቻ መሆኑን ማረጋገጥ ፣

ለ. በማዕቀፍ ስምምነቱ ውስጥ የተገለፁ ቅርንጫፎች እና የሚፈፀሙ ግዴታዎች በስምምነቱ መሠረት የተፈፀመ መሆኑን ማረጋገጥ

ሐ. በውሉ ላይ የሚነሱ አጨቃጫቂ ጉዳዮችን የማዕቀፍ ስምምነት ከሚያስተዳድረው ኮርፖሬት ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ጋር በጋራ በመሆኑ ለመፍታት ጥረት ማድረግ፣

መ. የማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው በዋና ዋና ክፈለ ጉደዮች ማለትም የዕቃ ጥራት እና መጠን ማጓደል፣ የማቅረቢያ ጊዜ አለመጠበቅ፣ በአስተሻሸግ እና በመሳሰሉ የፈፀማቸውን ጥፋቶች የማዕቀፍ ስምምነቱን ለሚያስተዳድረው ኮርፖሬት ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በወቅቱ በጽሑፍ ማሳወቅ

ሠ. በማዕቀፍ ስምምነት ለተካተቱ ፍላጎቶቻቸው የግዥ ትዕዛዝ የሚቀርብበት መጠንና ጊዜ መለየትና ግዥውን የሚፈጽመውን አካል ስለአፈፃፀሙ ማማከር፣

25.7. በኮርፖሬሽኑግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬትና በቅርንጫፍጽ/ቤቶች ሥራ እንዳይጓተት የማዕቀፍ ስምምነት በወቅቱ መፈረም የሚኖርበት ሲሆን ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በወቅቱ የማዕቀፍ ስምምነት ሊፈረም አለመቻሉን ካረጋገጠላቸው፣ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚኖራቸውን ፍላጎት በዚህ መመሪያ የተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎችን በመጠበቅ መግዛት ይችላሉ፡፡

25.8. ኮርፖሬሽኑ ከሚከተሉት በአንድ ምክንያት የማዕቀፍ ስምምነቱን ሊሰርዝ ይችላል፡፡

ሀ. የማዕቀፍ ስምምነቱ አቅራቢ በውሉ መሠረት ግዴታውን አለመወጣቱ፣

ለ. ቅርንጫፎች  የግዥ ፍላጎት በግልጽ በታወቀ ምክንያት ሲለወጥ፣

ሐ. የተደረገው የማዕቀፍ ስምምነት ዋጋ፣ ሌሎች ሁኔታዎች እንዲሁም የገበያው ነባራዊ ሁኔታ ሲታይ ኮርፖሬሽኑ ሊጎዳ የሚችል ሰፊ ልዩነት መኖሩ ሲረጋገጥ ፣

መ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ /ሀ/እና /ለ/ መሠረት የማዕቀፍ ስምምነት እንዲቋረጥ ሲወሰን የማዕቀፍ ስምምነቱ የሚቋረጥበት ምክንያት እና ተፈፃሚ የሚሆንበትን ቀን በመግለጽ የአንድ ወር ቅደሚያ ማስጠንቀቂያ ለማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው በጽሁፈ መስጠት አለበት፡፡

ሠ. የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ጊዜ እስከሚጠናቀቅ በውሉ ላይ የተገለፁት የኮረፖሬሽኑ አካላት ግዥውን ከሌላ አቅራቢ መፈጸም አይችሉም፡፡

## 26. <u>የፕሮጀክት ማኔጅመንት አገልግሎት</u>

የኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም እርሱ በሚወክለው የፕሮጀክት ማኔጅመንት አገልግሎት በተሟላ መንገድ መስጠት የሚያስችሉ ዓለም አቀፍ የፕሮጀክት አተገባበር ዘዴዎች በማጣጣም የዲዛይን ፈጠራ ውድድር (Design Competition) የዲዛይን ቢዩልድ (DB) ፣ የጥናት ግዥና ኮንትራት (EPC) ፣ ግንባታ በባለቤትነት (ኦፐሬሽንና ማስተላለፍ (BOOT/BOT) እና መሰል የግንባታና የምህንድስና አገልግሎቶች በዚህ መመሪያ እንዲሰጥ ተፈቅዷል፤

# ክፍል አራት

## የውል አስተዳደር

### 27. የውል ሁኔታዎች

27.1. የውሉ ሠነድ የሥራውን ስፋት፣ መቅረብ ያለባቸውን ዕቃዎች እና መስጠት ያለባቸውን አገልግሎቶች፣ የኮርፖሬሽኑና የአቅራቢውን መብትና ግዴታ፣ የኮንስትራክሽን ሥራውን ቁጥጥርና አስተዳደር የሚያግዙ የኮርፖሬሽኑ የምህንድስና ባለሞያዎች ቀጥሮ ከሆነ የእነዚህን ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ የሚያሳይ መሆን አለበት፡፡ ከውሉ ጠቅላላ ሁኔታዎች በተጨማሪ ከሚገዛው ዕቃ ወይም አገልግሎት የተለየ ባህርይ ጋር የሚሄዱ ልዩ ሁኔታዎችን እና ፕሮጀክቱ የሚከናወንበትን ቦታ የሚያመለክት መሆን አለበት፤

27.2. የውል ቃሎችና ሁኔታዎች ረቂቅ ከጨረታ ሰነድ ጋር አንድ ክፍል ሆኖ መቅረብ አለበት፤

27.3. በግዥ ፈፃሚው የኮርፖሬሽኑ አካል እና በአቅራቢው መካከል ውል ካልተፈረመ በስተቀር የጨረታው አሸናፊ በመገለጹ ብቻ ውል እንደተፈጸመ አይቆጠርም፡፡ እንደአስፈላጊነቱ የውሉ አፈጻጸም የሚከተላቸውን ዋና ዋና ሂደቶች፣ የማስረከቢያ ጊዜ፣ አስተሻሽግ፣ የማጓጓዝ ኃላፊነት፣ የዋጋ ማስተካከያ፣ የክፍያ አፈጻጸም፣ የርክክብ እና የፍተሻ ሥነ ሥርዓት፣ ዋስትና እና የመሳሰሉትን አተገባበር በግልጽ ያስቀመጠ መሆን ይኖርበታል፤

27.4. በአቅራቢው እና በግዥ የሥራ ክፍል መካከል የሚደረገው ውል አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን፤ የግንባታ ሥራውን፣ የምክርና አገልግሎቱን ወይም አጠናቆ ባያስረክብ፡-

ሀ. ርክክብ ባልተፈጸመበት ግዥ ዋጋ በየቀኑ የውሉ 0.1% ወይም 1/1000 መቀጫ እንደሚከፍል፤ ነገር ግን የሚቀጣው የገንዘብ መጠን አጠቃላይ ከውሉ 10%/ አሥር በመቶ / ሊበልጥ እንደማይችል፤

ለ. በዚህ ዓይነት የሚታሰበው መቀጫ የውሉን ዋጋ 10% /አሠር በመቶ/ የሚበልጥ በሚሆንበት ጊዜ ኮርፖሬሽኑ ውሉን የመሠረዝ መብት እንዳለው፤

ሐ. የውሉ አፈፃፀም መዘግየት በሥራው እንቅስቃሴ ላይ ችግር የሚያስከትል ከሆነ ኮርፖሬሽኑ የመቀጫው መጠን 10% / አሥር በመቶ / እስከሚሞላ ድረስ

መጠበቅ ሳይገደድ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን መሠረዝ እንደሚችል መጠቀስ ይኖርበታል፡፡

27.5. አቅራቢው በውሉ መሠረት የማስረከቢያ ጊዜውን ባለማክበሩ የሚቀጣውን ቅጣት በሚመለከተው የግዥ ማጽደቅ ስልጣን ላለው ለዋና ስራ አስፈጻሚ ቀርቦ መጽደቅ ያለበት ሲሆን አቅራቢው የሚያቀርበውን ምክንያት ተቀባይነት መጣራት ይኖርበታል፤

27.6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (27.4) እና (27.5) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ አቅራቢው ዕቃውን ወይም አገልግሎቱን በውሉ ላይ በተመለከተው ጊዜ ያላቀረበው በበቂ ምክንያት መሆኑ ከታመነበት ግዥ የማጽደቅ ሥልጣን በተሰጠው የሥራ ኃላፊ የማቅረቢያው ጊዜ ሊራዘምለት ወይም ቅጣቱ ሊነሳለት ይችላል፤

27.7. የሚከተሉት ሰነዶች እንደ ስምምነቱ አካል ተቆጥረው በመነበብ ውሉን ይመሰርታሉ፡-

ሀ. አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች / General Conditions of Contract/

ለ. ልዩ የውል ሁኔታዎች / Special Conditions of Contract/

ሐ. የፍላጎቶች መግለጫ / Specififcations or Requirements /

መ. የጨረታ ማቅረቢያ ሠንጠረዥና በአቅራቢው የቀረበ የዋጋ አከፋፈል ሰሌዳ/ Bid Submission Sheet & Price Schedule Sheet/

ሠ. የግዥ ፈፃሚው አካል ለአቅራቢው ለመዋዋል መፍቀዱን የሚያሳውቅ ደብዳቤ /Notification of Award /

ረ. ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶች /other documents reqired /

27.8. ከዚህ በተጨማሪ የውሉ ይዘት ላይ የሠፈሩ ቃላት መግለጫዎች አንድ አይነት ትርጓሜ በውሉ ሁኔታዎች ውስጥ በሚገለፁት አኳኋን ይሆናል፡፡

27.9. በውሉ ላይ የሚደረጉ ለውጦች በጽሑፍ ሆነው በአግባቡ በማስረጃነት መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

27.10. ማንኛውም የግዥ ውል ተቀባይነት የሚኖረው ሥልጣን በተሰጣቸው የኮርፖሬሽኑ አካላት ከተፈረመ ብቻ ነው ፡፡

27.11. ኮርፖሬሽኑ በውል ሰነድ ላይ የሚሰፍሩ ኃላፊነቶችን እና ግዴታዎችን በጥንቃቄ መመርመር ያለበት ሲሆን በኮርፖሬሽኑ ደረጃ ሊከናወኑ የማይችሉ ግዴታዎችን ተቀብሎ ውል መፈረም የለበትም፡፡

## 28. የውል ማስከበሪያ

28.1. በዋጋ ማቅረቢያ ከሚፈጸም ግዥ በስተቀር ለማናቸውም ሌላ የግዥ ውል ኮርፖሬሽኑ የውል ማስከበሪያ መቀበል አለበት፤

28.2. የጨረታው አሸናፊ ከኮርፖሬሽኑ ጋር ውል ከፈረመበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ለጨረታ ማስከበሪያ ተቀባይነት እንዳላቸው በአንቀፅ 13.19.4 በተገለጹት የዋስትና ዓይነቶች መሰረት ክፍያ በሚፈጸምበት የገንዘብ ዓይነት ቢያንስ የውሉን ዋጋ 10% / አስር በመቶ / በውል ማስከበሪያነት ለኮርፖሬሽኑ ማስያዝ አለበት፤

28.3. ኮርፖሬሽኑ አቅራቢው በውሉ መሰረት አለመፈጸሙን ሲያረጋግጥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (28.2) መሰረት አቅራቢው ያስያዘውን የውል ማስከበሪያ ሙሉ በሙሉ መውረስ ይኖርበታል፤

28.4. ኮርፖሬሽኑ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (28.3) መሰረት ለወሰዳቸው እርምጃዎች የተሟላ ሰነድ በመያዝ ጉዳዩ በሚመለከተው ሕጋዊ አካል ሲጠየቅ ማቅረብ እና የአሰራሩን አግባብነት ማስረዳት ይኖርበታል፡፡

28.5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (28.2) የተመለከተው ቢኖርም፡-

ሀ. ከአገር ውስጥ የግንባታ ዘርፍ ሥራ ተቋራጮች ወይም መድኃኒት እና የህክምና መሣሪያዎች አምራች ድርጅቶች ለሚፈጸም ግዥ ከታወቀ የመድን ድርጅት የሚቀርብ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የውል ማስከበሪያ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

ለ. የምክር አገልግሎት በመስጠት ተግባር ላይ የተሠማሩ አማካሪዎች በሚሰጡት የምክር አገልግሎት ሂደት ውስጥ ኮርፖሬሽኑ ላይ ጉዳት ሊደርስ ይችላል ተብሎ ሲገመት የባለሙያ የካሣ መድን እንደያቀርቡ መጠየቅ ይችላል፡፡

ሐ. አምራች ጥቃቅን አነስተኛ ተቋማት በአዋጁ በተገለጸው መሰረት በውል ማስከበሪያ ምትክ ካቋቋሚቸው አካል የሚሰጣቸውን የዋስትና ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡

መ. ከፍተኛ ለሆኑ ግዥዎች አቅራቢዎች የሥራ አፈፃፀም ዋስትና በሲፒኦ ወይም በባንክ ዋስትና ማስያዝ ለሥራ አዳጋች በሚሆንባቸው ወቅቶች ኮርፖሬሽኑ የአቅራቢዎችን አስተማማኝነት ከግምት በማስገባት የሥራ አፈፃፀም ዋስትና ከታወቀ የመድን ድርጅት እንደአስፈላጊነቱ በሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ ወይም በሁኔታ ላይ የተመሠረተ የውል ማስከበሪያ እንዲያስይዙ ሊፈቅድ የሚችል ሲሆን ይህም በዋና ሥራ አስፈፃሚው በቅድሚያ መጽደቅ አለበት፡፡

ረ. ተጫራቾች ለኪራይ አገልግሎት የቅድሚያ ክፍያ የማይከፈላቸው ከሆነ የውል ማስከበሪያ አስቀድመው እንዲያቀርቡ አይጠይቁም፡፡ ሆኖም ከእያንዳንዱ ክፍያቸው 10 በመቶ በሪቴንሽን መልክ በመቀነስ እስከ የበጀት ዓመቱ መጨረሻ ድረስ ይዞ ማቆየትና በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከተጠራቀመው ሪቴንሽን ውስጥ 10 በመቶውን ብቻ በማስቀረት ቀሪው እንዲለቀቅላቸው መደረግ አለበት፡፡ አከራዮች በአንድ የበጀት ዓመት ሊያዝ ከሚችለው በላይ ያልተከፈላቸው የአገልግሎት ክፍያ ካላቸው ከሚፈፀምላቸው ክፍያ ላይ ሪቴንሽን መቀነስ አያስፈልግም፡፡

ሰ. በፍትሐብሔር ሕግ በተደነገገው መሠረት ተጫራቾች የሚያቀርቡት ማናቸውም ዓይነት የዋስትና ሠነድ በሁለት የዋስትና ሰጪው አካል ባለሥልጣናት የተረጋገጠ መሆን ያለበት ሲሆን ይህም በሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ውስጥ መካተት አለበት፡፡

28.6. በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መካከል የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የተያዘው የውል ማስከበሪያ አቅራቢው የውል ግደታውን ሙሉ በሙሉ እንዳጠናቀቀ መመለስ ይኖርበታል፡፡

## 29. <u>የቅድሚያ ክፍያ</u>

29.1. በኮርፖሬሽኑ ግዢ አፈፃፀም እንደ አስፈላጊነቱ ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ እስከ 30% /ሠላሳ በመቶ / የሚደርስ የቅድሚያ ክፍያ ሊሰጥ ይችላል፡፡ የሚሰጠው የቅድሚያ ክፍያ መጠንም በተጫራቾች መመሪያ ላይ መገለጽ ይኖርበታል፡፡

29.2. አቅራቢዎች በውሉ መሠረት ከሚጠይቁት የቅድሚያ ክፍያ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና እንደ አቅራቢው ምርጫ ከታወቀ ባንክ የሚሰጥ የተረጋገጠ ቼክ /CPO/ ወይም በሁኔታው ላይ ያልተመሠረተ የባንክ ዋስትና ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

29.3. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 29 ንዑስ 29.4 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ለአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት የሚሰጠው የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ካቋቋሚቸው አካል የሚሰጣቸውን የዋስትና ደብዳቤ ማቅረብ የሚችሉ ሲሆን ይህም በግዥ አፅዳቂው ኮሚቴ በቅድሚያ መጽደቅ አለበት ፡፡

29.4. በንዑስ አንቀጽ 29 ንዑስ 29.2 እና 29.3 መሰረት ለሚፈጸም የቅድሚያ ክፍያ የቀረበው ዋስትና በሁኔታ ላይ የተመሠረተ ሲሆን ውል ሰጪው ኮርፖሬሽኑ ውል ተቀባይ ከሆነው ሥራ ተቋራጭ ወይም አነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋም ጋር የቅድሚያ ክፍያውን አጠቃቀም በሚመለከት የተለየ ውል መዋዋል አለበት፡፡ ውሉም የሚከተሉትን ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡-

ሀ) በውሉ መሠረተ ለሥራ ተቋራጭ ወይም ለአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋሙ የሚፈፀመው የቅድሚያ ክፍያ እንደ አስፈላጊነቱ የውሉን ጠቅላላ ዋጋ ከ30% /ሠላሣ በመቶ/ ያልበለጠ ሲሆን አከፋፈሉም በሦስት ዙር ሆኖ የመጀመሪያው እና የሁለተኛ ዙር የጠቅላላውን ቅድሚያ ክፍያ 40% /አርባ በመቶ/ እንዲሁም በመጨረሻው ዙር የጠቅላላውን ቅድሚያ ክፍያ 20% /ሃያ በመቶ/ መሆን አለበት፤

ለ) ከላይ በፊደል ተራ "ሀ" የተቀመጠው የቅድሚያ ክፍያ አፈጻጸም እንደተጠበቀ ሆኖ የመጀመሪያው እና የሁለተኛ ዙር የጠቅላላው ቅድሚያ ክፍያ 40% /አርባ በመቶ/ በሚከፈልበት ወቅት ኮርፖሬሽኑ /ቅድሚያ ክፍያውን ያጸደቀው አካል/ ሥራ ተቋራጭ ወይም አነስተኛና ጥቃቅን ተቋሙ በቅድሚያ ክፍያውን በአግባቡ የሚጠቀምበት መሆኑን መከታተል አለበት፤

ሐ) ከላይ በፊደል ተራ "ሀ" እና "ለ" የተቀመጡት አሠራሮች እንደተጠበቁ ሆነው ሁለተኛው ዙር የቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ ለሥራ ተቋራጩ ወይም ለአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋሙ ክፍያ የሚፈጸመው ቀደም ሲል በአንደኛው ዙር በወሰደው ገንዘብ ተገቢውን ሥራ የሠራ መሆኑ ሲረጋገጥ ሲሆን ሦስተኛው ዙር የቅድሚያ ክፍያም የሚፈጸመው በአንደኛውና በሁለተኛው ዙር በተለቀቁት የቅድሚያ ክፍያዎች ተገቢው ሥራዎች የተሠሩ መሆናቸው ከተረጋገጠ በኋላ ነው ፡፡

29.5. አቅራቢው የወሰደው የቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ በውሉ በየደረጃው በሚዘጋጁት የክፍያ ምስክር ወረቀቶች ወይም በየደረጃው በሚፈጸሙ ለሥራ ተቋራጩ ወይም ለአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋሙ መሠረት ሊከፈለው ከሚገባው ሂሣብ ላይ እየተቀነሰ እንዲመለስ መደረግ አለበት፡፡

## 30. <u>ውል መፈረም</u>

30.1. ኮርፖሬሽኑ የመደበኛ ጨረታ ሠነዶች አንድ ክፍል የሆነው አጠቃላይ የውል እና ስምምነት ላይ የተደረሰባቸውን ልዩ የውል ሁኔታዎች የያዘውን የውል ሠነድ ከአቅራቢው ጋር መፈራረም አለበት፡፡

30.2. በአቅራቢው እና በኮርፖሬሽኑ መካከል የሚደረገው ውል የሁለቱን ወገኖች ኃላፊነት በግልጽ ማመልከት ያለበት ሲሆን የሚከተሉትን ጉዳዮች በተጨማሪነት ያከተተ መሆን ይኖርበታል፡፡

ሀ. በውሉ የሚቀርበው ዕቃ የግንባታ ሥራ ወይም የምክር እና ሌሎች አገልግሎቶች ዓይነት፣ ጥራትና ብዛት ፣ የሚቀርብበት አኳኋን ወይም የማስረከቢያ ጊዜውን ፣ የሚከፈለውን አጠቃላይ እና የነጠላ ዋጋ መጠን፣ የአከፋፈል ሁኔታ እና የክፍያ ጊዜውን፤

ለ. ከሶስተኛ ወገን የሚገኙ አገልግሎቶችን እንደ መጓጓዣ፣ ኢንሹራንስ፣ ትራንዚት እና የመሳሰሉት ተግባራትን የመከታተል እና የመፈጸም ኃላፊነት የማን እንደሚሆን መጠቀስ ያለበት ሲሆን ኃላፊነቶቹም በተሻለ ብቃት ሊፈጽማቸው በሚችል አካል እንዲሠሩ መደረግ ይኖርበታል፡፡

ሐ. አቅራቢው በመጫረቻ ሠነዱ ላይ ያመለከተው የዋጋ ቅናሽ ወይም ሌሎች ሁኔታዎች እና አፈፃፀማቸውን በግልጽ ያመላከተ መሆን አለበት፤

መ. በውል አፈፃፀም ወቅት የሚነሱ አለመግባባቶች የሚፈቱበትን አካሄድ ፣

ሠ. የውጭ አገር ተጫራች ከጠቅላላው የውሉ መጠን ውስጥ በውጭ አገር ገንዘብ እና በብር ሊከፈለው የሚገባው የገንዘብ መጠን ድርሻ ታይቶ መገለጽ ይኖርበታል፣

ረ. የውል አካል የሆኑ የግዢ ሠነዶች እና የተፈፃሚነት ወሰን

ሰ. ለውል አፈፃፀም የተያዘው የውል ማስከበሪያ ሊወረስ የሚችልባቸውን ሁኔታዎች

ሸ. አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን፣ የምክር አገልግሎቱን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራውን ወይም አገልግሎቱን አጠናቆ ባያስረክብ ላዘገየበት ጊዜ የሚወሰደውን እርምጃ ፤

ቀ. ውሉ በዚህ መመሪያ በተቀመጠው የመፈረም ሥልጣን መሠረት የሚመለከተው ኃላፊ ውሉን ያፀድቃል፡፡

በ. በአቅራቢው እና በኮርፖሬሽኑ በኩል የሚፈርሙ ሁለት ሁለት ምስክሮች ስም፣ ፊርማ እና ሌሎችንም አስፈላጊ የሆኑ ነጥቦች መያዝ ይኖርበታል፡፡

30.3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ 30.6 ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ሌላ የተለየ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር አሸናፊው ተጫራች ማሸነፉ ከተገለጸለት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ቀርቦ ውሉን መፈረም ይኖርበታል፡፡

30.4. ኮርፖሬሽኑ አሸናፊ መሆኑን በገለፀለት በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ የግዢ ውል ያልፈረመ አቅራቢ ከጨረታው ይሠረዝና ከአንድ እስከ ሁለት ዓመት ኮርፖሬሽኑ በሚያወጣቸው በማናቸውም ጨረታዎች እንዳይሳተፍ ሪፖርቱን ለኤጀንሲው ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡ ይህ ውሣኔ ተግባራዊ የሚሆነው በግዢ ፈፃሚው አካል የሚቀርበው የአፈፃፀም ሪፖርት ለሚመለከተው የግዥ አፅዳቂ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበት እና ታምኖበት በዋና ስራ አስፈፃሚ ሲጸድቅ ነው፡፡

30.5. በአቅራቢው በኩል ውል መፈረም የሚችሉት አቅራቢው ወይም ህጋዊ ውክልና የተሰጠው ሰው ብቻ ነው፤

30.6. በኮርፖሬሽኑ በኩል ውሉን መፈረም ያለበት በውሉ የሚፈፀመው ግዥ የዕቃ፣ የግንባታ ሥራዎች፣ የምክርና ሌሎች አገልግሎቶች ዋና ሥራ አስፈፃሚው ባላቸው የግዥ ማጽደቅ ሥልጣን ወይም ውክልና በሚሰጡት አካል ይሆናል፡፡

30.7. ኮርፖሬሽኑ የጨረታውን ወይም የቅሬታውን ውጤት ለተጫራቾች ከገለፀበት ቀን ጀምሮ ሰባት /7/ ቀናት ከመሙላቱ በፊት የግዢ ውል መፈረም የለበትም፡፡

## 31. ውልን ተፈፃሚ ማድረግ

31.1. ኮርፖሬሽኑ ከአቅም በላይ የሆነና የተለየ ሁኔታ ካላጋጠመው በስተቀር ከአቅራቢዎች ጋር የተደረጉ የውል ስምምነቶች በፍጥነት ተፈፃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

31.2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ 31.1 ላይ የተመለከተውን ተግባራዊ ለማድረግ ውሉ የሚያስቀምጠው ቅድመ ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮርፖሬሽኑ የሚከተሉትን ተግባራት መፈጸም ይኖርበታል፡፡

ሀ) ውሉ ቅድሚያ ክፍያ እንደሚፈጸም የሚያዝ ከሆነ በዚህ መመሪያ ላይ በተቀመጠው መሰረት አቅራቢው የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና እንዲያሲዝ በማድረግ የቅድሚያ ክፍያውን በወቅቱ መፈጸም ፣

ለ) ሌተር ኦፍ ክሬዲት ሊከፈትላቸው ለሚገባ ግዢዎች ተገቢው ፎርማሊቲ መሟላቱን በማረጋገጥ ሌተር ኦፍ ክሬዲቱን በፍጥነት መክፈት ፣

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ በፊደል ተራ “ሀ” ከተቀመጡት በተጨማሪ በኮርፖሬሽኑ ሊፈጸሙ የሚገቡ ተግባራት በውሉ መሰረት በወቅቱ ማከናወን ፡፡

31.3. ኮርፖሬሽኑ ውሉን ተፈፃሚ ለማድረግ በአቅራቢው ሊከናወኑ የሚገባቸውን ተግባራት በመለየት አቅራቢው በውሉ መሰረት ተግባራቱን በወቅቱ መፈጸሙን ተከታትሎ ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

31.4. ኮርፖሬሽኑ የውሉ ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተው ውሉ ተፈፃሚ መሆን የጀመረበትን ቀን መዝግቦ መያዝ እና እንደ አስፈላጊነቱ አቅራቢው እንዲያውቀው ማድረግ ይኖርበታል፡፡

31.5. ኮርፖሬሽኑ የግንባታ ዘርፍ ሥራ ግዢ ሲፈጽም ክፍያ የሚፈጸመው የግንባታውን የክንውን መረጃ መሰረት አድርጎ እና የሚከተለውን አፈጻጸም ተከትሎ መሆን ይኖርበታል፡፡

ሀ. ለግንባታ ሥራ ክፍያ የሚፈጸመው የሥራውን ደረጃ በሚቆጣጠረው መሐንዲስ ወይም ኃላፊነት ባለው ሥራ ክፍል በሚሰጥ የክፍያ የምስክር ወረቀት መነሻነት ብቻ ይሆናል፡፡

ለ. ለማናቸውም የግንባታ ሥራ በክፍያ የምስክር ወረቀት መሰረት ከሚፈጸመው ከእያንዳንዱ ክፍያ ላይ ለግንባታ ሥራው ጥራት ዋስትና እንዲሆን 5% /አምስት በመቶ/ መያዣ መልክ ተቀንሶ ይያዛል፡፡

ሐ. የግንባታ ሥራው ሲጠናቀቅ እና ጊዜያዊ ርክክብ ሲደረግ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ /ለ/ መሰረት ከተያዘው ገንዘብ ላይ 50% /ሃምሣ በመቶ/ ለሥራ ተቋራጩ ይለቀቃል፡፡ ቀሪው 50% /ሃምሣ በመቶ/ ለአንድ ዓመት የጥገና ጊዜ ተይዞ ይቆያል፡፡ ሆኖም የሥራ ተቋራጩ ከአንድ (1) ዓመት በኃላ የሥራው ሁኔታ ታይቶ ቀሪው ቀሪው 50% /ሃምሣ በመቶ/ ይለቀቅለታል፡፡

መ. በሚቆጣጠረው መሐንዲስ ወይም ኃላፊነት ባለው ሥራ ክፍል የክፍያ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ከሥራ ተቋራጩ ተዘጋጅቶ በቀረበለት አስራ አራት (14) ቀናት ውስጥ የምርመራውን ሥራ ማጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡

ሠ. የክፍያ የምስክር ወረቀት በሚቆጣጠረው መሐንዲስ ወይም ኃላፊነት ባለው ሥራ ክፍል ተረጋግጦ በቀረበ ሃያ ስምንት (28) ቀናት ውስጥ ኮርፖሬሽኑ ተገቢውን ክፍያ ለሥራ ተቋራጩ መፈጸም አለበት፡፡

ረ. በሚቆጣጠረው መሐንዲስ ወይም ኃላፊነት ባለው ሥራ ክፍልየክፍያ የምስክር ወረቀት ተዘጋጅቶ ከቀረበለት በኂላ ያለ በቂ ምክንያት በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ /መ/ ላይ ከተጠቀሰው ጊዜ ያሳለፈ እንደሆነ በመዘግየቱ ምክንያት ተቋራጩ በኮርፖሬሽኑ ላይ ለሚያቀርበው ማንኛውም ተጨማሪ የክፍያ ጥያቄ በሚቆጣጠረው መሐንዲስ ወይም ኃላፊነት ባለው ሥራ ክፍል ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

ሰ. ያለ በቂ ምክንያት በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ /ሠ/ ላይ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በሚቆጣጠረው መሐንዲስ ወይም ኃላፊነት ባለው ሥራ ክፍል በቀረበለት ማረጋገጫ መሰረት ክፍያ ባይፈጽም ተቋራጩ በውሉ መሰረት ለሚያቀርበው ተጨማሪ የክፍያ ጥያቄ ኮርፖሬሽኑ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

## 32. <u>የውል አፈፃፀምን መከታተል</u>

32.1. ኮርፖሬሽኑ የውል አፈፃፀምን የሚከታተል አካል መለየት ወይም የውል ክትትል በተለያዩ አካላት በቅንጅት የሚፈጸም በሚሆንበት ወቅት አካላቱ ተግባርቸውን በግልጽ እንዲያውቁ ማድረግ ይኖርበታል ፡፡

32.2. የውል አፈፃፀምን የሚከታተለው የኮርፖሬሽኑ አካል አቅራቢው በውሉ መሰረት የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት በውሉ ላይ በተገለጸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እየተከናወኑ የሚገኙ መሆኑን መከታተል ይኖርበታል፡፡

32.3. ኮርፖሬሽኑ በውል ስምምነቱ መሰረት እንደ አስፈላጊነቱ የሚከተሉትን የውል አስተዳደር ተግባራት ማከናወን ይጠበቅበታል፡፡

ሀ. ተከታታይ ክፍያዎችን በወቅቱ መፈጸም ፤

ለ. አቅራቢው የውል ግዴታውን እየተወጣ እንደሚገኝ የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን በወቅቱ መስጠት፤

ሐ. አቅራቢው የውል ግዴታውን መወጣት እንዲችል ሕጋዊ የሆነ እገዛ በማድረግ የውሉ አፈፃፀም የተሳካ እንዲሆን ማደረግ ይኖርበታል፡፡

32.4. በውል አፈፃፀም ወቅት እንደ ሁኔታው የውል ማሻሻያ ማድረግ የሚቻል ሲሆን የሚደረገውየውል ማሻሻያ የኮርፖሬሽኑን ጥቅም የሚጎዳ እና በጨረታው ከተወዳደሩ ሌሎች ዕጩ ተወዳዳሪዎች አንፃር ለአቅራቢው የተለየ ጥቅም የሚሰጥ መሆን የለበትም፤

32.5. በውል አፈፃፀም ክትትል ወቅት ኮርፖሬሽኑ በተለይ የሚከተሉትን ተግባራት መፈጸም ይኖርበታል፡፡

ሀ. የውል ስምምነቱን ሁኔታዎች ጠብቆ ሌተር ኦፍ ክሬዲት በወቅቱ መክፈት

ለ. ተቀባይነት የሚኖራቸውን የሌተር ኦፍ ክሬደት ማስተካከያ ጥያቄዎች ተቀብሎ አፋጣኝ ምላሽ መስጠት፣

ሐ. ተገቢው አገልግሎት ከማግኘቱ በፊት የውል ማስከበሪያ፣ የሌተር ኦፍ ክሬዲት፣ የዋራንቲ መጠቀሚያ ጊዜዎች እንዳያልፉ ጥንቃቄ እና ክትትል ማድረግ፣

መ. የግንባታ ሥራዎች በተያዘላቸው ጊዜ ገደብ ውስጥ መገንባታቸውን የዕቃ አቅርቦቶች እና አገልግሎቶች በውሉ ጊዜ ውስጥ ለመከናወናቸው ክትትል መደረጉን እና ሪፖርት መቅረቡን፣

ሠ. ከውል አፈፃፀም ጋር በተያያዘ ከአቅራቢዎች ምንም ዓይነት የይገባኛል ጥያቄዎች እንዳይፈጠሩከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ፡፡

32.6. ኮርፖሬሽኑ በውልአፈፃፀም ወቅት ከሦስተኛ ወገን የሚገኙ አገልግሎቶችን መለየት እና አገልግሎቶቹ የውል አፈፃፀሙን በሚያግዝ መልኩ መስጠታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

32.7. የግንባታ ሥራዎች ውል ክትትል ዝርዝር አፈፃፀም በግንባታ ሥራ መመሪያ መሰረት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## 33. ውል ስለማሻሻል

33.1. በውል አፈፃፀም ወቅት እንደሁኔታው የውል ማሻሻያ ማድረግ የሚቻለ ሲሆን የሚደረገው የውል ማሻሻያ የኮርፖሬሽኑን ጥቅም የሚጎዳ ፣ እንዲሁም በጨረታው ከተወዳደሩ ሌሎች ዕጩ ተወዳዳሪዎች አንፃር ለአቅራቢው የተለየ ጥቅም የሚሰጥ መሆን የለበትም ፡፡

33.2. ኮርፖሬሽኑ በገባቸው ውሎች ውስጥ ለተጠቀሱ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ብዛት የማስረከቢያ ጊዜ ፣ የአከፋፈል ሁኔታ ላይ ለውጥ ማድረግ በሚፈለግበት ወቅት ከአቅራቢው ወይም ከተቋራጩ ጋር በመወያየት ለውጥ ማድረግ ይችላል፤

33.3. የውል ማሻሻያዎች ለማድረግ የሚቻለው በውሉ ላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሲሆን ብቻ ነው፤

33.4. ማንኛውም በጽሑፍ ያልተደረገ፣ ቀን ያልተፅፈበት፣ በግልጽ ውሉን የማይጠቅስና ስልጣን ባላቸው አካላት ያልተፈረመ ማሻሻያ ወይም ለውጥ ዋጋ አይኖረውም፡፡

## 34. ውል ስለማቋረጥ

34.1. ኮርፖሬሽኑ የግዥ ውል ከማቋረጡ በፊት ማናቸውንም ኮርፖሬሽኑን የማይጎዳ አማራጮችንመውሰድ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም አማራጮች ውጤት ካላስገኙ እንደ አስፈላጊነቱ ከህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት የምክር አገልግሎት በማግኘት ውሉን በሙሉ ወይም በከፊል ማቋረጥ ይችላል፡፡

34.2. አቅራቢው፣ ተቋራጩ ወይም አገልግሎት ሰጪው በውሉ የተጠቀሰውን ግዴታ በአግባቡ መወጣት ሳይችል ሲቀር ውል ይቋረጣል፤

34.3. የዕቃው፣ የግንባታ ሥራው ወይም የአገልግሎቱ ጥራት በውሉ በተጠቀሰው መሠረት ሳይሆን ሲቀር ውል ይቋረጣል፤

34.4. አቅራቢው፣ ተቋራጩ ወይም አገልግሎት ሰጪው በውሉ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ዕቃውን፣ የግንባታ ሥራውን ወይም አገልግሎቱን ማቅረብ ሳይችል ሲቀር ውል ይቋረጣል፤

34.5. አቅራቢዎች፣ ተቋራጮች ወይም አገልግሎት ሰጪዎች ኪሳራ ደርሶባቸው ሥራ ሲያቋርጡ ውል ይቋረጣል፤

34.6. በኮርፖሬሽኑ እና አቅራቢዎች፣ ተቋራጮች ወይም አገልግሎት ሰጪዎች መካከል በሚደረግ ስምምነት ውል ይቋረጣል፤

34.7. አቅራቢው፣ ተቋራጩ ወይም አገልግሎት ሰጪው በጨረታ ውድድር ወይም በውል አፈፃፀም ወቅት በሙስና ወይም በማጭበርበር ተግባር የተሳተፈ መሆኑን ኮርፖሬሽኑ ሲያረጋግጥ ውል ይቋረጣል፤

34.8. ኮርፖሬሽኑ አቅራቢው፣ ተቋራጩ ወይም አገልግሎት ሰጪው ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን በማንኛውም ጊዜ ሊያቋርጥ ይችላል፡፡ ውል የማቋረጫ ማስጠንቀቂያው ለኮርፖሬሽኑ አመቺነት ሲባል መሆኑን የውል አፈጻጸም ደረጀውንና ውሉ ከመቼ ጀምሮ መቋረጥ እንዳለበት መገለጽ አለበት፡፡ ይህም በሚሆንበት ጊዜ የተጠናቀቁና ከማስጠንቀቂያ በኋላ በ 28 /ሃያ ስምንት/ ቀናት ውስጥ ለመረከብ ዝግጁ መሆን የሚችሉ እቃዎችን ኮርፖሬሽኑ በውሉ ዋጋና ሁኔታ ይረከባል፡፡ ለቀሩት ዕቃዎች ኮርፖሬሽኑ ቀጥሎ ካሉት አማራጮች መምረጥ ይችላል፡፡

   ሀ. በከፊል የቀረበውን ዕቃ ወይም ተያያዥ አገልግሎቶች በውል ጨረታ ዋጋ መረከብ

   ለ. ቀሪውን በመሰረዝ በከፊል ለተጠናቀቁት ዕቃዎችና ተያያዥ አገልግሎቶች እንዲሁም አቅራቢው ቀደም ሲል ለገዛው ቁሳቁሶች ዕቃዎችና ተያያዥ አገልግሎቶች በውሉ ላይ በተጠቀሰው ዋጋ መሠረት መክፈል አለበት፡፡

34.9. አቅራቢው በውሉ የተጠቀሰውን ግዴታ በአግባቡ መወጣት ባለመቻሉ ውሉ በመቋረጡ ምክንያት ኮርፖሬሽኑ ከሚደርስበት ጉዳት ጋር በተያያዘ የሚከተሉትን እርምጃዎች ሊወሰድ ይችላል፡፡

   ሀ. አቅራቢው ያስያዘውን የሥራ አፈፃፀም ዋስትና ሙሉ በሙሉ መውሰድ

   ለ. በሌሎች ጨረታዎች ከ1-2 ዓመት /አንድ እስከ ሁለት/ እንዳይሳተፍ ማገድ

   ሐ. በሌሎች ድርጅቶች ጨረታ እንዳይሳተፍ ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ማሳወቅ፡፡

34.10. የሚመለከተው የግዥ የሥራ ክፍል ግደታውን በአግባቡ ያልተወጣ አቅራቢ በጨረታ እንዳይሳተፍ የእገዳ ደብዳቤ በደረሰው በ5 /አምስት/ ቀናት ውሰጥ አቅራቢው በጉዳዩ ላይ ያለውን አስተያየት ለዚሁ አካል ማቅረብ ይችላል፡፡ የአቅራቢው አስተያየት

ተቀባይነት ካላገኘ ወይም አቅራቢው በ5 /አምስት/ ቀናት ጊዜ ውስጥ አስተያየቱን ካላቀረበ ኮርፖሬሽኑ በሚያወጣቸው ማናቸውም ጨረታዎች እንዳይሳተፍ ያግዳል፡፡

34.11. አቅራቢው በውሉ የተጠቀሰውን ግዴታ በአግባቡ መወጣት ሳይችል ሲቀር ኮርፖሬሽኑ ውሉን ከሰረዘ በኋላ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በግምገማው ውጤት ሁለተኛ ለሆነው ተጫራች የግዥ ትዕዛዝ መስጠት ይችላል፡፡ ይህ መሆን ካልቻለ ግን በተሻለ ዘዴ በአፋጣኝ ዕቃውን ወይም አገልግሎቱን ሊያገኝ የሚችልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

34.12. ኮርፖሬሽኑ ውሉን በሙሉም ሆነ በከፊል ያቋረጠ እንደሆነ አቀራቢው ያላስረከባቸውን ዕቃዎች የግንባታ ሥራዎች ወይም ያልፈፀማቸውን አገልግሎቶች በፈለገው ሁኔታ ሊገዛ ይችላል፡፡ ለደረሰበት ተጨማሪ ወጪም አቅራቢውን ማካካሻ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ አቅራቢውም ያልተቋረጠውን የውል ግዴታ መፈፀም ይኖርበታል፡፡

34.13. አቅራቢዎች ዕዳ መክፈል ባለመቻላቸው ወይም በኪሳራ ምክንያት ውሉ ሲቋረጥ ኮርፖሬሽኑ ለአቅራቢው የሚከፍለው ካሳ አይኖርም፡፡ ውል የማቋረጥ ድርጊት ኮርፖሬሽኑ ያለውን የመክሰስ መብት ወይም የሌላ መፍትሔ ዕድል አያሳጣም፡፡

## 35. <u>ውል ማጠናቀቅ</u>

35.1. ኮርፖሬሽኑ ከአቅራቢዎች ጋር የተፈረሙ ውሎችና ተያያዥ ጉዳዮች ተገቢውን ዕልባት በወቅቱ አግኝተው ውሉ መዘጋቱን ማረጋገጥ አለበት፡ ለዚህም ፡-

ሀ. አቅራቢው በውል ስምምነቱ መሰረት የሚገባውን የግንባታ ዘርፍ ሥራ፣ ዕቃ፣ የምክር ወይንም ሌሎች አገልግሎቶች ማቅረቡን ማረጋገጥ፣ አለባቸው፤

ለ. በውሉ መሰረት የተያዙ ዋስትናዎች ተገቢው ክትትል የተደረገባቸው እና አስፈላጊ በሆነ ወቅት ውሳኔ የተሰጠባቸው መሆኑን ማረጋገጥ፣

ሐ. በውሉ መሠረት ለአቅራቢዎች ሊከፈል የሚገባ ክፍያ የተጠናቀቀ መሆኑ፤ ክፍያዎች ሁሉ በውሉ መሰረት አገልግሎት መገኘቱን ማረጋገጥ፣

መ. ከሶስተኛ ወገን ማለትም ከኢንሹራንስ ኩባንያዎች፣ ከአጓጓዦች፣ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ ከጉምሩክ አስተላላፊዎች፣ ከባንክ እና ከሌሎች አገልግሎት ሰጪዎች ጋር የተያያዙ የባንክ ጥቅሞች መከበራቸውን እና የባንኩ ግዴታዎች የተፈፀሙ መሆኑን ማረጋገጥ፣

35.2. ኮርፖሬሽኑ ከአቀራቢው እና ከሦስተኛ ወገን ጋር ያሉ ያልተጠናቀቁ ሒሳቦችን በመዝጋት እንደ አስፈላጊነቱ የውል አፈፃፀም ግምገማ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

35.3. ኮርፖሬሽኑ ከውሉ መጠናቀቅ በኋላ አስፈላጊ ማስረጃዎች ተጠናቅረው መያዛቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

## 36. ርክክብ እና ክፍያ አፈፃፀም

36.1. ኮርፖሬሽኑ ክፍያ ከመፈፀሙ እና ሙሉ ርክክብ ከማካሄዱ በፊት በዕቃዎች እና ተያያዥ አገልግሎቶች ላይ ምርመራዎችንና ሙከራዎችን ማካሄድ አለበት፡፡ ለሚከናወነው ምርመራና መሰራቱን በማረጋገጥ እንደ አስፈላጊነቱ የአገልግሎት ግዥ መፈፀም ይችላል፡፡

36.2. ምርመራዎችና ሙከራዎችን ያካሄድ ባለሙያዎች አቅርቦቱ በውሉ መሠረት መከናወኑን ማረጋገጥ እና መፈረም ያለባቸው ሲሆን ባለሙያዎቹ በፍላጎት ዝርዝር መግለጫ ዝግጅት አና በግምገማ ላይ ያልተሳተፉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

36.3. በውሉ መሠረት ያልሆኑ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ርክክብ ከመፈፀሙ በፊት ለአቀራቢው ተመላሽ መደረግ እና በሌሎች መተካት አለባቸው፡፡

36.4. ኮርፖሬሽኑ ከቅድመ ክፍያ በስተቀር ማንኛውም ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ውሉ በአግባቡ መፈጸሙን ማጣራት የሚኖርባቸው ሲሆን በዚህም መሠረት ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በውሉ ላይ በተሰጠቀው የጥራት ደረጃ፣ ብዛት፣ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ መሠረት መሆኑን እና በተወሰነለት የጊዜ ገደብ ውስጥ መፈፀሙን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡ ለዚህም ይረዳ ዘንድ ክፍያው በሚፈጸምበት ወቅት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሰነዶች ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

ሀ. የግዥ ውልና ትዕዛዝ

ለ. የዕቃው፣ የግንባታ ሥራው እና የአገልግሎት መረከቢያ ሠነድ ፤

ሐ. የዕቃ እና የግንባታ ሥራ ምርመራ ውጤት ሠነድ

መ. የአቅራቢው ወይም የተቋራጩ የክፍያ መጠየቂያ ሠነድ

ሠ. ከዚህም በጥሬ ገንዘብ፣ በሲፒኦ አና ወደ አቅራቢው ወይም ተቋራጩ ሒሳብ በማስገባት መፈፀም የሚቻል ሲሆን ማንኛውም ክፍያ በሚፈፀምበት ወቅት ሥልጣን በተሰጣቸው ሁለት ሠራተኞች መፈረም ይኖርበታል፡፡ ይህም በኮርፖሬሽኑ የክፍያ አፈጻጸም መመሪያ መሠረት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

36.5. በማዕከል ለሚፈፀሙ ግዥዎች ክፍያው በኮርፖሬት ፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የሚፈፀም ሲሆን በቅርንጫፎች ለሚካሄዱ ግዥዎች ክፍያው በቅርንጫፎች የሚፈፀም ይሆናል፡፡

36.6. አቅራቢው ከኮርፖሬሽኑ ክፍያ የሚጠይቀው ዕቃዎችና ተያያዥ አገልግሎቶችን ማቅረቡን ከሚገልጹ ደረሰኞች የቀረቡ ሰነዶችና በውል ውስጥ የተጠቀሱ ግዴታዎችን ካሟላ ኮርፖሬሽኑ ክፍያውን ወዲያው መፈጸም አለበት፡፡

36.7. በውሉ በሌላ አገር ገንዘብ እንዲከፈል ካልተጠቀሰ በስተቀር ማንኛውም ክፍያ በኢትዮጵያ ብር መክፈል ይኖርበታል፡፡

## 37. <u>ከአቅም በላይ የሆነ ችግር</u>

37.1 .ከአቅም በላይ ሆነ ችግር ደርሷል የሚባለው አቅራቢው ድንገት ደራሽ በሆነ ሁኔታ የውል ግዴታውን እንዳይፈጽም ከአቅሙ በላይ ሆነ ችግር ባጋተመው ጊዜ ነው፡፡

37.2 ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ነው ሊያሰኝ የሚችሉ ምክኒያቶች ከሚከተለው አንዱ ሊሆኑ ይችለላሉ፡፡

ሀ. ውል እንዳይፈጸም በመንግስት የሚደረግ ክልከላ፤

ለ. እንደ መሬት መናወጥ፤መብረቅ፤ማእበል፤እና የመሳሰሉ ፍጥረታዊ መቅጸፍቶች፤

ሐ. የጠላት፤ የውጪ ሀገር ወይም የሀገር ውስጥ ጦርነት፤

መ. ውል የገባው ወገን መሞት ወይም ባልታሰበ ሁኔታ የሚደርስበት ከባድ አደጋ ወይም ጽኑ ህመም፤

ሠ. በፍትሐብሔር ህግ የተዘረዘሩ ሌሎች ከአቅም በላይ አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ

37.3 ግልጽ የሆነ ተቃራኒ የውል ቃል ከሌለ በቀር ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች ተደርገው ሊቆጠሩ አይችሉም፡፡

ሀ. ለተዋዋይ ፋብሪካ ወይም ስራውን ከሚያከናውንበት በአንደኛው ቅርንጫፍ መ/ቤት ውስጥ የተደረገ የሰራተኛ አድማ ወይም የመ/ቤት መዝጋት፤

ለ. ለውሉ አፈጻጸም አስፈላጊ ሆኑ አቅርቦቶች ዋጋ መወደድ ወይም መርከስ፤

ሐ. ተዋዋይ ያለበትን የውል ግዴታ አፈጻጸም ወጪ የሚያከብድበት አዲስ ህግ መውጣት፤

# ክፍል አምስት

## ሥልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነት

### 38. ዋና ሥራ አስፈፃሚ

በልማት ድርጅቶች ማቋቋሚያ አዋጅ 25/1984 አንቀጽ 16 እና በፌደራል የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ 649/2001 አንቀጽ 8 ላይ የተገለፁት እንደ ተጠበቁ ሆኖ ዋና ሥራ አስፈፃሚው እነዚህ ተጨማሪ ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

38.1. ኮርፖሬሽኑ በዕቃ፤ በግንባታ ዘርፍ ሥራ፣ በምክርና ሌሎች አገልግሎቶች ግዥ አፈጻጸም ወጪ ሳደረገው ገንዘብ ተመጣጣኝ ጠቀሜታ ማግኘቱን የሚያረጋግጥ ሥርዓት መዘርጋቱን ማረጋገጥ፤

38.2. የኮርፖሬሽኑን የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ማሻሻያ ይገመግማል፣ ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ሲኖሩ ለኮርፖሬሽኑ ሥራ አመራር ቦርድ አቅርቦ እንዲፀድቅ ያደርጋል፤

38.3. የግዥ ሥራን እንዲያከናውኑ የሚመደቡ ሠራተኞችና ኃላፊዎች በዘርፉ በቂ የትምህርት፤ ዝግጅት፣ የሥራ ልምድ እና ጥሩ ሥነ-ምግባር ያላቸው መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

38.4. የግዥ ሥራን እንዲፈጽም የሚደራጀው የሥራ ክፍል ሥራውን በቡድን ለማከናወን የሚያስችለው አደረጃጀት፣ በቂ ስልጣን ያለውና ግልጽ የአሰራር ሥርዓት የተዘረጋለት መሆኑን ማረጋገጥ ፤

38.5. የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉና ከሶስት ያላነሱ አባላት ያሉት የኮርፖሬሽኑን ከፍተኛ ግዢዎች መርምሮ የሚያፀድቅ እና ከሦስት ዓመታት የማይበልጥ የአገልግሎት ዘመን የሚኖረው የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ማቋቋም፤

ሀ. እስከተቻለ ድረስ በኮርፖሬሽኑ ውስጥ በከፍተኛ የኃላፊነት ደረጃ ላይ የሚገኙ፣

ለ. ስብጥሩ ግን በተቻለ መጠን ከተለያየ የሙያ ዘርፍ የተውጣጡና በኮርፖሬሽኑ ሥራ የተሻለ እውቀትና ልምድ ያላቸው፣

ሐ. በመልካም ስነ ምግባራቸው ያላቸው፣ የተመሰገኑና እምነት የሚጣለባቸው፤

38.6. ውስብስብ ለሆነ እና ዝርዝር የቴክኒክ ግምገማ ለሚፈልጉ ግዥዎች ጊዜያዊ ገምጋሚ ኮሚቴ ማቋቋም፣

38.7. የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ አባላት ሥራቸውን ለማከናወን የሚያስችላቸው በቂ ጊዜ እና የቢሮ የሚያስፈልጉ መገልገያ መሣሪያዎች ይመቻቻል፤

38.8. በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ አባልነት የሚመደቡ ሠራተኞች ለሥራው የሚያውሉት ጊዜ የመደበኛ ሥራቸው አካል ሆኖ በሥራ ፕሮግራሞቻቸው እና ውጤት ላይ መመዝገቡን ማረጋገጥ፤

38.9 ለግዥ ሥራ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት የሥራ ክፍሉም ሆነ የውሳኔ ሃሣብ የሚያቀርቡ የጨረታ ኮሚቴዎች ሥራቸውን በተገቢው ለመወጣታቸው ክትትል ማድረግ እንደ አስፈላጊነቱም የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ፤

38.10 የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የኮርፖሬሽኑን የግዥ ዕቅድ መርምሮ ማፅደቅ፤

ሀ. የግዥ ዕቅዱ ከኮርፖሬሽኑ የሥራ ፕሮግራሞች ጋር መጣጣሙን፤

ለ. ተሰባስበው ሊፈፀሙ የሚችሉ ግዥዎች አንድ ላይ መሰባሰባቸውን፤

ሐ. ዕቅዱ የኮርፖሬሽኑን የግዥ ፍላጎቶች በሙሉ ያካተተ መሆኑን፤

38.11. በዚህ መመሪያ መሠረት በኮርፖሬሽኑ በዋና ሥራ አስፈፃሚ መጽደቅ የሚያስፈልጋቸው ግዥዎችን በሚመለከት፤

ሀ. በግዥ የሥራ ክፍሉ ደረጃ እንዲፀድቁ ውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

ለ. ከሥራው ጋር በቀጥታ ግንኙነት የሚኖረው የሥራ ኃላፊ እንዲያፀድቅ ውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

ሐ. በኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ የሚሰጠው ውክልና በገንዘብ መጠን ተገድቦ በተለያዩ ደረጃዎች ላይ ለሚገኙ የሥራ ኃላፊዎች ሊሰጥ ይችላል፡፡

38.12 በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13.14 መሠረት በግዥ አፈፃፀም ሂደት የሚደረጉ የዋጋ ማስተካከያዎችን አግባብነት ማረጋገጥ ፤

38.12. የደንበኞች ቅሬታ በየደረጃው ቀርቦ በሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ሳይፈታ ሲቀር ፍታት፣

38.13. በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ግዥዎችን ያፀድቃል፣ እንደ አስፈላጊነቱም ውል ይፈርማል

38.14. እንደ አስፈላጊነቱ ከግዥው ውስብስብነት ወይም ኮርፖሬሽኑ ካለው የግዥ አቅም በላይ ሲሆን የኮርፖሬሽኑ ግዥ በሦስተኛ ወገን እንዲፈፀም ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 39. ኮርፖሬት ሠርቪስ ዘርፍ ም/ዋና ሥራ አስፈፃሚ

39.1 በዋና ስራ አስፈጻሚ በመሰጠው ውክልና ግዥ ሥራ እና በጨረታ ኮሚቴነት ለተመደቡ ሠራተኞች እና የሥራ ኃላፊዎች የኮርፖሬሽኑን የግዥ አፈፃፀም መመሪያ፣ መደበኛ የግዢ ሠነዶች እና ሌሎች አስፈላጊ ሠነዶች እንዲደርሷቸው እና የኮርፖሬሽኑን የግዢ ሥርዓት በሚገባ እንዲያውቁ የሚያስችል ሥልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፤

39.2 በዚህ መመሪያ በተሰጠው የስልጣን ውክልና መሠረት የኮርፖሬሽንኑ እስትራቴጂክ ግዥዎችን ያቅዳል፤ ተፈፃሚ እንዲሆን ያስተባብራል፤ ይከታተላል፤

39.3 በዋና ሰራ አሰፈጻሚ በሚሰጠ የውክልና ስልጣን ልክ የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴና የግዥ ቴክኒክ ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል፤

39.4 ኮርፖሬሽኑ በዕቃና አገልግሎት ግዥ አፈፃፀም ወጪ ላደረገው ገንዘብ ተመጣጣኝ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ማግኘቱን ያረጋግጣል፤

39.5 ከአቅራቢዎች ጋር የሚኖሩ ግንኙነቶችን በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤

39.6 የገበያ ዋጋ ጥናት የሥራ አፈፅፀምን በበላይነት ይከታተላል፤

39.7 ግዥን አስመልክቶ ከዳይሬክቶሬቶችና ከቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጆች የመወሰን አቅም በላይ የሆኑ የደንበኞችን ቅሬታዎች ይፈታል፤

39.8 በኮርፖሬሽኑ የግዥ አፈጻጸም መመሪያ መሠረት ውሣኔ እንዲሰጥ ከተቀመጠለት ሥልጣን በላይ የሆኑ ግዥዎችን ለዋና ሥራ አስፈፃሚ አቅርቦ ያፀድቃል፤

39.9 የሚከተሉትን ጨምሮ የኮርፖሬሽኑን የግዥ አፈፃፀም በሚመለከት የኮርፖሬሽኑ የውስጥ ኦዲት፤ የኮርፖሬሽኑ ስነ-ምግባርና ፀረ ሙስና መከታተያ ጽ/ቤቶች፤ ጉዳዩ የሚመለከተው የመንግስት አካል ለሚያደርገው የግዥ ኦዲት ወይም ምርመራ ሥራ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡-

ሀ. ለኦዲት ሥራው የሚያስፈልጉ ሰነዶች በሚፈለገው ጊዜ እንዲቀርቡ ማድረግ ፤

ለ. ለተመደቡት ኦዲተሮች አገልግሎት የሚሆን የስራ ቦታ እንዲመቻች ማድረግ፤

ሐ. ስለተፈፀሙት ግዥዎች አካሄድ ሊያስረዳ የሚችል ኃላፊ ወይም ሠራተኛ እንዲመደብ ማድረግ፤

መ. በዚህ አንቀፅ ንዑስ 39.9 ፊደል ተራ ከ"ሀ" እስከ "ሐ" በተገለፀው መሠረት በተደረገ የግዥ ኦዲት በሚሰጡ አስተያየቶች መሠረት ተገቢውን ማስተካከያ ማድረግና የተደረጉ ማስተካከያዎችንም ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ፡፡

## 40 የቤት ልማት ዘርፍ እና የቤት አስተዳደር ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚዎች፤

40.1 በሚመለከታቸው የሥራ ዘርፎች የግዥ ፍላጎት በመለየት የቴክኒክ መግለጫ ተካቶበት የጨረታ ሠነድ እንዲዘጋጅ በማድረግ ለዋና ሥራ አስፈፃሚ ያቀርባል፡፡

40.2 በሚመለከታቸው የሥራ ዘርፍ ጋር የተገናኙ ውሎችን በዋና ስራ አስፈፃሚው በሚሰጠው ውክልና መሰረት ይዋዋላሉ፤ አፈፃፀማቸውን ይከታተላሉ ፡፡

40.3 ከሚመለከታቸው የሥራ ዘርፍ ጋር በተገናኘ ከአማካሪዎችና ከሥራ ተቋራጮች ጋር የሚኖረውን የሥራ ግንኙነት ያስተባብራሉ፣ ይከታተላሉ፣ ይመራሉ፡፡

## 41 የፕሮጀክት ክትትልና ኮንትራት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

42.1. የኮርፖሬሽኑን የቤት ልማት ዝርዝር የአካባቢ ልማት ፕላንና ዲዛይን፣ የታይፖሎጂ ዲዛይንና ዝርዝር ዲዛይን፣ ግንባታ፣ እና ሌሎች ተያያዥ ሥራዎችን በአማካሪዎች እና በተቋራጮች ማሰራት እንዲቻል የኮርፖሬሽኑ እንዲሁም የመንግስትን የግዥ ህግ መሠረት በማድረግ የጨረታ ሰነድ እንዲዘጋጅ በማድረግ ለኮርፖሬት ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፡፡

41.1 የጨረታ ሰነዱን ሲያዘጋጅ ከሚገዛው አገልግሎት (ዝርዝር የአካባቢ ልማት ፕላንና ዲዛይን፣ የታይፖሎጂ ዲዛይንና ዝርዝር ዲዛይን፣ ግንባታ፣ እና ሌሎች ተያያዥ ሥራዎች) ጋር የተያያዙ ስፔስፊኬሽኖችን በአግባቡ ተዘጋጅቶ መቅረቡን ያረጋግጣል፤

41.2 የጨረታ ሰነዱን አስፈላጊ መረጃዎች መሟላታቸውንና አሻሚና ለትርጉም ያልተጋለጠ ሰነድ መሆኑን ያረጋግጣል፤

41.3 የጨረታው አሸናፊ ከተለየ በኋላ ከአሸናፊው ድርጅት ጋር ውል መፈጸም እንዲቻል የውል ሰነዶችን ከህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት በጋራ ያዘጋጃል፤

41.4 ከጨረታ አሸናፊ ድርጅት ጋር ውሉ ከተፈጸመ በኋላ የሚሰራውን ሥራ (የዲዛይን፣ የግንባታ እና ሌሎች ሥራዎች) ለአሸናፊው ድርጅት በአግባቡ በማስረከብ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ያስተዳድራል፤ በየወቅቱ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ያቀርባል፤

41.5 ሥራውንና ለሥራው የሚውሉ ግብዓቶች (ግንባታውንና ለግንባታው የሚውሉትን ግብዓቶች) የጥራት ደረጃ ቁጥጥር መደረጉን ይከታተላል፤

41.6 ግንባታው በተገባው ውል መሠረት፣ የጥራት ደረጃ፣ የጊዜና የዋጋ ገደብ ተጠብቆ መሠራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፤ በበላይነትም ይቆጣጠራል፤

41.7 የተጠናቀቁ ዲዛይኖችን እና ግንባታዎችን በአግባቡ ተከታትሎ፣ ተቆጣጥሮ እና በውሉ መሠረት መሆኑን አረጋግጦ ከአማካሪዎቹ እና/ወይም ከሥራ ተቋራጮቹ ይረከባል፤

41.8 በየምዕራፉ ለአማካሪዎች እና ሥራ ተቋራጮች ክፍያዎችን መፈጸም እንዲቻል አፈጻጸማቸውን በመገመገምና በማረጋገጥ የተሰራውን ሥራ በማረጋገጥ በውሉ መሰረት የክፍያ ሰነዶችን አረጋግጦ ያቀርባል፤

41.9 የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶችን በውሉ መሰረት መጠናቀቃቸውን በማረጋገጥ ጊዜያዊና የመጨረሻ ርክክብ ይፈፅማል፤

## 43. <u>የቤቶች ጥገናና እድሳት ዳይሬክቶሬት</u>

43.1. የኮርፖሬሽኑን ቤቶች የጥገናና ዕድሳት ዲዛይን፤ የስራ ዝርዝር፣ ግንባታ፣ እና ሌሎች ተያያዥ ሥራዎችን በአማካሪዎች እና በተቋራጮች ማሰራት እንዲቻል የኮርፖሬሽኑ እንዲሁም የመንግስትን የግዥ ህግ መሠረት በማድረግ የጨረታ ሰነድ እንዲዘጋጅ በማድረግ ለኮርፖሬት ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ያቀርባል።

43.2. የጨረታ ሰነዱን ሲያዘጋጅ ከሚገዛው አገልግሎት (ዲዛይን፤ የስራ ዝርዝር፣ ግንባታ፣ እና ሌሎች ተያያዥ ሥራዎችን) ጋር የተያያዙ ስፔስፊኬሽኖችን በአግባቡ ተዘጋጅቶ መቅረቡን ያረጋግጣል፤

43.3. የጨረታ ሰነዱን አስፈላጊ መረጃዎች መሟላታቸውንና አሻሚና ለትርጉም ያልተጋለጠ ሰነድ መሆኑን ያረጋግጣል፤

43.4. የጨረታው አሸናፊ ከተለየ በኋላ ከአሸናፊው ከአሸናፊው ድርጅት ጋር ውል መፈጸም እንዲቻል የውል ሰነዶችን ከህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት በጋራ ያዘጋጃል፤

43.5. ከጨረታ አሸናፊ ድርጅት ጋር ውሉ ከተፈጸመ በኋላ የሚሰራውን ሥራ (የዲዛይን፣ የግንባታ እና ሌሎች ሥራዎች) ለአሸናፊው ድርጅት በአግባቡ በማስረከብ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ያስተዳድራል፤ በየወቅቱ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ያቀርባል፤

43.6. ሥራውንና ለሥራው የሚውሉ ግብዓቶች (ግንባታውንና ለግንባታው የሚውሉትን ግብዓቶች) የጥራት ደረጃ ቁጥጥር መደረጉን ይከታተላል፤

43.7. ግንባታው በተገባው ውል መሠረት፣ የጥራት ደረጃ፣ የጊዜና የዋጋ ገደብ ተጠብቆ መሠራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፤ በበላይነትም ይቆጣጠራል፤

43.8. የተጠናቀቁ ዲዛይኖችን እና ግንባታዎችን በአግባቡ ተከታትሎ፣ ተቆጣጥሮ እና በውሉ መሠረት መሆኑን አረጋግጦ ከአማካሪዎቹ እና/ወይም ከሥራ ተቋራጮቹ ይረከባል፤

43.9. በየምዕራፉ ለአማካሪዎች እና ሥራ ተቋራጮች ክፍያዎችን መፈጸም እንዲቻል አፈጻጸማቸውን በመገመገምና በማረጋገጥ የተሰራውን ሥራ በማረጋገጥ በውሉ መሰረት የክፍያ ሰነዶችን አረጋግጦ ያቀርባል፤

42.11 የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶችን በውሉ መሰረት መጠናቀቃቸውን በማረጋገጥ ጊዜያዊና የመጨረሻ ርክክብ ይፈፅማል፤

## 44. <u>የኮርፖሬት ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት</u>

1. የኮርፖሬሽኑን የግዢ እቅድ ያዘጋጃል፤
2. ከግዢ ጠያቂ የስራ ክፍል ጋር በመተባበር የጨረታ ሰነዶችን አዘጋጅቶ ለግዢ አጽዳቂ ኮሚቴ ያቀርባል፤
3. ኮርፖሬሽኑ የሚያስተዳድራቸውን የድርጅት እና የንግድ ቤቶች ለ3ኛ ወገን በጨረታ ሲተላለፍ በጨረታ ሰነድ ዝግጅት ፤ ሺያጭ እና አፈጻጸም ሕጉን ተከትሎ ይተገብራል ይከታተላል፤
4. በቤት ልማት ዘርፍ እና በቤት አስተዳደር ዘርፍ በኩል የሚቀርቡ የግንባታ እና የአገልግሎት ግዥ ሂደቶች ላይ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባራት ያከናውናል፡-

4.1. በብዙሀን መገናኛ ዘዴዎች በጨረታው ላይ መሳተፍ ለሚፈልጉ አካላት ጥሪ ያደርጋል፣

4.2. የጨረታ ሰነዱ ሽያጭ ጊዜ በፕሮግራሙ መሠረት የጨረታ ጊዜ በተጠናቀቀበት ዕለት የጨረታ ሳጥኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመፈራረም ሳጥኑን ያሽጋል/መታሸጉን ያረጋግጣል፤

4.3. የግዥ ጥያቄውን ካቀረበው ዳይሬክቶሬት፣ ከኮርፖሬት ኦዲት አገልግሎት ዳይሬክቶሬት፣ ከሥነ-ምግባር መከታተያ ጽ/ቤት ተወካዮች ጋር በጋራ በመሆን

የጨረታ ሳጥኑን በይፋ በመክፈት፤ በጨረታ ሰነዱ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት የተጫራቾች የቴክኒካል ሰነዶችን የቴክኒካል ግምገማ እንዲደረግ ለሚመለከተው የቴክኒክ ኮሚቴ እንዲተላለፍ ያደርጋል፤ የቴክኒካል ግምገማው ውጤት እስኪጠናቀቅ የተጫራቾችን የፋይናንሻል ሰነድ በጨረታ ሳጥኑ በመመለስ ከላይ ከተጠቀሱት ተወካዮች ጋር በመሆን ሳጥኑን ያሽጋል፡፡

4.4. የቴክኒካል ግምገማ ውጤቱ በግዥ  አፅዳቂ ኮሚቴ ከፀደቀ በኋላ የግዥ ጥያቄውን ካቀረበው ዳይሬክቶሬት፣ ከኮርፖሬት ኦዲት አገልግሎት ዳይሬክቶሬት፣ ከሥነ-ምግባር መከታተያ ጽ/ቤት ተወካዮች ጋር በጋራ በመሆን ተጫራቾች ያቀረቡትን የፋይናንሻል ሰነድ በመክፈት ዝርዝር የማወዳደሪያ ትንተና እንዲሰራ ለሚመለከተው የቴክኒክ ኮሚቴ እንዲተላለፍ ያደርጋል፤

4.5. ውጤቱን በግዥ  አፅዳቂ ኮሚቴ ሲፀድቅ ለአሸናፊ ድርጅትና ለተሸናፊ ድርጅት/ቶች የጨረታውን ውጤት ያሳውቃል፤

4.6. በጨረታ ሂደቱ ከተጫራቾች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በወቅቱ መርምሮ ምላሽ ይሰጣል፤

4.7. የግዥ መርሐ ግብሮችንና የግዥ ዕቅዶችን ያዘጋጃል፤ የግዥ ዕቅድ በማውጣት ከሠራተኞች ጋር ስለአፈፃፀሙ ስምምነት ያደርጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤ ይገመግማል፤

4.8. ከግዥ አፈፃፀም ቡድን የመወሰን አቅም በላይ የሆኑ የደንበኞች ቅሬታዎችን ይፈታል፤

4.9. በግዥ ሥራ ለተሰማሩ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በቂ ሥልጠና እንደያገኙ ያደርጋል፤

4.10. በኮርፖሬሽኑ የግዥ አፈጻጸም መመሪያ መሠረት ውሣኔ እንዲሰጥ ከተቀመጠለት ሥልጣን በላይ የሆኑ ግዥዎችን ለኮርፖሬት ሰርቪስ ዘርፍ ም/ዋና ስራ አስፈፃሚ አቅርቦ ያፀድቃል፤

5. የኮርፖሬሽኑን የግዥ አፈፃፀም በሚመለከት የኮርፖሬሽኑ የውስጥ ኦዲት፤ የኮርፖሬሽኑ ሥነ-ምግባር መከታተያ ጽ/ቤት፣ ጉዳዩ የሚመለከተው የመንግስት አካል ለሚያደርገው የግዥ ኦዲት ወይም ምርመራ ሥራ ሁኔታዎች ያመቻቻል፤

ሀ. ለኦዲት ሥራው የሚያስፈልጉ ሰነዶች በሚፈለገው ጊዜ እንዲቀርቡ ማድረግ፤

ለ. ለተመደቡት ኦዲተሮች አገልግሎት የሚሆን የስራ ቦታ እንዲመቻች ማድረግ፤

ሐ. ስለተፈፀሙት ግዥዎች አካሄድ ሊያስረዳ የሚችል ኃላፊ ወይም ሠራተኛ እንዲመደብ ማድረግ፡፡

መ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ 43.5 በተገለፀው መሠረት በተደረግ የግዥ ኦዲት በሚሰጡ አስተያየቶች መሠረት ተገቢውን ማስተካከያ ማድረግና የተደረጉ ማስተካከያዎችን ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ፡፡

6. የግዥ ሂደቶችን በየደረጃውና እንደአስፈላጊነቱ ለጠያቂ ዳይሬክቶሬቶች፣ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ሰነዶችን አባሪ በማድረግ በደብዳቤ ያሳውቃል፡፡
7. በዚህ መመሪያ ያልተጠቀሱ ሰኔ 2002 በወጣው በፌደራል የግዢ አፈጻጸም መመሪያ ላይ በአንቀጽ 6 ስር የተዘረዘሩ ተግባርና ኀላፊነት ይኖረዋል፡፡

## 44. <u>የቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጆች</u>

44.1. በሚሰጣቸው ውክልና የቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጆች በየበጀት ዓመቱ ለስራ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ጥያቄ ለሚመለከተው አካል መላኩን ይከታተላሉ፤

44.2. በዋና ሥራ አስፈፃሚ በሚሰጠው የስልጣን ውክልና መሰረት ግዥዎችን ያፀድቃል፣ ውል ይዋዋላል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

44.3. የቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጆች በየደረጃው የሚፈፀሙ ግዥዎች የገበያ ዋጋ መሰረት ያደረገ መሆኑን ይከታተላሉ፤

44.4. በሚሰጣቸው የውክልና ስልጣን ልክ የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴና የግዥ ቴክኒክ ኮሚቴ ያቋቁማሉ፤

44.5. ከግዥ ሥራ ክፍሉ የመወሰን አቅም በላይ የሆኑ የደንበኞችን ቅሬታዎች ይፈታል፤

44.6. በግዥ ሥራ ለተሰማሩ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በቂ ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፤

44.7. የሚከተሉትን ጨምሮ የኮርፖሬሽኑን የግዥ አፈፃፀም በሚመለከት የኮርፖሬት ኦዲት አገልግሎት ዳይሬክቶሬት፤ የጥራት ቁጥጥርና ክፍያ ኦዲት ዳይሬክቶሬት፣ የኮርፖሬሽኑ ሥነ-ምግባር መከታተያ ጽ/ቤት፤ ጉዳዩ የሚመለከተው የመንግስት አካል ለሚያደርገው የግዥ ኦዲት ወይም ምርመራ ሥራ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡-

ሀ. ለኦዲት ሥራው የሚያስፈልጉ ሰነዶች በሚፈለገው ጊዜ እንዲቀርቡ ማድረግ ፤

ለ. ለተመደቡት ኦዲተሮች አገልግሎት የሚሆን የስራ ቦታ እንዲመቻች ማድረግ፤

ሐ. ስለተፈፀሙት ግዥዎች አካሄድ ሊያስረዳ የሚችል ኃላፊ ወይም ሠራተኛ እንዲመደብ ማድረግ፤

መ. በዚህ አንቀፅ ንዑስ 44.7 በተገለፀው መሠረት በተደረገ የግዥ ኦዲት በሚሰጡ አስተያየቶች መሠረት ተገቢውን ማስተካከያ ማድረግና የተደረጉ ማስተካከያዎችንም ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ፡

45. **<u>የግዥ አፈፃፀም /የሌሎች እና የምህንድስና ግዥ/ ቡድን መሪዎች</u>**

45.1. የጥቃቅን ወጪ ግዥን ያፀድቃል፤

45.2. በየደረጃው ለሚከናወኑ ግዥዎች የሚቀርቡ የውሳኔ ሃሳብ ማረጋገጫ ይሰጣል፤ የገበያ ዋጋ ጥናትን ያስተባብራል፣ ይመራል፤ አደራጅቶ በማረጋገጥ ለውሳኔ ያቀርባል፤ በየደረጃው የምህንድስና፤የዕቃና የአገልግሎት ግዥ ጨረታዎችን በበላይነት ይከታተላል፣ የጨረታውን ሂደት ይቆጣጠራል፣ አረጋግጦ ለውሳኔ ያቀርባል፤

45.3. በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈፀም ግዥ ሰብሳቢ በመሆን አረጋግጦ ለግዥ አፅዳቂ ለውሳኔ ያቀርባል፤

45.4. የኮርፖሬሽኑን ወይም የቅርንጫፉን የግዥ ፍላጎት በጊዜ መርሃ ግብሩ መሰረት አደራጅቶ ለግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ወይም ለቅርንጫፉ ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ ያቀርባል፤

46. **<u>የግዥ ቡድን</u>**

46.1. በፀደቀው የግዥ ዕቅድ መሠረት ለመፈፀም የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫን ከሚመለከተው አካል ይጠይቃል፤

46.2. የጨረታ ሰነድ ያዘጋጃል፤ የጨረታ ጥሪዎችን ያካሂዳል፤ የተዘጋጁ የጨረታ ሠነዶችን ይመረምራል፣ የግምገማ ውጤት ያዘጋጃል፤ የጨረታ ማስከበሪያ ፀንቶ የሚቆየበትን ጊዜ ክትትል ያደርጋል፤ እንዲሁም የተካሄዱ የቴክኒክ እና የዋጋ ግምገማዎችን ውጤት መነሻ በማድረግ የግዥ አሸናፊውን ይለያል፤

46.3. ለአሸናፊ ተጫራቾች የአሸናፊነት መግለጫ ደብዳቤ፣ የውል ሰነድ ያዘጋጃል እና የውል አፈፃፀሞችን ይከታተላል፤

46.4. የተዘጋጁ የክፍያ ሠነዶችን ይመረምራል፤

46.5. የግዥ ሂደቱ ተጠናቅቆ ክፍያ ከተፈፀመ በኂላ ሠነዶች የተሟሉ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

46.6. የገበያ ጥናት ያካሂዳል፤

47. <u>የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት</u>

47.1. በግዥ ስራ ክፍል የሚዘጋጀው ዓመታዊ ዕቅድ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ባስገባ መንገድ መዘጋጀቱን ያረጋግጣል፣

ሀ. የተለዩት የግዥ ፍላጎቶች ከኮርፖሬሽኑ ፕሮግራሞች ጋር የሚጣጣሙ መሆኑን፣

ለ. እያንዳንዱ ፍላጎት ለማሟላት ከግዥ የተሻለ ሌላ አማራጭ አለመኖሩን፣

ሐ. እቅዱ ግዥን በጥቅል ለመፈፀም በሚያስችል መልኩ መዘጋጀቱን ፣

መ. ከኮርፖሬሽኑ ልዩ ባህርይ አንፃር ሊሟሉ የሚገባቸው ሌሎች ሁኔታዎች መሟላታቸውን፤

47.2. በግዥ የስራ ክፍል የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ የሚከተሉትን ሁኔታዎች መሟላቱን ያረጋግጣል፡-

ሀ. በኤጀንሲው ለየግዥው አይነት የተዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ የተከተለ መሆኑን፣

ለ. የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫው በዚህ መመሪያ የተገለፁትን ሁኔታዎች ያሟላ መሆኑን፣

ሐ. የመወዳደሪያ መስፈርቶቹ አድሏዊ ያልሆኑ፣ ግልፅ እና ተደራሽ መሆናቸውን፣

መ. ተገቢ ቅፃችን፣ እንደግዥው ዓይነት ሊገለጹ የሚገባቸውን ሁኔታዎች እና ሌሎችንም መሠረታዊ ጉዳዮች ማሟላቱን፣

47.3. የሚከተሉት የማጣራት ሥራዎች በማከናወን ከተወሰነው የገንዘብ መጠን በላይ የሆኑ ግዥዎችን የግምገማ ሪፖርቶችን መርምሮ ያፀድቃል፣

ሀ. ግምገማው በወጣው የጨረታ ሰነድ መሰረት መሰራቱን፣

ለ. የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የጠበቀ መሆኑን፣

ሐ. በግዥ ውሳኔ ሀሳቡ ላይ ለመድረስ የተከናወኑት ዝርዝር ግምገማዎችና አጠቃላይ የግዥ ሂደቱ ኮርፖሬሽኑ ለሚከፍለው ክፍያ ተመጣጣኙን ለማስገኘት የሚያስችሉ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

47.4. በቀረበው የግዥ ግምገማ ሪፖርት ላይ የሚሰጥ ማንኛውም አይነት የኮሚቴው ውሳኔ ምክንያታዊ መሆን ይኖርበታል፤

47.5. የግዥ አፈፃፀም መመሪያውን እና ሌሎች በኮርፖሬሽኑ የሚወጡ የአፈፃፀም ሥርዓቶች በተሻለ ሁኔታ ሊፈፀሙ የሚችሉበትን አሰራር ለኃላፊው ያማክራል፣

47.6. በኮሚቴው ስለተከናወኑ የግዥ ተግባራት፣ ስላጋጠሙ ችግሮች እና የመፍትሔ ሀሳቦች የሚገልጽ ሪፖርት ለኮርፖሬሽኑ የበላይ ኃላፊ ያቀርባል፣

47.7. በኮርፖሬሽኑ የግዥ አፈፃፀም ሂደት ውስጥ በኮሚቴው ስለተወሰኑ ውሳኔዎች በኮርፖሬሽኑ የበላይ ኃላፊ ወይም በሌላ ሥልጣን ባለው አካል ሲጠየቅ ማብራሪያ ይሰጣል፡፡

## 48. <u>የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ አወቃቀር</u>

የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴዎች ከኮርፖሬሽኑ አደረጃጀት እና የሥራ ባህሪ ጋር በተጣጣመ መልኩ በኮርፖሬሽኑ በዋናው መ/ቤት እና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ይቋቋማሉ ፡፡

## 49. <u>የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ሰብሳቢ ኃላፊነትና ተግባር</u>

49.1. የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴን የስብሰባ ቀንና ሰዓት ይወስናል፣ ስብሰባውንም ይመራል፤

49.2. የጨረታው የመክፈቻ ሥነ-ሥርዓት ቃለ-ጉባኤ፤ ኮሚቴው ባደረጋቸው ስብሰባዎችና በጨረታ ግምገማው የተደረሰበት ውሣኔ ቃለ ጉባኤና አግባብነት ያላቸው ሰነዶች ተሟልተው መቅረባቸውን ያረጋግጣል፤

49.3. ከጨረታ ሂደት ጋር የተያያዙ ተግባራት ይህን መመሪያ ተከትለው የተፈፀሙ መሆኑን ያረጋግጣል ፤

49.4. የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴው የውሳኔ ሃሳቦች እንደ አግባብነቱ ለኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በማቅረብ ያፀድቃል፡፡

## 50. <u>የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ፀሐፊ ኃላፊነትና ተግባር</u>

50.1 የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ፀሐፊ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ. በግዥ ቡድኖች እየታገዘ ማንኛውንም የግዥ ኮሚቴን የስብሰባ ቃለ-ጉባዔ እንዲያዝና፤ ኮሚቴው የተሟሉ ሠነዶችና መዛግብቶች እንዲኖሩትና በጥንቃቄ እንዲያዙ ያደርጋል፤

ለ. ከግዥ አጽዳቂ ኮሚቴው ሰብሳቢ ጋር በመነጋገር አጀንዳ ያዘጋጃል፤ የኮሚቴው ስብሰባ የሚካሄድበትን ጊዜና ቦታ ለአባላት ያሳውቃል፤

ሐ. በግዥ አፈጻጸም ሂደት ከአቅራቢዎች ጋር የተደረገ ውይይት ካለ በግዥ ቡድኖች እየታገዘ ቃለ-ጉባዔ ተመዝግቦ እንዲያዝ ያደረጋል፤

መ. በግዥ አጽዳቂ ኮሚቴው ስብሰባዎች ላይ ድምጽ ይሰጣል፤

ሠ. የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፡፡

50.2 የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት

ሀ. የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ሊሰበስብ የሚችለው ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ሲገኙ ሲሆን፤ ውሣኔ የሚተላለፈው በድምጽ ብልጫ ነው፤

ለ. የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ በውሣኔ አሰጣጥ ወቅት እኩል ድምጽ በሚኖረው ጊዜ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ተቀባይነት ይኖረዋል፤

ሐ. በድምጽ አሰጣጥ ወቅት በሃሳብ የተለየ አባል ሲኖር የተለየበት ምክንያት በቃለ-ጉባኤው እንዲሰፍር ይደረጋል፡፡

51. <u>**የቴክኒክ ኮሚቴ**</u>

በዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም እርሱ በሚወክለው የሚቋቋም እና ውስብስብ ባህሪያት ያላቸውን ግዥዎች መርምሮና ገምግሞ ለሚመለከተው አካል የውሣኔ ሃሳብ ያቀርባል፡፡ የቴክኒክ ኮሚቴው አባላት ቁጥር ሶስት እና ከዚያ በላይ ሲሆን የቴክኒክ ኮሚቴው ብዛት ደግሞ እንደአስፈላጊነቱ አንድና ከዚያ በላይ ሊሆን ይችላል፡፡

# ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 52. ተቀባይነት ያገኘ የአቅራቢዎች ዝርዝር ስለመጠቀም

52.1 የአቅራቢዎችን ዝርዝር (List suppliers) የማቋቋም (አደራጅቶ የመያዝ) ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ. ኮርፖሬሽኑ ተገቢ የሆኑ አቅራቢዎችን በአፋጣኝ እንዲለይ ለማስቻል፤

ለ. ብቃት ያላቸው አቅራቢዎችን በመምረጥ ረገድ የሚደረገውን ማጣራት ለማጠናከር፤

ሐ. ወጪ ለተደረገው ገንዘብ ተመጣኙን ጥቅም ማስገኘት እንዲቻል

መ. ከአቅራቢዎች ጋር በማደረግ ግንኙነት ከተገኘ ልምድ የተለያዩ ዘዴዎችን ለማዳበር

52.2 በማንኛውም የኮርፖሬሽኑ ግዥ ለመሣተፍ በመንግስት የአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ መመዝገብ ግዴታ ነው፡፡

ሀ. በኮርፖሬሽኑ ግዥ መሣተፍ የሚፈልጉ አቅራቢዎች እንደአግባብነቱ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር፤ ከከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር፤ ከኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ወይም አግባብ ካለው ባለሥልጣን እየተባሉ ከሚጠሩት የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡

ለ. ኮርፖሬሽኑ በሚያወጣው ጨረታ የሚሳተፍ ማንኛውም አቅራቢ ወይም ተጫራች ለመቀበል በቂ እና በተሟላ መልኩ ስለእያንዳንዱ ተጫራች ተገቢውን መረጃ መያዝ ይጠበቅበታል፡፡ በተለይ ከኮርፖሬሽኑ ጋር በተለያየ ጊዜ የሰጣቸውን የዕቃ ወይም የአገልግሎት ውል አፈፃፀም የተሸነፉበት ምክንያትም ጭምር በአጠቃላይ ጠንካራ እና ደካማ ጎናቸውን የሚገልጽ ዝርዝር መረጃ ይይዛል፡፡

52.3 በአቅራቢነት (List Suppliers) ለመመዝገብ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች፡-

ሀ. አቅራቢው የተሠማራበትን የሥራ ዘርፍ የሚገልጽ የታደሰ ንግድ ፈቃድ

ለ. ታክስ መክፈሉን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት

ሐ. ተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ከሆነ የተመዘገበበትን ማስረጃ

መ. የምክር አልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ የተሰማራ አቅራቢ ከሆነ በዚህ ንኡስ አንቀጽ በፊደል ሀ፤ለ እና ሐ ከተገለፀው በተጨማሪ ስለተሠማራበት የሙያ ዘርፍ በሚመለከተው አካል የተሰጠ ማስረጃ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ፤

ሠ. በግንባታ ሥራ ላይ የተሰማራ አቅራቢ ከሆነ በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ሀ፤ ለእና ሐ ከተገለፀው በተጨማሪ የምዝገባ ደረጃውን መስፈርት የሚያሟላ የመሣሪያ እና የሰው ኃይል ዝግጅት ያለው መሆኑን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች እንዲሁም የስራ ተቋራጭነት ሥራ እንዲሠራ በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ወይም በኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ወይም ተመሳሳይ ፈቃድ ከሚሰጡ አካላት የተሰጠውን ደረጀ የሚገልጽ መስረጃ፤

ረ. የተሽከርካሪ ጥገና አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ የተሠማራ ከሆነ ከፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን የተሠጠ ደረጃውን የሚገልጽ ማስረጃ፣

ሰ. መድሃኒት እና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎችን በማቅረብ የተሠማራ ከሆነ ከምግብ መድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን የተሠጠውን ማስረጃ፡፡

52.4 ኮርፖሬሽኑ ግዴታውን በአግባቡ ያልተወጣ አቅራቢን ከአቅራቢነት ዝርዝር ሊሠረዝ ይችላል፡፡

52.5 አቅራቢው በግዥው ውል መሠረት ግዴታውን ሳይፈጽም ሲቀር ኮርፖሬሽኑ ይህንኑ ወዲያውኑ ለኤጀንሲው እና ሌሎች አግባብነት ላላቸው ባለሥልጣን መ/ቤቶች ሪፖርት ሊያደርግ ይችላል፡፡

52.6 የአቅራቢዎች ዝርዝር በማስታወቂያ ጥሪ ተደርጎ እና በግዥ ፈፃሚው አካል ተቀባይነት ሲያገኝ ተግባራት ይሆናል፡፡

52.7 የኮርፖሬሽኑ የአቅራቢዎች ዝርዝር በየአመቱ የሚከለስ ሲሆን በጥቁር መዝገብ የተያዙ ከአቅራቢዎች ዝርዝር የሚወጡ እና አዳዲስ አቅራቢዎች ደግሞ በዝርዝሩ ውስጥ የሚካተቱ ይሆናል፡፡

## 53. ብቁ ተጫራቾች

53.1. በማንኛውም የኮርፖሬሽኑ ግዥ ለመሳተፍ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን እንዲሁም ከግዥው ልዩ ባህርይ በመነሳት ኮርፖሬሽኑ የሚያወጣቸውን ሌሎች መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፡፡

ሀ. ውል ለመዋዋል የሕግ ችሎታ

ለ. በሚገቡት ውል መሰረት ለመፈጸም የሚያስችል የሙያና የቴክኒክ ብቃት፣ የፋይናንስ አቅም፣ የመሳሪያና ሌሎች የመገልገያ ስፍራዎች፣ ግዥው የሚፈጸምበት ተግባር የስራ አመራር ችሎታ መልካም ዝናና በቂ የሰለጠነ የሰው ኃይል፤

ሐ. መረጃው እስከተገኘ ድረስ በዕዳ ያልተያዘ ፣ ያልከሰረ ወይም የስራ እንቅስቃሴውን ያላቋረጠ የንግድ ስራ እንቅስቃሴው ያልታገደ ወይም በእነዚህ ምክንያቶች ተከሶ በክርክር ላይ ያልሆነ

መ. በኮርፖሬሽኑ ውስጥም ሆነ በሌሎች ድርጅቶች ባለው የውል አፈፃፀም ችግር ምክንያት በጥቁር መዝገብ ውስጥ ያልተመዘገበ፤

ሠ. አግባብነት ባላቸው የግብር ህጎች መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታዎቹን የተወጣ፡፡

53.2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 53.1 የተጠቀሱት እንደተጠበቀ ሆነው ተጫራቾች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማስረጃዎች ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

ሀ. ኢትዮጵያዊ የሆኑ ተጫራቾች በመንግስት የአቅራቢዎች መዝገብ ውስጥ የተመዘገቡ መሆኑን የሚያመላክት የዋና ምዝገባ የምስክር ወረቀት

ለ. ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ተዛማጅነት እና አግባብነት ያላቸው የጽሑፍ ማስረጃዎች

ሐ. አግባብነት ያለው የንግድ ፈቃድ ፤

መ. የግብር ክፍያ ምስክር ወረቀት እንደሁም እንደአስፈላጊነቱ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ምዝገባ

ሠ. እንደአስፈላጊነቱ ሌላ ተፈላጊ የሙያ በቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ፡፡

ረ. ኮርፖሬሽኑ አቅራቢው በዚህ አንቀጽ የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆኑን ለማጣራት የአቅራቢውን ኘላንት ወይም ፋብሪካ የሚገዛውን ዕቃ ወይም አገልግሎት

መሠረት በማድረግ ከኮርፖሬሽኑ ባለሙያዎች ወይም የሥራ ኃላፊዎች የተውጣጣ ቡድን እንዲጎበኝ ሊያደረግ ይችላል፡፡

## 54. የዕጩ ተወዳዳሪዎች ወይም ተጫራቾች አቤቱታ የማቅረብ መብት

በአንቀጽ 55 ላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮርፖሬሽኑ በዚህ መመሪያ የተመለከተውን በአግባቡ ባለመፈጸሙ ምክንያት ጉዳት ወይም ኪሳራ ደርሶብኛል ወይም ሊደርስብኝ ይችላል የሚል ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች ጨረታው እንደገና እንዲታይለት ወይም ሂደቱ እንዲጣራለት ውሳኔውን ለሰጠው አካል ወይም ለኮርፖሬሽኑ ሥራ አስፈፃሚ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

## 55. አቤቱታ ማቅረብ የማይቻልባቸው ሁኔታዎች ፤

55.1. በተወሰነው የግዥ ዘዴ ምርጫ ላይ፤

55.2. በተገለፀው የተጫራቾች አመራረጥ ስርዓት ላይ፤

55.3. ለአገር ውስጥ አቅራቢዎች፣ ምርቶች እናየግንባታ ዘርፍ የተሰጠ ልዩ አስተያየት ላይ፤

55.4. ጨረታን የመጫረቻ ሰነድን ወይም የዋጋ ማቅረቢያን ውድቅ ለማድረግ በተሰጠ ውሣኔ ላይ፤

55.5. ኮርፖሬሽኑ የግምገማውን ውጤት ወይም ለቀረበለት አቤቱታ ውሳኔ በጽሑፍ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 7 /ሰባት/ የሥራ ቀናት ካለፉ ፤

55.6. በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ መሠረት ውል ከተፈረመ፤

55.7. የኮርፖሬሽኑን የሥራ ባህሪ መሠረት አድርጎ በተዘጋጀ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ላይ፤

55.8. በውስን ጨረታና በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈፀም ግዥ በተከናወነ የተጫራቾች አመራረጥ ላይ፤

55.9. በጨረታ ሰነድ ላይ አስቀድሞ በሰፈረ የተጫራቾች ማወዳደሪያ መስፈርት ላይ፤

## 56. ለኮርፖሬሽኑ የሚቀርብ አቤቱታ የሚጣራበት ስርዓት

56.1. ግዥ ፈፃሚ አካላት የጨረታውን ወይም የአቤቱታውን ውጤት ለተጫራቾች ከገፀሉበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 7/ሰባት/ የሥራ ቀናት ከመሙላቱ በፊት የግዥውን ውል መፈረም የለባቸውም፡፡

56.2. በግዥ አፈፃፀመ ሂደት ጉዳት ወይም በደል ደርሶብኛል የሚል አቅራቢ ወይም ተጫራች ለአቤቱታው መሠረት የሆነውን ውሳኔ ካወቀበት ወይም ማወቅ ከነበረበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 7/ሰባት/ የሥራ ቀናት ጊዜ ውስጥ አቤቱታውን በመጀመሪያ ማቅረብ ያለበት

ውሳኔውን ለሰጠው አካል ሆኖ በተሰጠው ምላሽ ካልረካ ለሚመለከተው የበላይ አካል ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ከዚያ ጊዜ በኋላ ለኮርፖሬሽኑ የሚቀረብ አቤቱታ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

56.3. አቤቱታውን ባቀረበው እጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች እና በግዥ ሥራ ክፍል መካከል ካልተፈታ አቤቱታው በሚመለከተው አካል ወይም በዋና ሥራ አስፈጻሚ ቀርቦ ውሳኔ ማግኘት አለበት፡፡

56.4. በሚመለከተው አካል ያልተፈታ አቤቱታ ለኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ቀርቦ ውሳኔው በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ በጽሑፍ መሰጠት አለበት፡፡ ውሳኔውም ለውሳኔው መሰረት የሆነውን ምክንያት እና አቤቱታው በሙሉ ወይም በከፊል ተቀባይነት ያገኘ ከሆነ የሚወሰደውን የማስተካከያ እርምጃ ማመላከት አለበት፡፡

56.5. በኮርፖሬሽኑ የተሰጠው ውሳኔ ግለባጭ ውሳኔው በተሰጠ በ5 /አምስት / የስራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ላቀረበው ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች እንዲደረስ መደረግ አለበት፡፡

56.6. ከዚህ በላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተጫራቾች የቴክኒክና የዋጋ የመጫረቻ ሠነዳቸውን፡፡ በተለያዩ ሁለት ፖስታዎች እንዲያቀርቡ በተደረገበት ጨረታ፤

ሀ. የቴክኒክ ግምገማ ውጤቱን ኮርፖሬሽኑ ለሁሉም በጨረታው ተሳታፊ ለሆኑ ተጫራቾች በእኩል ጊዜ በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

ለ. ማንኛውም ተጫራች የቴክኒክ ግምገማው አፈፃፀም የግዥ የአፈፃፀም መመሪያውን እና የጨረታ ሰነዱን መሠረት አድርጎ አልተከናወነም የሚል ቅሬታ ካለው ፣ ቅሬታውን በ5 የስራ ቀን ውስጥ ማቅረብ እንደሚችል ኮርፖሬሽኑ የቴክኒክ ግምገማ ውጤቱን ተጫራቾች በሚያሳውቅበት ደብዳቤ ላይ ማመላከት ይኖርበታል፤

ሐ. የቴኪኒክ ግምገማውን በሚመለከት ለቀረበው አቤቱታ የግዥ ጨረታ ኮሚቴ የተሰጠው ውሣኔ የግዥ መመሪያውን እና የጨረታ ሰነዱን የጠበቀ አለመሆኑን ማረጋገጥ የሚችል ተጫራች የኃላፊውን ውሳኔ ባወቀ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለሚቀጥለው ኃላፊ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

መ. ኮርፖሬሽኑ የዋጋ መወዳደሪያ ሀሳብ የያዘውን ኤንቬሎፕ ሊከፍት የሚችለው የቴክኒክ ግምገማ ውጤቱን ለተጫራቾቹ ካሳወቀ ከአምስት የስራ ቀናት በኋላ ይሆናል፡፡ ሆኖም የቴክኒክ ግምገማውን በሚመለከት ለቀረበው አቤቱታ የኮርፖሬሽኑ የግዥ አፅዳቂ

ኮሚቴ በሰጠው ወሳኔ ባለመስማማት በተገቢው ጊዜ ውስጥ ለኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቤቱታ ያቀረበ ከሆነ ዋና ስራ አስፈጻሚ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ የዋጋ መወዳደሪያ ሀሳብ የያዘውን ኤንቬሎፕ ሳይከፍት እንደታሸገ ማቆየት ይኖርበታል፡፡

ሠ. አቤቱታ የቀረበበት ማንኛዉም ግዥ የሚጣራዉ ለጨረታ የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ እና የኮርፖሬሽኑን የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ይሆናል፡፡

ረ. እንደ ነገሩ ሁኔታ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ነው ሊያሰኙ የሚችሉ ምክንያቶች በተመሳሳይ ፤ውሉ እንዳይፈጸም በመንግስት የሚደረግ ክልከላ፤ እንደ መሬት መናወጥ፣ መብረቅ፣ ማዕበል እና ይህን የመሳሰሉ የተፈጥሮ አደጋዎች፤ የውጭ አገር ወይም የሀገር ውስጥ ጦርነት፤ ውል የገባው ወገን መሞት ወይም ባልታሰበ ሁኔታ የሚደርስበት ከባድ አደጋ ወይም ጽኑ ሕመም፤ በፍትሐብሔር ሕግ የተዘረዘሩ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ነው የሚያሰኙ ምክንያቶች ናቸው ፡፡

56.7. ግልጽ የሆነ የተቃራኒ የውል ቃል ከሌለ በቀር ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች ተደርገው ሊቆጠሩ አይችሉም፡፡

ሀ. በተዋዋይ ዘርፍ ወይም ሥራውን ከሚያከናውንበት ባንደኛው የመስሪያ ቤት ቅርንጫፍ ውስጥ የተደረገ የሠራተኛ አድማ ፤

ለ. ለውሉ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ አቅርቦቶች ዋጋ መወደድ ወይም መርከስ፤

ሐ. ተዋዋይ ያለበትን የውል ግዴታ አፈፃፀም የሚያከብድበት አዲስ ሕግ መውጣት፤

56.8. አቤቱታ የቀረበበት ማኛውም ግዥ የሚጣራው ለጨረታው የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ፤ እና በኮርፖሬሽኑ የሚተላለፍ ማናቸውም ውሳኔ እንዲሁም ለውሳኔው መሠረት የሆኑት ምክንያቶች እና ሁኔታዎች የግዥውን አፈጻጸም ሥርዓት የሚያሳዩ ሠነዶች አካል ሆነው መመዝገብ አለባቸው ፡፡

56.9. የቅሬታ አቀራረብ አፈፃፀምን በተመለከተ በቅሬታ መቀበያ መሠረት ይሆናል፡፡

## 57. <u>ኮርፖሬሽኑ የግዥ አፈፃፀም ሂደትን ማገድ ስለመቻሉ</u>

57.1. አቤቱታው ፍሬ ነገር ያለው እና እውነት መሆኑ ከተረጋገጠ የግዥው አፈጻጸም ሥርዓት ያለመታገዱ በተጫራቹ ላይ ሊስተካከል የማይችል ጉዳት የሚያስከትል

መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን እንዲሁም አቤቱታው ተቀባይነት የሚያገኝ መሆኑ ሲገመት እና የእገዳው ውሳኔ መተላለፍ የኮርፖሬሽኑን እና የሌሎችን አቅራቢዎች ጥቅም የማይጎዳ ሲሆን ጉዳዩ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ ጨረታው ታግዶ እንዲቆይ መደረግ ይደረጋል፡፡

57.2. የግዥ ውል ከተፈረመ በኋላ ክብደት የሚሰጠው አቤቱታ የቀረበ ሲሆን እና ይህም አቤቱታ በአንቀጽ 60 የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ሆኖ ሲገኝ ኮርፖሬሽኑ ጉዳዩ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ የግዥውን አፈፃፀም ታግዶ እንደቆይ ሊያደረግ ይችላል፡፡

57.3. ኮርፖሬሽኑ በአስቸኳይ መሟላት ያለበትን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የግዥው አፈፃፀም መቀጠል እንዳለበት ካረጋገጠ በአንቀጽ 52.1 እና 52.2 የተመለከተው እገዳ ተፈፃሚ አይሆንም፤

57.4. በኮርፖሬሽኑ የሚተላለፍ ማናቸዉም ውሳኔ እንዲሁም የውሳኔው ምክንያቶች እና ሁኔታዎች የግዥውን ሰርዓት የሚያሳዩ ሰነዶች አካል ሆነው መመዝገብ አለባቸው፣

## 58. <u>ልዩነቶች</u>

በግዥ ሂደት ወቅት የሚያጋጥሙ ከመመሪያው ውጭ የሆኑ አሠራሮች ለዋናው ሥራ አስፈጻሚ ቀርበው ሊወሰኑ ይገባል፡፡

## 59. <u>የግዥ ሠነዶች</u>

59.1. ኮርፖሬሽኑ ከግዥ ጋር በተያያዙ መዝገቦችን እና ሠነዶችን ግዥው ከተፈጸመበት ቀን አንስቶ የኦዲት ምርመራው ከተከናወነ በኋላ ለተጨማሪ 10 ዓመታት ማቆየት አለበት፡፡

በዚህ ዓይነት የሚያዙት መረጃዎች የሚከተሉትን ይጨምራል፡፡

ሀ. የሚገዙትን ዕቃዎች ፣ የግንባታ ሥራዎች ወይም አገልግሎቶች አጭር መግለጫ

ለ. የጨረታ ማስታወቂያ

ሐ. የጨረታ መወዳደሪያ ሃሳብ ወይም የዋጋ ማቅረቢያ ያቀረቡ አቅራቢዎች ስምና አድራሻ እንዲሁም በጨረታው አሸናፊ የሆኑ ተጫራቾች ስምና አድራሻ ፤

መ. ለጨረታ ግምገማ የተዘጋጀውን መስፈርት እና ተፈፃሚ የተደረገበትን ሁኔታ ፤ የጨረታ ግመገማና የውድድሩን አፈፃፀም እና ከተወዳዳሪዎች የቀረበውን የመወዳደሪያ ሃሳብ እና የዋጋ ማቅረቢያ የሚያሳይ አጭር መግለጫ፤

ሠ. ከግልጽ ጨረታ ውጪ ሌሎች የግዥ ዘዴዎች መከተል የተመረጠበትን ምክንያት

59.2. ከአሸናፊው ጋር ውል ከተፈረመ ወይም በማናቸውም ምክንያት ውሉ ከተቋረጠ በኋላ የግዥውን ዝርዝር አፈፃፀም የሚያሳየው መረጃ በጨረታው ዕጩ ተሳታፊ የሆኑ ተወዳዳሪዎች ሲጠይቁ እንዲያዩት መደረግ አለበት፡፡ ይሁን እንጂ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ወይም ፍርድ ቤት ካልታዘዘ በስተቀር ኮርፖሬሽኑ የሚከተሉትን መረጃዎች መስጠት የለበትም፡፡

ሀ. የመረጃው ይፋ መሆን በሕግ የማይፈቀድ፤ የሕግ አፈፃፀም የሚያሰናክል የሕዝብን ጥቅም የሚቃረን የተዋዋዮችን ሕጋዊ የንግድ ጥቅም እንዲሁም ቀና ውድድርን የሚጎዳ ከሆነ

ለ. በአንቀፅ 59.1 “መ” በተመለከተው መሰረት በማሳጠር የተዘጋጀውን ሠነድ ካልሆነ በስተቀር ከተጫራቾች የቀረበውን የመወዳደሪያ ሃሳብ ከመመርመር እና ከመገምገም ተግባር ጋር የተያያዙ መረጃዎችን እና ተጫራቾች ያቀረቧቸውን የመወዳደሪያ ሃሳቦች እና የጨረታ ሠነዶች ይዘት የሚገልጹ መረጃዎች፡፡

# ክፍል ሰባት

## የኮርፖሬሽኑ የግዥ ሥነ-ምግባር ደንብ

### 60. የግዥ የሥነ-ምግባር ደንብ

60.1. ትርጓሜ

ሀ. ይህ የሥነ-ምግባር ደንብ በኮርፖሬሽኑ ግዥ በመፈፀም ሥራ ላይ የተሠማሩ ሠራተኞችን ሥነምግባር የሚመሩ ደንቦችን በዝርዝር ያስቀምጣል፡፡ይህ ደንብ በሕግ የተደነገጉ የሥነ-ምግባር ደንቦችንና በተጨማሪም ተገቢነት ያላቸውን ሌሎች የሥነ-ምግባር ደንቦችን ይጨመራል፡፡

ለ. ኮርፖሬሽኑ የሚፈጽማቸው ውሎች በሚጠይቁት የቅርብ ክትትልእንዲሁም የዕቃና የአገልግሎት ግዥው መጠን ከፍተኛ በመሆኑ የተነሳ የኮርፖሬሽኑ ግዥ ልዩ የሥነ ምግባር ባህርይ ይጠይቃል፡፡

60.2. መርሆዎች

ኮርፖሬሽኑ በሚፈጽማቸው ግዥዎች የሚሳተፉ ሰዎች ሊከተሏቸው የሚገባቸው መሪ ሃሳቦች የሚከተሉት ናቸው፤

ሀ. በግል ጥቅማቸው እና በግዥ ኃላፊነታቸው መካከል ግጭት ስለመኖሩ ጥርጥር የሚያሳድር መሆን የለበትም፤

ለ. የማናቸውም ግለሰብ ድርጊት በስጦታ ወይም በማናቸውም ጥቅም በመደለል አንድን ሰው ወይም ድርጅት የደገፈ ወይም የተቃወመ መሆኑን የሚያሳይ ስሜት የሚፈጥር መሆን የለበትም፤

ሐ. ከአቅራቢዎች ጋር የሚደረግ ግንኙነት ግልጽ፤ ትክክለኛ እና አድልዎ የሌለበት መሆን አለበት፤

መ. ሥነ-ምግባራዊአፈፃፀም ተገቢ በሆኑ ሥርዓቶች እና አሠራሮች መበረታታት እና መደገፍ ይኖርበታል፤

ሠ. የኮርፖሬሽኑ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ በሥራ አጋጣሚ የተመለከታቸውን የተፈጠሩ ወይም ሊፈጠሩ የታሰቡ የሙስና ተግባራትን ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ የሚኖርበት ሲሆን ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም የሚያደርገው ጥቆማ በማስረጃ የተደገፈ መሆኑን ማረጋገጥ እና የታሰበውን የሙስና ተግባር ሊደግፍ ከሚችል ማንኛውም ተግባር ራሱን መጠበቅ ይኖርበታል፤

## 61. <u>የጥቅም ግጭትን ስለማሳወቅ</u>

61.1. በኮርፖሬሽኑ በግዥ ሥራ ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የተሰማራ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ከሚሰራው ሥራ ጋር በተገናኘ የሚሰጠው ውሳኔ በማንኛውም መልኩ ራሱን ወይም ቤተሰቡን ሊጠቅም የሚችል መሆኑን ሲረዳ ከሥራው ጋር የተገናኘ የጥቅም ግጭት መኖሩን በማሳወቅ ከግዥ ሂደቱ ሥራ ራሱን ማግለል ይኖርበታል፡፡ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ላይ ቤተሰብ ማለት የመጀመሪያ የሥጋ ዝመድና የቅርብ ዝምድና የቅርብ ጓደኝነት የንግድ ግንኙነት እና ሽርክና ያለው እንዲሁም ከተጫራቹ ጋር ያለው የቅርብ ግንኙነት በግዢ ውሳኔ ላይ ተጽዕኖ ሊፈጥር ይችላል የሚል እምነት ሲኖር ማለት ነው፡፡

61.2. ኮርፖሬሽኑ በግዥ ሥራ ላይ የተሳተፈ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ከሚሰራው ሥራ ጋር በተያያዘ የጥቅም ግጭት እንዳለው ከማንኛውም ምንጭ መረጃ ሲደርሰው፤

ሀ. ሠራተኛው ወይም ኃላፊው በቀረበው የጥቅም ግጭት ጉዳይ ላይ አስተያየቱን በጽሑፍ እንዲሰጥ ያደርጋል፤

ለ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ “ሀ” እና ተገቢ ነው ብሎ ባመነባቸው መንገዶች ተጨማሪ መረጃ በሰባሰብ ሠራተኛው ወይመ ኃላፊው ከያዘው የግዥ ሥራ ጋር በተያያዘ የጥቅም ግጭት እንዳለው ወይም እንደሌለው ይወስናል፤

ሐ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ “ለ” ኮርፖሬሽኑ ሠራተኛው ወይም ኃላፊው ከሚሠራው የግዥ ሥራ ጋር በተያያዘ የጥቅም ግጭት መኖሩን ሲያረጋግጥ፤ ሠራተኛውን ወይም ኃላፊውን ከሒደቱ እንዲገለል ያደርጋል፤ ሠራተኛው ወይም ኃላፊው በሒደቱ ተሳትፎባቸው ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮች እንደገና እንደታዩ ያደርጋል፤ ሠራተኛው ወይም ኃላፊው የጥቅም ግጭቱን ያላሳወቀው ከግንዛቤ ጉድለት ነው ብሎ ካላመነ በስተቀር በሠራተኛው ወይም በኃላፊው ላይአስተዳደራዊ እርምጀ ይወስዳል፡፡

61.3. በኮርፖሬሽኑ ግዥ ሥራ ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚሳተፈ ማንኛውም የኮርፖሬሽኑ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ወይም አቅራቢዎች እኩል የመወዳደርና ውል የመፈጸም ዕድም እንዳያገኙ የሚያደረግ ማንኛውንመ ተግባር መፈፀመ የለበትም፡፡ ለዚህም፤

ሀ. በጨረታ ጥሪ ሁሉም ዕጩ ተወዳዳሪዎች በቂመረጃ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ የሚዘጋጀው የጨረቻ ሰነድ በጨረታው ለመሳተፊ እና ተመራጭነት ሊያገኝ የሚችል የመጫረዣ ሰነድ ለማዘጋጀት የማያስችለ የተሟላ እና ግልጽ መረጃ መያዙን ማረጋገጥ፤

ለ. በጨረታ ሰነድ የተገለጸው ማንኛውም የመወዳደሪያ መስፈርትመ ሆነ የፍላጎት መግለጫ ዝርዝር የተወሰነ ዕጩ ተወዳዳሪን ሊጠቅም በሚችለ መልኩ አለመዘጋጀቱን ማረጋገጥ፤

ሐ. የጨረታው ውጤት ለሁሉምተሳታፊዎች በአኩል ጊዜ መገለጹን ማረጋገጥ፤

መ. በውል ሰነድ ዝግጅት ለአቅራቢዎች የሚሰጠው ኃላነት ግደታቸውን ሆነ ብሎ ለማቅለል ወይም ለማክበድ ያላለመ እና አስከተቻለ ድረስ ተመሳሳየ ውል ለሚፈርሙ አቅራቢዎች ተመሳሳይ ይዘት ያለው ውል ሆኖ መዘጋጀቱን ማረጋገጥ፤

ሠ.በውል አፈጻጸም ወቅት ክፍያን ቁጥጥርን የመረጃ ልውውጥን እና የመሳሰሉት ተግባራት በእኩልነት ለሁሉም አቅራቢዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ማረጋገጥ፡፡

62. <u>ስጦታና መስተንግዶ</u>

62.1. የግዥ ሠራተኛ ከተጫራቾች ወይም በጨረታ ሊሳተፉ ይችላሉ ተብለው ከሚገመቱ ስጦታ መቀበል የለበትም፡፡ መስተንግዶን አና ስጦታን መቀበል የሚከለክለው ደንብ በተዘዋዋሪ መንገድ እንዲጣስ ሙከራ ማድረግ ሊሆን ስለሚችል የግዥ ሠራተኛ መስተግንዶ አና ስጦታ መቀበል አይኖርበትም፤

62.2. የግዥ ሠራተኛ እና ኃላፊዎች በግዥ ሥራቸው ላይ ተጽዕኖ የሚያስድር ወይም ሊያሳድር የሚችል ምንም ዓይነት ስጦታ ወይም የገንዘብ ዋጋ ያለውን ነገር ወይም አገልግሎት ከሦስተኛ ወገን መቀበል የለባቸውም፡፡ ለዚህ ንዑስ አንቀጽ አፈፃፀም የግዢ ሠራተኞች እና ኃላፊዎች የሚከተሉትን ያካተተ ተገቢ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

ሀ. የገንዘብ ዋጋ ያለውን ስጦታ በተለየ ለኮርፖሬሽኑ አቅራቢ/ ዕጩ አቅራቢ ከሆነ አካል አለመቀበል፤

ለ. የሥራ ዕድል ለራሱ ወይም ለቤተሰቡ አለመቀበል ፤

ሐ. በግል በሚደረግ ግዥ ላይ ለኮርፖሬሽኑ አቅራቢ /ዕጩ አቀራቢ ከሆነ አካል የተለየየዋጋ ቅናሽ ወይም አገልግሎት አለመቀበል፤

62.3. በሥራው ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል የግብዣ ፕሮግራም መቀበል አይቻልም፡፡ ሆኖም ግብዣው በዋና ሥራ አስፈፃሚ ሲታመንበተና ሲፈቀድ በውጭ በአገር ውስጥ የሚካሄድ እና ጉዞን ሊጨመር የሚችል ጉብኝነት በሚከተሉት ሁኔታዎች ማካሄድ ይቻላል፡፡

ሀ. የረዥም ጊዜ ውል ማድረግ ሲያስፈልግ እና ጉብኝት ማድረጉ የዕቃውን ጥራት ከማረጋገጥ አንፃር ጠቀሜታ ይኖረዋል የሚል እምነት በሚመለከት የግዢ አፀዳቂ ኮሚቴው ሲታመንበት

ለ. በሁለት ደረጃ ጨረታ ወቅት በመጀመሪያው ደረጃ ላይ የዕጩ ተወዳዳሪዎችን የጨረታ ሃሳብ በሠነድ ብቻ በማየት በቂ መረጃ አይገኝም ተብሎ ሲታመን እና ጉብኝት ማድረጉ የተሻለ ሆኖ ለሁሉም እጩ ተወዳዳሪዎች እኩል እድል በመስጠት ጉብኝት ማድረግ ለኮርፖሬሽኑ የተሻለ ጥቅም ያስገኛል ተብሎ በግዥ አፀዳቂ ሲታመንበት፤

ሐ. በሁለት ደረጃ ጨረታ ወቅት በሁለተኛው ደረጃ አሸናፊው ተለይቶ እና የአሸናፊነት መግለጫ ተሰጥቶ ውል ከመፈረሙ በፊት ዕቃው በኮርፖሬሽኑ በጸደቀው የጠቀሜታ ዝርዝር መሰረት እንደሚቀርብ በጉብኝት መረጋገጡ አስፈላጊ መሆኑ የግዢ አፀዳቂ ሲያምንበት፤

62.4. ከላይ በንዑስ አንቀፅ (2)ላይ የተቀመጠው ቢኖርም ሠራተኛው ወይም ኃላፊው አቅራቢው /ዕጩ አቅራቢው ለማስታወቂያነት አገልግሎት የሚያዘጋጃቸው የውስጥ እሴት እንጂ የገበያ ዋጋ የሌላቸው በነጻ የሚታደሉ ስጦታዎችን መቀበል ይችላሉ፡፡

## 63. <u>የመረጃዎች ምሥጢርነት</u>

63.1. በምሥጢር የተያዘ የንግድ መረጃ በምሥጢርነት መጠበቅ አለበት፡፡ ለግል ፍላጎት ወይም በውድድር ላይ ተጽዕኖ በሚያሳድር መንገድ ጥቅም ላይ መዋል የለበትም፤

63.2. በተመሳሳይ የተለዩ ውሎችን የሚመለከቱ መረጃዎች፤ ውሎች ወይም የአሠራር ሥርዓቶች የግዥ ኃላፊው ካልተፈቀደ በስተቀር ለመገናኛ ብዙኃን መገለጽ የለባቸውም፤

63.3. የኮርፖሬሽኑ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ከግዢ ሥራ ጋር በተገናኘ ያወቃቸውን የኮረፖሬሽኑን ወይም የዕጩ ተወዳዳሪዎችን ወይም የአቅራቢዎችን ሚስጥራዉ መረጃ መጠበቅ ይኖርበታል፡፡ ለዚህም፤

ሀ. ውድድርን ሊገድብ የሚችል ወይም ለተወዳዳሪዎች ፍትሐዊ ያልሆነ ጥቅም የሚያስጥ ወይም የኮርፓሬሽኑን ጥቅም ሊጎዳ የሚችለ መረጃ በልዩ ሁኔታ በኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች ካልተፈቀደ በስተቀር ለማንኛውም አካል አለመስጠት ፤

ለ. ኮርፖሬሽኑ በውል አፈፃፀም ወቅት ከአቅራቢዎች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት የኮርፖሬሽኑን ውሳኔ እና መረጃ መጠበቅ ፤

ሐ. የዕጩ ተወዳደሪዎችን መረጃ እና የግምገማ ሂደት ውጤቱ በኮርፖሬሽኑ ከመገለፁ በፊት ለማንኛውም አካል አለማሳወቅ፡፡

## 64. ተገቢ ግንኙነቶች

64.1. የግዥ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ለሁሉም አቅራቢዎች ታማኝ ፤ ትክክለኛ እና አድልዎ የማያሳዩ መሆን አለባቸው፡፡ አቅራቢዎችን ማሳሳት ወይም በማንኛውም መንገድ መጫን የለባቸውም፤

64.2. ለዕጩ ተወዳዳሪዎች እና አቅሪቢዎች እኩል የመወዳደር እና ውል የመፈጸም እድል እንዳያገኙ የሚያደርግ ማንኛውም ተግባር መፈፀም የለበትም፡፡ ለዚህም፡-

ሀ. በጨረታ ጥሪ ሁሉም ዕጩ ተወዳዳሪዎች በቂ መረጃ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ በጨረታው ለመሳተፍ እና ተመራጭነት ሊያገኝ የሚችል የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት የሚያስችል የተሟላ እና ግልጽ መረጃ መያዙን ማረጋገጥ፤

ለ. በጨረታ ሰነዱ የተገለፀው ማንኛውም የመወደሪያ መስፈርትም ሆነ የፍላጎት መግለጫ ዝርዝር የተወሰነ ዕጩ ተወዳዳሪን ሊጠቅም በሚችለ መልኩ አለመዘጋጀቱን ማረጋገጥ፤

ሐ. የጨረታው ውጤት ለሁሉም ተሳታፊዎች መገለጹን ማረጋገጥ፤

መ. በውል ሰነድ ዝግጅት ለአቅራቢዎች የሚሰጠው ኃላፊነት ግዴታቸውን ሆነ ብሎ ለማቅለል ወይም ለማክበድ ያላለመ እና እስከተቻለ ድረስ ተመሳሳይ ውል ለሚፈርሙ አቅራቢዎች ተመሳሳይ ይዘት ያለው ውል ሆኖ መዘጋጀቱን ማረጋገጥ፣

ሠ. በውል አፈፃፀም ወቀት ክፍያን፤ ቁጥጥርን፤የመረጃ ልውውጥን እና የመሳሰሉትን ተግባራት በእኩልነት ለሁሉም አቅራቢዎች ተግባራዊመሆኑን ማረጋገጥ፡፡

## 65. የኃላፊነት መነጣጠል እና የሥራ ዝውውር

ገቢ የተደረጉ ዕቃዎችን የማረጋገጥ እና የክፍያ መጠየቂያን የማጽደቅ ኃላፊነቶችንና የመሳሰሉትን ለአንድ ሰራተኛ ሊሰጡ የማይገቡ ኃላፊነቶች መነጣጠል አለባቸው፡፡ ሥነ-ምግባር የጎደላቸው ተግባሮች እንዳይፈፀሙ መከላከል የሚያስችል የኃላፊነት መነጣጠል እንዲኖር ሥራዎች በምን መንገድ እንደሚከፋፈሉ የሥራ መሪዎች ማሰብ ይኖርባቸዋል፡

## 66. መደበኛ እና ልዩ ኦዲት

ኮርፖሬሽኑ የቁጥጥር ሥርዓት ያለ እና የሚሠራ መሆኑን ለማረጋገጥ የግዥ እንቅስቃሴዎችን በሚመለከት ያላሰለሰ ኦዲት መደረጉን መከታተል አለበት፡፡ የዚህ አይነቱ ኦዲት በኮርፖሬሽኑ የውስጥ ኦዲት እንዲሁም በኮርፖሬሽኑ ስነምግባር መከታተያ ጽ/ቤት፣በጥራት ቁጥጥርና የክፍያ ኦዲት ዳይሬክቶሬት በኩል መከናወን አለበት፡፡ ሆኖም በውጪ ኦዲተሮች ተጨማሪ ኦዲት ሊደረግ ይችላል፡፡ በኦዲት ግኝት መሠረት ተገቢው ማስተካከያ ይደረጋል፡፡

## 67. ከዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚጠበቅ ሥነ-ምግባር

በኮርፖሬሽኑ ግዢ የሚሳተፉ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚከተሉትን ዋና ዋና የሥነ ምግባር መርሆዎች መከተል አለባቸው፡-

67.1. ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም አቅሪቢ በኮርፖሬሽኑ “ግዢ ሥራ ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ለተሠማራ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ራሱ ወይም በሦስተኛ ወገን በኩል በዚህ መመሪያ አንቀፅ 62 ሥር የተጠቀሰውን ስጦታ መስጠት የለበትም፤

67.2. ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም አቅራቢ የሚያውቀውንና የኮርፖሬሽኑ በግዢ አፈፃፀም ወይም በውል አስተዳደር ወቅት ለሚሰጠው ውሳኔ ይረዳዋል ብሎ የሚገመተውን መረጃ ለኮርፖሬሽኑ መግለጽ አለበት፤

67.3. ኮርፖሬሽኑ በሚያደርገው የግዢ አፈፃፀም በመስኩ በተሠማራ ሌላ ተወዳዳሪ ጋር በመነጋገር ዋጋ መስጠት፤ ኮርፖሬሽኑን ሊጎዳ የሚችል መረጃ መለዋወጥ ወይም በግዢ አፈፃፀሙ ለመሳተፍ የሌላ ተወዳዳሪን ሠነድ ወይም መረጃ መጠቀም የለበትም፤

67.4. ኮርፖሬሽኑ ግዢ አፈፃፀም ሊፈጸም የታሰበን የሙስና ተግባር ለሚመለከተው አካል የሙስና ተግባረ ተባባሪ ሆኖ አለመገኘት፡፡

## 68. የግዥ መመሪያውን ስለማስተዋወቅ

አቅራቢዎች የኮርፖሬሽኑን የግዥ አካሄድ ፍላጎት ደንብ እና ሥርዓት ጠንቅቀው እንዲያውቁ ኮርፖሬሽኑ የግዢ መመሪያውን አቅራቢዎች በቀላሉ ሊረዱት በሚችሉበት ሁኔታ አዘጋጅቶ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 69. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች፤

ይህ መመሪያ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተወሰኑ ውሳኔዎች እና በሂደት ላይ ያሉ ግዥዎች ኮርፖሬሽኑ ቀድሞ ሲገለገልበት በነበረው በፌደራል የግዥና ንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት የሚፈጸሙ ይሆናሉ፤

## 70. የግዥ መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ ለኮርፖሬሽኑ የሥራ አመራር ቦርድ ቀርቦ ሲፈቀድ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## 71. የተሻሩ መመሪያዎች

1 ከዚህ በፊት ሲፈፀምበት የነበረው የግዥ መመሪያ ተፈፃሚ አይሆንም ፡፡

2 ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛዉም ዓይነት መመሪያ እና ልምዳዊ አሠራሮች በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸዉም፡፡

## 72. የግዥ መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ የግዥ መመሪያ በኮርፖሬሽኑ የሥራ አመራር ቦርድ ከፀደቀበት ----------------- ቀን 2011 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

……………………………………………………

ወ/ሮ ደሚቱ ሐምቢሳ
የፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ